# መ

**መ** በዚህ መዝገበ ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ "**ለ**" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

**መ–** (ከ "አ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ማ-" ይሆናል) ከግስ አምድ መነሻ ላይ እየተቀጠለ ስሞችን ወይም አርእስትን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ። ምሳ. መስበር /መስራት/ መፃፍ።

**መሀር "መከር"**ን ተመ.

**መሃለቅ** ስ 1. የከብደት መለኪያ (ለወርቅ)። 2. ከብረት ነክ ነገሮች ክብ ሆኖ የተሰራና ለመገበያያነት ያገለግል የነበረ የድሮ ገንዘብ።

**መሃላ "ማለ"** ስር **"ማላ"**ን ተመ.

**መሃል "*ማከለ"** ስር ተመ.

***መሃረ**

**መምህር (ብ.ቁ.መምህራን)** ስ 1. አስተማሪ ። 2.(ቤ.ክህ.) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስርአት መሰረት ለገዳም አስተዳዳሪ የሚሰጥ የማእረግ ስም።

**መምህራን ማሰልጠኛ** ስ መምህራንን በመምህርነት ሙያ የሚያሰለጥን ተቋም።

**መምሬ** ስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስርአት መሰረት የቅስና ስልጣን ያለው ካህን የሚጠራበት የማእረግ ስም።

**ምሁር (ብ.ቁ.ምሁራን)** ስ በትምህርት÷ በእውቀት አእምሮው የበሰለ ሰው።

**ተማረ** ግ 1.ትምህርት ቤት ገብቶ ትምህርት ቀሰመ። 2. አወቀ÷ ለመደ÷ ሰለጠነ። *ምና ተማረ።*

**የተማረ** ትምህርት÷ እውቀት የቀሰመ፤ ምሁር።

**ተማሪ** ስ 1. ትምህርት ቤት ገብቶ በመማር ላይ ያለ ሰው። ቅ 2. ለማጅ÷ ተለማማጅ።

**ተማሪ ቤት** ስ ትምህርት ቤት።

**ትምህርት** ስ 1. ትምህርት ቤት በመግባት የሚገኝ ወይም የሚቀሰም እውቀት። 2. ከስራ ልምድ÷ ከህይወት ገጠመኝ÷...የሚገኝ እወቀት። *ካለፈው ስህተቱ ትምህርት ኣግኝቷል።*

**ትምህርት ወሰደ/አገኘ** አወቀ÷ ተረዳ÷ ተገነዘበ።

**ትምህርት ቤት** ስ ተማሪዎች በአስተማሪዎች አማካይነት የተለያየ እውቀት÷ ትምህርት የሚቀስሙበት ተቋም።

**ተማማረ** ግ እንዱ ከሌላው ትምህርት÷ እውቀት÷ ልምድ÷...ቀሰመ።

**አስተማረ** ግ 1. በትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪዎች ትምህርት ሰጠ። 2. አሳወቀ÷ አሰለጠነ። *ልብስ መተኮስ ያስተማራት እሱ ነው።* 3. እንዲማር ረዳ÷ አገዘ። *ያስተማረኝ አጎቴ ነው።*

**አስተማሪ** ስ 1. በማስተማር ሙያ ላይ የተሰማራ (ሰው)። 2. አለማማጅ÷ አሰልጣኝ።

**አስተምህሮ** ስ (ፍል.) በተወሰነ የእውቀት ዘርፍ ውስጥ ያለ መሰረታዊ ሃሳብ፤ ትምህርታዊ ይዘት፤ መርህ፤ እምነት፤ ቀኖና።

**መሃረብ (መሃረም)** ስ ለአፍንጫ÷ ለእጅ÷...ማፅጃ÷ ማበሻ እንዲሆን የተዘጋጀና በኪስ ወይም በቦርሳ የሚያዝ አነስተኛ ጨርቅ።

**መሃሪ "ማረ"** ስር ተመ.

**መሃራ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) 1. ለሙታን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ተዘጋጅቶ ለካህናት የሚሰጥ ምግብና መጠጥ። 2. ለሙታን መታሰቢያ የሚደረግ ፀሎት።

**መሃን "መከነ"** ስር **"መካን"**ን ተመ.

**መሃንዲስ** ስ የህንፃን÷ የድልድይን÷...ስራ የሚቀይስና ስራውንም የሚቆጣጠር ባለሙያ፤ ኢንጂነር።

**ምህንድስና** ስ የመሃንዲስነት ሙያ ትምህርት።

**መሃከለኛ "*ማከለ"** ስር **"መካከለኛ"** ን ተመ.

**መሃከል "*ማከለ"** ስር **"መካከል"** ን ተመ.

**መሃይም(ማይም)** (ብ.ቁ. **መሃይምናን፤ ማይምናን)** ስ 1. ማንበብና መፃፍ የማይችል ሰው። ቅ 2. (ስድብ) ጠለቅ ያለ እውቀት የሌለው።

**መሆዶ(ሞሆዶ)** 1. ስ እንደ ሞሰብ ሆኖ ከጭቃ የሚሰራ የእንጀራ ማስቀመጫ። ቅ 2. (ዘይ.) ሆዳም።

***መለለ**

**መለሉ** ቅ ቀጥ ብሉ ረዘም ያለ።

**መለል አለ** ግ ቀጥ÷ ረዘም አለ።

**መለመለ**[1] ግ ቅጠልን÷ ቅርንጫፍን ከዋናው ግንድ ላይ ቆረጠ÷ ቀነጠበ።

**መለመላ** ስ እርቃን÷ ራቁትነት።

**መለመላውን ቀረ** ያለምንም ንብረት ወይም ገንዘብ ባዶ እጁን ቀረ።

**ምልማይ** ስ ከዛፍ ወይም ከግንድ የተመለመለ ቅጠል ወይም ቅርንጫፍ።

**ምልምል** ቅ ቅጠሉ ወይም ቅርንጫፉ የተቀረጠ÷ የተመለመለ (ዛፍ÷ ግንድ÷...)።

**መለመለ[2]** ግ የሚስማማውን፥ የሚፈልገውን መረጠ (ለአባልነት፥ ለወታደርነት፥...)፡፡

**መልማይ** ቅ የሚፈለገውንና ተስማሚነት ያለውን ሰው የሚመርጥ፤ መራጭ፡፡

**ምልመላ** ስ ለአንድ ለተወሰነ ተግባር ወይም ሙያ የሚፈለገውን የሰው ሃይል የመምረጥ ስራ፡፡

**ምልምል** ቅ 1. ለተወሰነ ተግባር፥ ሙያ የተመረጠ ወይም የታጨ፡፡ *ምልምል ወታደር፡፡* 2. ወይዛዝርት በድብቅ የሚይዙት ወጣት የሆነ ወዳጅ፡፡

**መለመላ** "**መለመለ[1]**" ስር ተመ.

**መለሰ** ግ 1. አንድን ነገር ቀድሞ ወደነበረበት ቦታ አመጣ ወይም ወሰደ፡፡ 2. የተዋሰውን ነገር ለባለቤቱ ሰጠ፥ አስረከበ፡፡ 3. ለተጠየቀው ነገር ማብራሪያ ወይም መልስ ሰጠ፡፡ 4. ከፈለ፡፡ *ውለታ መለሰ፡፡* 5. ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ተረጎመ፡፡ *ፅሁፉን ወደ እንግሊዘኛ የመለሰው ጓደኛዬ ነው፡፡* 6. ደገመ፡፡ *ያንኑ እየመለሰ ተናገረ፡፡* 7.ገርበብ አደረገ (በርን፥ መስኮትን)፡፡ 8. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) አንባቢ አበላሽቶ ሲያነብ መምህሩ ወይም አድማጩ ትክክለኛውን አነባበብ ወይም ቃል ላንባቢው ነገረ፡፡ 9. ገታ፥ ከለከለ፡፡ 10. አዞረ፥ አቅጣጫውን ቀየረ፡፡ *ፊቱን ወደ ምስራቅ መለሰ፡፡* 11. አልቀበል አለ፡፡ *ማስረጃው በቂ ሳይደለም ብሎ መለሰው፡፡*

**ከ-(በ) መለስ** ከ- ወዲህ፡፡ *ከሳዋሽ በመለስ፥...፡፡*

**መለስ ቀለስ አለ** በተደጋጋሚ መጣ፥ ተመላለሰ፡፡

**መለስተኛ** ቅ መካከለኛ፡፡

**መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት** ስ የ7ኛና የ8ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥበት ት/ቤት፡፡

**መልስ** ስ 1. ለተጠየቀው ጥያቄ የሚሰጥ ማብራሪያ፥ ሃሳብ፥ አስተያየት፥...፡፡ 2. ከሄዱበት ወደነበሩበት የመምጣት ክንውን፡፡ 3. ሙሽሮች በተጋቡ በሶስተኛው ቀን የሴት ወገኖች የሚያደርጉት ግብዣ፡፡ 4. የሴቷም ሆነ የወንዱ ወገኖች ከሰርጉ በሗላ ለሙሽሮች የሚያደርጉት ግብዣ፡፡ 5. አንድን የተፈጸመ ድርጊት ተከትሎ የሚከናወን አፀፋዊ ድርጊት፡፡ 6. በክፍያ ከተሰጠ ገንዘብ ውስጥ ከሚፈለገው ሂሳብ በላይ ትርፍ በመሆኑ ለከፋዩ ተመላሽ የሚሆን ገንዘብ፡፡

**የመልስ ምት** ስ (ስፖ.) በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ኳስ በግብ መአዘን አቅጣጫ በተቃራኒው ቡድን ተጫዋቾች ወደ ውጭ ስትወጣ ጨዋታውን እንደገና ለመጀመር የሚደረግ የኳስ ምት፡፡

**የመልስ ጨዋታ** ስ (ስፖ.) ሁለት ቡድኖች አንድ ጊዜ ከተጋጠሙ በሗላ እንደገና በሌላ ጊዜና ቦታ የሚያደርጉት ግጥሚያ፡፡

**ምልሰት** ስ እንደ ስነፅሁፍ፥ ቲያትር፥... ባሉ የፈጠራ ስራዎች ውስጥ ተከታታይነት ያለውን ድርጊት ወይም ታሪክ በመሃል ለተወሰነ ጊዜ በማቋረጥና ወደሗላ በመሄድ ያለፈ ድርጊትን ማሳየት ወይም ያለፈ ታሪክን መተረክ፡፡

**ምላሽ** ስ 1.የጥያቄ መልስ፡፡ 2. ትውኪያ፥ ትፋት፤ ቅርሻት፡፡

**ምልስ** ቅ 1.ቂም የማይዝ፥ የደረሰበትን በደል ቶሎ የሚረሳ፤ ገር፡፡ 2. ቁጣው ቶሎ የሚበርድ፡፡

**መለስ አለ** ግ 1. ከበፊቱ ሻል አለ፡፡ *ንፋሱ መለስ አለ /ሰውነቱ መለስ አለ/ ንዴቱ መለስ አለ፡፡* 2. ገርበብ አለ፡፡

**መለስ ያለ** ቅ መካከለኛ፥ መጠነኛ የሆነ፡፡

**ተመለሰ** ግ 1. ቀደም ሲል ወደነበረበት ቦታ መጣ ወይም ሄደ፡፡ 2. በትውስት የተወሰደው ነገር እንደገና ለባለቤቱ ተሰጠ፤ ተከፈለ፡፡ 3. ለጥያቄው መልስ፥ መፍትሄ ተሰጠ፡፡ 4. እንደገና ሆነ፥ ተደረገ፥ ተደገመ፡፡ *የጥንቱ ሳለማለ ተመለሱ፡* 5. ተስተካከለ፥ ታረመ፥ ደህና ሆነ(ምሳ.ጠባይ)፡፡ 6. ቀደም ሲል ያልተቀበለውን አስተያየት፥ እምነት፥...አሁን ተቀበለ፥ አመነ፡፡ *ወደ ክርስትና ተመለሰ፡፡*

**ተመላሽ** ቅ 1. ወደመጣበት ወይም ወደነበረበት የሚመለስ፡፡ 2. የተረፈ፡፡ *ከከፈልኩት ገንዘብ ውስጥ 10 ብር ተመላሽ ላለሁ፡፡* 3. ለተወሰነ ጊዜ በመያዣነት ተይዞ የሚቆይ(ገንዘብ)፡፡

**ተመላለሰ** ግ 1. በተደጋጋሚ እየመጣ ሄደ፡፡ 2. ንግግር ተለዋወጠ፡፡ *ክፉና ደግ ተመላለሱ፡* 3. እርስበርስ አንዱ ለአንዱ ሰጠ፥ አደረገ፤ ውለታ፥ ብድር ተከፋፈለ፡፡ *ብድር ተመላለሰ፡፡*

**ተመላላሽ** ቅ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ በቋሚነት እየሄደና እየመጣ አንድን የተወሰነ ተግባር የሚያከናውን፡፡

**ተመላላሽ መኪና** ስ ከአንድ የተወሰነ ቦታ ወደ ሌላ የተወሰነ ቦታ የሚሄድና የሚመጣ መኪና፡፡

**ተመላላሽ ሰራተኛ** ስ ቀን ቀን ወደ ተቀጠረችበት ቤት እየሄደች በመስራት ማታ ማታ ለአዳር ወደ ቤቷ የምትመለስ የቤት ሰራተኛ፡፡

**ተመላላሽ ተማሪ** ስ የአዳሪ ተማሪ ያልሆነ፥ ለቀለቡና ለአዳሩ ወደቤቱ እየተመላለሰ የሚማር ሰው፡፡

**ተመላላሽ ታካሚ** ስ ሆስፒታል ውስጥ ሳይተኛ እየተመላለሰ የሚታከም በሽተኛ፡፡

**ኣመላለሰ** ግ 1. ሰውን፥ እቃን፥...ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ወሰደ፥ አጓጓዘ፡፡ 2. በመሄድና በመምጣት እንዲለፋ ወይም እንዲደክም አደረገ (ጉዳዩን ቶሎ ባለመፈፀም)፡፡ 3. መልስ አሰጠ፤

*አጨቃጨቀ:: የሰውየው ሳነጋገር የሚያናድድ ነበር፤ ትን ምን ላመላለሰኝ በማለት ዝም ላልኩት::*

**ማመላለሻ** ስ ማጓጓዣ (በቅሎ፥ መኪና፥ አይሮፕላን፥...)::

**አስመለሰ** ግ 1. አስታወከ:: 2. ተወስዶበት የነበረውን ነገር፥ እቃ ወይም ንብረት እንዲሰጠው አደረገ:: 3. ባቁማር የተበላውን ገንዘብ መልሶ በላ::

**መለሰኛ** "ለሰነ" ስር ተመ.

**መለሳ** ስ ታዛ፥ የእንግዳ ማረፊያ::

**መለስተኛ** "መለሰ" ስር ተመ.

**መለቀሻ** "*ለቀሰ" ስር ተመ.

**መለበጃ** "ለበደ" ስር ተመ.

**መለብለቢያ** "ለበለበ" ስር ተመ.

**መለንቀጫ** "ለነቀጠ" ስር ተመ.

**መለኛ** "መላ" ስር ተመ.

***መለከ**

**መለኮት** ስ 1. አምላክ፥ እግዚአብሔር:: 2. ረቂቅ የሆነ የአምላክ ባሀርይ::

**መለኮታዊ** ቅ አምላካዊ::

**ምልኪ** ስ 1. አንድን ድርጊት ወይም አጋጣሚ የመጥፎ ወይም የጥሩ ምልክት ላድርጎ የመውሰድ እምነት፤ ለምሳሌ ባዶ እንስራ የያዘች ሴት አንድን መንገደኛ አቋርጣው ከሄደች እንደ መጥፎ ምልክት የሚታይ ሲሆን ባንፃሩ ደግሞ ውሃ የሞላ እንስራ የተሸከመች ሴት ካቋረጠችው እንደ ጥሩ ምልክት ይወሰዳል:: 2. ለአድባር፥ ለቆሌ፥ ...ቡና ማፍላት፥ ደም ማፍሰስ፥...፤ አምልኮ ባእድ::

**ተመለከ** ግ ፀሎት፥ ምስጋና፥ መስዋእት ቀረበለት፥ ተሰገደለት፤ ታመነበት::

**አመለከ** ግ 1. በእግዚአብሄር ታመነ፥ ለእግዚአብሄር ተገዛ:: 2. ለጣዖት ሰገደ፥ ተገዛ:: 3 (ዘይ.) ተማመነ፥ ተመካ፤ እንደ አምላክ ቆጠረ::

**አመለከበት** 1.ተማመነበት:: 2. አሚረተበት፥ ከፉ ተመኘበት::

**ማምለኪያ** ስ አምልኮ የሚፈፀምበት ቦታ ወይም የሚመለከበት ነገር::

**አምላክ** ስ እግዚአብሄር::

**አምልኮ(አምልኮት)** ስ 1. ለእግዚአብሄር መገዛት፥ መታመን:: 2. ለጣኦት፥ ለአድባር፥... መስገድ፥ መገበር::

**አምልኮ ባእድ** ስ ለጣዖት፥ ለአድባር፥... መገዛት፥ መስገድ::

**አምልኮኛ** ቅ 1. በቆሌ፥ በውቃቢ፥... የሚያምን፥ የሚያመልክ:: 2. እንደ ውሻ ማላዘን፥...ያሉትን ነገሮች እንደ መጥፎ ወይም እንደ ርግብ፥ ንብ፥ ...ያሉትን ነገሮች ደግሞ እንደ ጥሩ ምልክቶች በመውሰድ እንዲህ ይሆናል ብሎ የሚተነብይ ወይም የሚያምን (ሰው)::

***መለከተ**

**ምልክት** ስ 1.አንድን ነገር ከሌላው ለመለየት የሚያስችል መለያ:: 2. አንድን ነገር ለመጠቆም ወይም ለማሳየት፥ ፍንጭ ለመስጠት፥... የሚያገለግል ስእል፥ ፅሁፍ፥ ድምፅ ፥ እንቅስቃሴ፥...::

**ምልክት ሰጠ** 1. ጠቆመ፥ አሳየ:: 2. መለያ አበጀ::

**ለምልክት ያህል** 1. በጣም በጥቂቱ፥ በትንሹ:: 2. ምልክት እንዲሆን::

**ተመለከተ** ግ 1. አየ:: 2. ልብ ብሎ አየ፥ አስተዋለ::

**በተመለከተ** አስመልክቶ::

**ተመልካች** ቅ 1. ታዛቢ:: 2. ተቆርቋሪ፥ ጠባቂ:: 3. ሲኒማን ወይም ቲያትርን ወይም ኳስ ጨዋታን ለመመልከት የሚሄድ ሰው ወይም ህዝብ::

**ተመልካች ነው** አስተዋይ ነው::

**ለሚመለከተው ሁሉ** ጉዳዩ ለሚያገባው ሁሉ::

**አይመለከተውም** አያገባውም::

**ተመለካከተ** ግ በደንብ ሳይሆን ላይ ላዩን ወይም አለፍ አለፍ ብሎ አየ::

**ተመላከተ** ግ ከሌላ ቃል ወይም ነገር ጋር ተጣቀሰ::

**አመላከተ** ግ 1.አሳየ፥ ጠቆመ:: 2. አቤቱታ አቀረበ (በፅሁፍ ወይም በቃል):: 3. አሳሰበ፥ አሳወቀ፥ ጠየቀ (በፅሁፍ ወይም በቃል)::

**ማመልከቻ** ስ አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም፥ ለማስታወስ፥... በፅሁፍ የሚቀርብ የጥያቄ፥ የአቤቱታ፥... ደብዳቤ::

**ማመልከቻ አቀረበ /ሰጠ** በፅሁፍ አመለከተ::

**አመልካች** ቅ 1. የሚያሳይ፥ የሚያመለክት፥ ጠቋሚ:: 2. አቤቱታ አቅራቢ፥ ጠያቂ::

**አመልካች ተውላጠ ስም** ስ እንደ ይህ፥ ያ፥ እነዚህ፥ እነዚያ፥... ያሉ ተውላጠ ስሞች::

**አመልካች ጣት** ስ ከእጅ አውራ ጣት ቀጥሎ የሚገኝ ጣት፤ ሌባ ጣት(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)::

**አመላከተ** ግ አሳየ፥ ጠቆመ:: *ደሀና ጫማ መግዛት የምችልበትን ቦታ ላመላክተኝ::*

**አስመለከተ** ግ አሳሰበ፥ አሰኘ፥ አስመኘ::

*ምን እንዳስመለከተው እንጃ ቤተ ክርስቲያን ሳዘውትርኣል።*

**አስመልክቶ** ስለ። *ኢትዮጵያን ኣስመልክቶ ብዙ መናገር ይቻላል።*

**ኣመለካከት** ስ አስተያየት፥ የአስተሳሰብ አቅጣጫ፣ ርእዮተ አለም።

**መለከት** ስ የጥሩንባ ኣይነት (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**መለኩሴ** "**መነኮሰ**" ስር "**መነኩሴ**"ን ተመ.

**መለኪያ** "**ለካ**¹" ስር ተመ.

**መለኮሰ** "**መነኮሰ**" ን ተመ.

**መለኮሻ** "**ለኮሰ**" ስር ተመ.

**መለኮታዊ** "***መለከ**" ስር ተመ.

**መለወጫ** "**ለወጠ**" ስር ተመ.

**መለያ** "**ለየ**" ስር ተመ.

**መለያያ** ዝ.ከ.

**መለዮ** ዝ.ከ.

**መለገ**¹ (**መለገገ**) ግ ጠባ፥ መጠመጠ (ጡትን)።

**መለገ**² ግ ሸመቀ፥ አደባ።

**መለጎደ** ግ መታ።

**መለጠ** ግ 1. ፀጉርን ላጨ፥ ሙልጭ አድርጎ ነቀለ ወይም ነጨ። 2. ቆዳን፥ ልጥን፥...ገፍፎ አነሳ፥ ላጠ። 3.ፀጉሩ ሙልጭ ብሎ ተነቀለ ወይም ረገፈ፤ መላጣ ሆነ። 4. በአርጩሜ፥ በጅራፍ፥...ገረፈ።

**መሊጥ** ቅ (ስድብ) ራሰ በራ የሆነ ወይም ፀጉሩ ሙልጭ ብሎ ያለቀ ወይም የተነሳ።

**መላጣ** ቅ 1.ፀጉሩ ሙልጭ ብሎ የተነሳ። 2. ራሰ በራ። 3. ሳር፥ ዛፍ፥...የሌለበት፤ ገላጣ (መሬት)።

**ተመለጠ** ግ 1.ተላጨ፤ መላጣ ሆነ። 2. ራሰ በራ ሆነ።

**ተመላለጠ** ግ ተላላጠ፥ ተገጣጠበ፥ተገሸላለጠ።

**መላ** ስ ዘዴ፥ ብልሃት።

**መላ መታ** 1. ዘዴ፥ ብልሃት ፈጠረ። 2. የግምት ወይም የይሆናል አስተያየት አቀረበ፥ ሰጠ።

**መላ ቅጡ/ቅዱሱ ጠፋ** 1. ስርኣት ኣጣ። 2. ተዘበራረቀ።

**መላ ቅጡ ጠፋው** 1. ግራ ገባው፥ ተጨነቀ፥ ተምታታበት። 2. የሚሆነውን፥ የሚሰራውን ኣሳጣው።

**መላቅጥ ኣጣ** መላ ቅጡ ጠፋ።

**መላ ቅጥ የለውም** 1. ስርኣት፥ መልክ የለውም። 2. ስራው የማይጨበጥ ነው፥ ውል የለውም።

**መላ የለውም** 1. ዋጋ፥ ጥቅም የለውም። 2. መፍትሄ የለውም። 3. ስርኣት፥ ቅጥ የለውም።

**መላ ጣለ** 1. ገመተ፥ እንዲህ ሳይሆን ኣይቀርም ኣለ። 2. ዘዴ፥ ብልሃት ፈጠረ።

**በመላ** በግምት፥ በይሆናል።

**መለኛ** ቅ ብልሃተኛ፥ ዘዴኛ።

**መላ ምት** ቅ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ንድፈ ሃሳብ፥ የግምት ኣባባል።

**መላ ቢስ** ቅ 1.ቅጥ ያጣ፥ ስርኣት የሌለው። 2. ደንጋራ፥ ዘዴ የለሽ።

**መላ** ግ ሞላ።

**መላ** ቅ ጠቅላላ። *መላ ሰውነቴን ሳምኛል።*

**መላው** ሁሉም፥ ጠቅላላው። *መላው የኢትዮጵያ ህዝብ።*

**በመላ** በጠቅላላ፥ ሁሉም።

**መላላጫ** "**ላጠ**¹" ስር ተመ.

**መላምት** "**መላ**" ስር ተመ.

**መላሸ** "**ላሰ**" ስር ተመ.

**መላቀቂያ** "**ለቀቀ**" ስር ተመ.

**መላቢስ** "**መላ**" ስር ተመ.

**መላከ ሞት** "**መልኣክ**" ስር ተመ.

**መላከ ፅልመት** ዝ.ከ.

**መላው** "**መላ**" ስር ተመ.

**መላጃን** ስ በቀድሞ ጊዜ ንጉስ ከነሰራዊቱ የሚያርፍበትና ግብር የሚያበላበት ትልቅ ድንኳን።

**መላጊያ** "**ላገ**" ስር ተመ.

**መላጣ** "**መለጠ**" ስር ተመ.

**መልህቅ** ስ መርከብ በውሃ ወይም በነፋስ ግፊት እንዳትነዳ ወይም እንዳትንቀሳቀስ ወደ ታች ወጥሮ የሚይዝ መንጠቆ መሰል ከባድ ብረት።



መልህቅ

**መልህቅ ኣነሳ** ተንቀሳቀሰ፥ ጉዞ ጀመረ (መርከብ)።

**መልህቅ ጣለ** ቆመ (መርከብ)።

**መልማይ** "መለመለ[2]" ስር ተመ.

**መልስ** "መለሰ" ስር ተመ.

**መልቀሚያ** "ለቀመ" ስር ተመ.

**መልቀቂያ** "ለቀቀ" ስር ተመ.

**መልቲ** ቅ አታላይ፥ አጭበርባሪ፥ ቀጣፊ።

**መልአክ** (ብ.ቁ.**መላእክት**) ስ 1. የፈጣሪ መልእክተኛ፥ አገልጋይ የሆነና የማይሞት ረቂቅ ፍጡር። 2. (ዘይ.) ደግ፥ ሩህሩህ፥ ግብረ መልካም ሰው።

**መላከሞት** ስ ነፍስን ከስጋ ለመለየት የሚላክ መልአክ።

**መላከ ሞት የመሰለ** በመከሳቱ፥ በመገርጣቱ ወይም በመጎሳቆሉ የተነሳ ገፅታው የሚያስፈራ (ሰው)።

**መላከ ፅልመት** ስ የጨለማ መልአክ፤ ሰይጣን።

**መልእክተኛ** "ላከ" ስር ተመ.

**መልእክት** ዝ.ከ.

**መልከ መልካም** "መልክ" ስር ተመ.

**መልከ ቀና** ዝ.ከ.

**መልከ ቢስ** ዝ.ከ.

**መልከኛ[1]** ስ በየገጠሩ ሰፊ ርስት እየተሰጠው ይኖር የነበረ የንጉስ ወገን ወይም ባለሟል።

**መልከኛ[2]** "መልክ" ስር ተመ.

**መልካ** ስ ጥልቀትና አባጣ ጎባጣ የሌለው በመሆኑ ለመሸጋገሪያ የሚሆን የወንዝ ውሃ የሚያልፍበት ቦታ።

**መልክ** ስ 1. ፊት ወይም ገፅታ። 2. ውበት፥ ቁንጅና። *መልክ የላትም ፉንጋ ናት*። 3. ቀለም። *መኪናህ መልኩ ምን ዓይነት ነው?* 4. የአንድ ነገር ውጫዊ ገፅታ። 5. በአምስት በአምስት ስንኝ በግጥም የተዘጋጀ የምስጋና ድርሰት።ምሳ.መልከማርያም፥ መልከኢየሱስ፥...።

**መልክ አወጣ** ቆነጀ፥ አማረ።

**መልክ ያዘ** ስርአት ያዘ፥ ተስተካከለ።

**በመልክ በመልኩ** በአይነት በአይነቱ፥ በተገቢው ቦታ።

**መልከ መልካም** ቅ መልኩ የሚያምር፥ ውብ፥ ቆንጆ።

**መልከ ቢስ** ቅ መልከ ጥፉ።

**መልከ ቀና** ቅ ቆንጆ፥ ውብ፥ ሸጋ።

**መልከኛ** ቅ ቆንጆ፥ ውብ፥ ሸጋ።

**መልከጥፉ** ቅ የማያምር፥ አስቀያሚ።

**መልካም** ቅ ጥሩ፥ ማለፊያ፥ ደግ።

**መልኬ ጠፋኝ** አሁንም አሁንም መልኳን በመስታወት ማየት የምትወድ(ሴት)።

**መልክአ ምድር** ስ የመሬት አቀማመጥ ወይም ገፅታ።

**መልክተኛ** "ላከ" ስር "መልእክተኛ"ን ተመ.

**መልክአምድር** "መልክ" ስር ተመ.

**መሎጊያ** ስ እቃን በወሳንሳ ለመሸከም የሚያገለግል እንጨት።

**መመሪያ** "መራ" ስር ተመ.

**መመኪያ** "*መካ" ስር ተመ.

**መሙሊያ** "ሞላ" ስር "መሙያ"ን ተመ.

**መማለጃ** "ማለደ" ስር ተመ.

**መማክርት** "መከረ" ስር ተመ.

**መምህር** "*መሃረ" ስር ተመ.

**መምሬ** ዝ.ከ.

**መምቻ** "መታ" ስር ተመ.

**መምች** ዝ.ከ.

**መሚጫ** "ሚጠ" ስር ተመ.

**መረመረ** ግ 1. ሃኪም በሽታን፥ የጤንነትን ሁኔታ፥... የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎችን በመጠቀም ወይም ታካሚውን በቃል በመጠየቅ ለማወቅ ሞከረ። 2. የተደበቀን ነገር ወይም ምስጢር ለማወቅ ጠየቀ፤ አውጣጣ። 3. አንድን ጉዳይ በደንብ ተመለከተ፥ አጠና፥ አገናዘበ። 4. ፈተሸ፥ ፈተነ። *ለመሻገር ከመሞከርህ በፊት የውሃውን ጥልቀት በዱላህ መርምረው።*

**መርማሪ [ፖሊስ]** ስ ወንጀል ነክ ጉዳዮችን እየተከታተለ የሚያጣራ የፖሊስ አባል።

**ምርመራ** ስ 1. በሽታን፥ የጤንነትን ሁኔታ፥...ለማወቅ ሃኪም የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎችን በመጠቀም ወይም ታካሚውን በቃል በመጠየቅ የሚያደርገው ጥናት፥ ክትትል። 2. ስለ አንድ ነገር ሁኔታ፥ ምንነት፥...ለማወቅ የሚደረግ ፍተሻ፥ ጥናት።

**ምርመራ አደረገ** ግ ህክምና አደረገ፥ በሃኪም ታየ።

**ምርምር** ስ አዲስ ግኝት ለማግኘት ወይም ስለ አንድ ነገር ሁኔታ፥ ምንነት፥ ተፈጥሮ፥... ተጨማሪ መረጃ ለማሰባሰብ የሚደረግ ጥናት።

**ተመራመረ** ግ 1.የምርምር ስራ አካሄደ። 2. በሃሳብ ተራቀቀ፤ ተፈላሰፈ።

**ተመራማሪ** ስ የምርምር ስራ የሚያካሄድ ሰው።

**አመራመረ** ግ 1. አጠያየቀ፥ አፈላሰፈ። 2. አፈላለገ።

**ያመራማሪ** ስ አንድ እቃ በጠፋ ጊዜ ለአፈላለገ ሰው ወይም አካል የሚሰጥ ገንዘብ

ወይም ሌላ ነገር።

**መረመር** ስ ውሃ የበረበረው ጉድባ፥ ፈፋ።

**መረማመጃ** "*ረመደ" ስር ተመ.

**መረረ** ግ 1. ጣእሙ እንደ ሬት ወይም እንደ ኮሶ ሆነ። 2.ከረረ (ለነገር)። 3. (ዘይ.) አንገፈገፈ፥ ሰለቸ። *ኑሮ መረረው።*

**መሪር** ቅ የከፋ፥ የጠለቀ። *መሪር ሃዘን።*

**መራራ** ቅ 1. ጣእሙ ሬት ሬት ወይም ኮሶ ኮሶ የሚል። 2. መሪር።

**መራር** ዝ.ከ.

**ምሬት** ስ 1. ኮሶ ኮሶ ወይም ሬት ሬት የማለት ጣእም።2.(ዘይ.)የመሰልቸት፥ አጥብቆ የመጥላት፥ የመንገፍገፍ ስሜት።

**ምር** ስ እውነት።

**የምር/ከምር** የእውነት፥ የቀልድ ሳይሆን።

**ተመረረ** ግ ሰለቸ፥ ተንገፈገፈ።

**ተማረረ** ግ 1. ዝ.ከ. 2. ተካረረ፥ የምር ጥል ተጣላ።

**አመረረ** ግ 1. ቀልዱን የምር አደረገ፥ ተቆጣ። 2. ኮስተር ብሎ.አንድን ነገር ማከናወን ቀጠለ።

**አምርሮ ተናገረ** በብሶት፥ በብስጭት፥ በቁጭት ስሜት ተናገረ።


**አምርሮ አለቀሰ** በጣም አለቀሰ።

**አማረረ** ግ 1. በጣም አዘነ፣ ብሶት አሰማ። 2. አሳጣ፥ ወቀሰ። *ስለደረሰበት ችግር የሚያማርረው ዘመዶቹን ነው።*

**አስመረረ** ግ 1. አንገፈገፈ፥ አሰለቸ። *ኑሮ አስመረረው።* 2. አበሳጨ፥ አናደደ።

**መረሬ** ስ ርጥበት ባጣ ጊዜ የሚሰነጣጠቅ ጥቁር አፈር ወይም መሬት።

**መረሸት** ስ በበቅሎ አንገት የሚደረግ ባለ መርገፍ ጌጥ።



መረሸት

**መረሻት** ስ በሃር፥ በወርቀዘቦ፥ በጥልፍ የተሸለመና በበቅሎ ኮርቻ ላይ የሚደረግ ባለጌጥ ልብስ።

**መረቀ** ግ 1. ባረከ፣ ጥሩ ነገር ይስጥህ፥ ያጋጥምህ ብሎ ምኞቱን ገለፀ። 2. የተሰጠህ ስጦታ ይገባሃል፥ የተባረከ ይሁንልህ በማለት አፀደቀለት። *አዲስ የተገዛለትን ልብስ መረቀለት።* 3. ከገዛው ነገር በላይ ሻጭ ለገዢ ተመሳሳይ ወይም ሌላ ነገር ጨምሮ ሰጠ። *ስኳር ሲገዛ ባለሱቁ ከረሜላ መረቀለት።* 4. (ኢ.አ.ተ.ቤ.) ለመምህርነት በቅተሃል ብሎ ማረጋገጫ ሰጠ፥ መሰከረ፥ አስተምር ብሎ ፈቀደ።

**መርቆ ከፈተ** አንድ የተጋበዘ የክብር እንግዳ አዲስ ተቋም፥ ድርጅት፥ ኤግዚቢሽን፥ ሴሚናር፥...ሲከፈት በሚደረገው ልዩ ስነስርአት ላይ በመገኘት ስራው መጀመሩን ወይም መከፈቱን በይፋ አስታወቀ፣ ገለፀ።

**ምረቃ** ስ 1. በልዩ ልዩ የትምህርት ተቋሞች ውስጥ የሚሰጡትን የቀለም ወይም የሙያ ትምህርቶችን ላጠናቀቁ ተማሪዎች የምስክር ወረቀት፥ ዲፕሎም፥ ዲግሪ ለመስጠት የሚካሄድ ስነስርአት። 2. አዲስ የተሰራ ቤት፥ ሃውልት፥... ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲታይ ወይም እንዲጎበኝ ሲባል የሚካሄድ ስነስርአት። 3. የወለደን ወይም ከአደጋ የተረፈን ወይም ሌላ ጥሩ ነገር ያጋጠመውን ሰው "እንኳን ደስ አለህ" ወይም "እንኳን አተረፈህ"...ለማለት የሚደረግ ጉብኝት።

**ምሩቅ** ቅ 1. ቡሩክ። ስ 2. አንድ የተወሰነ ትምህርት ወይም ሙያ ተከታትሎ ያጠናቀቀና የምስክር ወረቀት ወይም ዲፕሎም ወይም ዲግሪ ያለው። *የስነፅሁፍ ምሩቅ።*

**ምራቂ** ስ 1. ከዋጋ ውጪ ሻጭ ለገዢ (ከገዛው ነገር በተጨማሪ) የሚሰጠው ተመሳሳይ ወይም ሌላ ነገር። 2. (ዘይ.) ሰውነቱ ቀጭንና አጭር የሆነ ሰው።

**ምርቃት** ስ 1. በጎ ስራ ለሰራ ሰው "ተባረክ"፥ "እድሜ ይስጥህ" በማለት የሚሰነዘር የመልካም ምኞት መግለጫ። 2. ምራቂ። 3. ምረቃ።

**ተመረቀ** ግ በቀለም ወይም በሙያ ትምህርት ተቋሞች ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ተከታትሎ በመጨረሱ የምስክር ወረቀት ወይም ዲፕሎም ወይም ዲግሪ ተሰጠው።

**ተመራቂ** ስ በቀለም ወይም በሙያ ትምህርት ተቋሞች ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ተከታትሎ በማጠናቀቅ የምስክር ወረቀት ወይም ዲፕሎም ወይም ዲግሪ ለመቀበል የተዘጋጀ ተማሪ።

**አስመረቀ** ግ አንድ የትምህርት ተቋም፥ ድርጅት፥...ለማስተማር የተቀበላቸውን ተማሪዎች አስተምሮ ወይም አሰልጥኖ አወጣ።

**መረቀነ** ግ 1. በጫት ሰከረ። 2. ተመኘ፥ ጓጓ፥ ፈለገ።

**ምርቃና** ስ ጫት በመቃም የሚመጣ ስካር።

**መረቀዘ** ግ ውስጥ ውስጡን በጣም ቆሰለ፥ ቂም ያዘ (ቁስል)።

**አመረቀዘ** ዝ.ከ.

**መረቅ** ስ 1. ስጋ የተቀቀለበት ውሃ:: 2. እንደ ስጋ፥ ድንች፥ ዶሮ፥... ያለ ወጥ ፈሳሹ ክፍል:: 3- ልብስ የታጠበበት የእንዶድ፥ የሳሙና፥ የኦሞ አረፋ:: *በሹራቡ መረቅ ሸሹን አጠቢበት::*

**ከነመረቁ አጠጣው** አጠገቡ ሆኖ ከላዩ ላይ በመደገን ተኩሶ መታው::

**መረባርብ "ረበረበ"** ስር ተመ.

**መረብ** ስ 1. ከገመድ ወይም ከክር ጥልፍልፍ ሆኖ የተሰራ የአሳ ማጥመጃ፣ መርበብ:: 2. በእግር ኳስ፥ በጠረጴዛ ኳስ፥ በእጅ ኳስ፥ በሜዳ ቴኒስ ጨዋታ ጊዜ በቋሚ እንጨቶች ወይም ብረቶች ተወጥሮ የሚዘረጋ ከክር፥ ከገመድ፥... ጥልፍልፍ ሆኖ የተሰራ የስፖርት እቃ:: 3. አንድ ድርጅት ወይም ቡድን አንድን ስራ የሚያከናውንበት ተዋረድ፣ መዋቅር::

**መረብ ዘረጋ** የአንድን ድርጅት የተለያዩ መዋቅራዊ አካላት መሰረተ፥ አዋቀረ::

**መረብ ጣለ** አሳ ለማጥመድ መረቡን ወደ ባህር ውስጥ ወረወረ::

**መረብ ስራ** ስ በክር፥ በገመድ፥...እንደ መረብ ተጠላልፎ የሚሰራ የእጅ ስራ::

**መረብ ኳስ** ስ (ስፖ.) ግራና ቀኝ በተተከሉ የእንጨት ወይም የብረት ቋሚዎች ላይ በተወጠረ መረብ፥ ስድስት ስድስት ሰዎችን የያዙ ሁለት ቡድኖች፥ ኳስን በእጅ በመቀባበል በመረቡ ላይ አሳልፎ በተቃራኒ ሜዳ ላይ ለማሳረፍ የሚያደርጉት የውድድር ጨዋታ::

**መረተ**[1] ግ 1.ፍሬው ከእብቅ፥ ከገለባ ተለየ:: 2. ብዙ ፍም ወረደ፥ ተንደረከከ::

**ምርት** ስ 1. በእርሻ፥ በፋብሪካ፥...ተሰርቶ የሚገኝ ማንኛውም ውጤት:: 2. እህሉ ተወቅቶ፥ ከእብቅና ከገለባ ተለይቶ የሚገኘው የተጣራ ፍሬ::

**ምርታማ** ቅ 1. ጥሩ ምርት የሚሰጥ ወይም የሚያስገኝ:: 2. ብዙ የስራ ፍሬ የሚያስገኝ፥ ውጤታማ::

**ተመረተ** ግ 1. ምርት ተገኘ:: 2. ተሰራ፥ ተዘጋጀ:: *ዘንድሮ ብዙ ጤግ ተመርቷል::*

**አመረተ** ግ 1. እህልን ዘርቶ፥ አጭዶና ወቅቶ ፍሬ አገኘ፤ አዘመረ:: 2. በፋብሪካ ልዩ ልዩ ነገሮችን ሰርቶ አወጣ::

**አምራች** ስ ምርት በሚያስገኝ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው::

**ማምረቻ** ስ ለምርት ስራ አገልግሎት የሚውል መሳሪያ::

**መረተ**[2] ግ ዛገ፥ መሬት መሰለ::

**መረነ** ግ ሞፈርና ቀንበርን በምራን አቆራኘ ወይም አሰረ::

**ምራን** ስ ሞፈርን ከቀንበር ጋር ማቆራኛ ወይም ማሰሪያ ጠፍር::(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)::

**መረን** ቅ ልቅ፥ ባለጌ፥ ስድ::

**መረን ለቀቀ** ሳይቆጣ ወይም ሳይቆጣጠር ቀረ፤ አባለገ (ልጅን)::

**መረን ወጣ** ስድ፥ ባለጌ ሆነ::

***መረከዘ**

**ምርኩዝ** ስ ለመደገፊያነት የሚያገለግል፥ ከብረት ወይም ከእንጨት የሚሰራና ሰዎች በእጃቸው የሚይዙት በትር፤ ከዘራ::

**የምርኩዝ ዝላይ** ስ (ስፖ.) በረዥም ምርኩዝ በመታገዝ ከተወሰነ ቦታ ላይ ጀምሮ ወደ ሰማይ በመነሳትና በሁለት ቋሚዎች ተደግፎ የተጋደመ ዘንግን ተወርውሮ ለማለፍ የሚደረግ የዝላይ አይነት:: የከፍታ ዝላይም ይባላል::

**ተመረከዘ** ግ ተረዳ፥ ታገዘ፥ ተደገፈ (በምርኩዝ፥ በመቋሚያ)::

**__ተመርኩዞ**_ምክንያት፥ መነሻ በማድረግ::

**አስመረከዘ** ግ እንዲመረኮዝ አደረገ፥ አስደገፈ::

**__አስመርኩዞ** ---ን መነሻ፥ ምክንያት አድርጎ::

**መረዋ** ስ 1. የቤተክርስቲያን ደውል ወይም ቃጭል:: 2. (ዘይ.) ቀጭንና የሚያምር (ድምፅ)::

**መረዘ** ግ 1. መርዝ አደረገ፤ በመርዝ በከለ:: 2. በጣም ጠላ፥ በክፉ ተመለከተ:: 3. (ቀለም፥ ቅባት፥...) ከነካው ነገር ላይ አለቅም አለ:: *ሻንጣው ውስጥ የነበረው ቀለም ፈስሶ ልብሶቹን መረዛቸው::*

**መራዥ** ቅ አነጣጣሪ፥ ተኩሶ የማይስት::

**መርዝ** ስ 1. ሲበላ ወይም ሲጠጣ ወይም ሲሸተት ወይም ሲነካ፥... ህመም ወይም ሞት ሊያስከትል የሚችል ነገር:: 2. ለመልቀቅ የሚያስቸግሩ ነገሮችን ለማስለቀቅ እንዲሁም የተለያዩ ነገሮችን ለመቀመም፥... የሚያገለግል ንጥረ ነገር::

**መርዘኛ** ቅ 1. መርዝ ያለው:: 2. ቂመኛ፥ ክፉ:: 3. ነገረኛ::

**ተመረዘ** ግ በመጥፎ ፀባይ ወይም ልማድ፥...ተያዘ፥ ተበከለ፥ ተበላሸ::

**መረዳጃ "ረዳ"** ስር ተመ.

**መረጃ "*ረዳ"** ስር ተመ.

**መረገ** ግ 1. በእንጨት የተሰራን የቤት ግድግዳ በጭቃ ለጠፈ:: 2. እንደ እንስራና ጋን ያሉትን የሸክላ እቃዎች አፍ ወይም ሰባራና ሽንቁርን አሸገ፥ ደፈነ:: 3. (ዘይ.) የራስን ጥፋት በሌላ አመካኘ፤ አላከከ:: *የራሱን ጥፋት በልጁ ላይ*

መረዝበት።

**መራጊ** ቅ ጭቃ መራጊ፥ ጭቃ ለጣፊ።

**መርግ** ስ ትልቅ ናዳ።

**ምርጊት** ስ 1. ከጭድ ጋር ተቦክቶ ከእንጨት በተሰራ የቤት ግድግዳ ላይ የተመረገ ልጥፍ ጭቃ። 2. ከጭድ ወይም ከገለባና ከሳር ጋር ተደባልቆ ከተቦካ ጭቃ የተበጀ የእንስራ፥ የድብኝት፥... ክዳን። 3. እንደ እንስራና ጋን ያሉ የሸክላ እቃዎች አፍ ወይም ሰባራና ሽንቁር የተደፈነበት ጭቃ። 4. (ዘይ.) የማይናገር፥ ዝምተኛ፥ ልጉም።

**ምርጊት ፊት** ስ ሁልጊዜ ፊቱ ላይ ፈገግታ የማይታይበት ሰው።

**ምርግ** ቅ 1. የተመረገ። ስ 2. ገና ያልተለሰነ፥ የጭቃ ልጥፍ ግድግዳ 3. የ"**ምርጊት**"ን 4ኛ ፍቺ ተመ.

**ምርግ አለ** ግ (ዘይ.) ልጉም አለ፤ ዝም አለ።

**መረገተ** ግ በጥፊ መታ፤ ደረገመ።

**መረገደ** ግ በክበርና በፀናፅል ድምፅ እየታጀበ ከአቋቋም የትምህርት አይነት አንዱ በሆነው በመረግድ የዜማ አወራረድ ስልት አዜመ።

**መረግድ** ስ ከአቋቋም የትምህርት አይነቶች አንዱ የሆነ በክበርና በፀናፅል ድምፅ እየታጀበ የሚባል ዜማ።

**አመረገደ** ግ መረገደ።

**መረገገ** ግ ጎመዘዘ፥ ከመጠጠ።

**መረጋገጫ "ረገጠ"** ስር ተመ.

**መረግድ "መረገደ"** ስር ተመ.

**መረጠ** ግ 1. የሚሻለውን፥ የሚስማማውን ወይም የሚፈልገውን ከሌላው ለይቶ አነሳ፥ አወጣ፥ ወሰደ። 2. ለአንድ አይነት ስራ ወይም ሹመት አጨ፥ ጠቆመ፥ መለመለ።

**አይመርጥም** 1. አያዳላም፥ አይለይም። 2. ጥሩም ሆነ መጥፎ ያገኘውን ሁሉ ያግበሰብሳል።

**ምራጭ** ቅ ከአንድ ነገር ላይ ደህና ደህናው ወይም የተሻለው ተወስዶ የቀረ፤ የማይፈለግ።

**ምርጥ** ቅ ከሁሉም የሚሻል፥ የሚበልጥ፤ ተፈላጊ።

**ምርጫ** ስ 1. ከቀረቡት ወይም ካሉት ልዩ ልዩ ነገሮች፥ አማራጮች፥...ተፈላጊውን ወይም ተስማሚውን የመጠቆም ወይም የመምረጥ ተግባር። 2. ፍላጎት። *አስተማሪ የሆነው በምርጫው ነው።* 3. ለአንድ ጥያቄ ከሚቀርቡት የተለያዩ መልሶች ተፈታኙ ትክክለኛውን ለይቶ ሊመርጥ ወይም ሊጠቁም የሚችልበት የፈተና አይነት።

**ተመረጠ** ግ 1.ለአንድ አይነት ተግባር ታጨ። 2- ከሌላ ነገር ጋር ሲወዳደር የተሻለ ሆኖ ተገኘ።

**ተመራጭ** ስ ለአንድ አይነት ስራ፥ ስልጣን፥... ብዙ ድምፅ አግኝቶ የተመረጠ ሰው።

**ተመርጦ የቀረ** ምራጭ።

**አማረጠ** ግ 1. አወዳደረ፥ አስተያየ፤ የሚሻለውን ለየ። *የምትፈልገውን አይነት አማርጠህ ግዛ።* 2. ከቀረቡት ነገሮች መሃል ደስ የሚለውን ወይም የሚፈልገውን ለይቶ እንዲወስድ እድል ሰጠ፥ ፈቀደ፥ አስመረጠ።

**አማራጭ** ቅ በአንድ ነገር ፈንታ በተለዋጭ ሊወሰድ ወይም ሊደረግ የሚችል።

**አስመረጠ** ግ 1. ከቀረቡት ነገሮች የወደደውን እንዲመርጥ ፈቀደ፤ አማረጠ። 2. የምርጫ ስነ ስርአት አካሄደ፥ መራ። 3. ሌላው ሰው እንዲመርጥ አደረገ። *ለማህበሩ ሊቀመንበርነት ያስመረጠው ጓደኛው ነው።*

**አስመራጭ[ኮሚቴ]** ቅ የምርጫውን ስነስርአት የሚያካሄድ ወይም የሚመራ አካል።

**መሪ "መራ"** ስር ተመ.

**መሪር "መረረ"** ስር ተመ.

**መራ** ግ 1. ፊት ፊት ሄደ፥ ቀደመ። 2.ሰጠ(*መሬትን*)። 3. የተደበቀን፥ የተሰወረን ነገር ወይም እቃ ጠቆመ፥ አሳየ፥ አመለከተ። 4. ስብሰባን፥ ስራን፥ ጦርነትን፥...በአስተባባሪነት ወይም በበላይነት አካሄደ። 5. አስተዳደረ፥ ገዛ። 6. አስተላለፈ፥ ወደ ሌላ አሻገረ (ጉዳይን፥ አቤቱታን፥...)። *ጉዳዩን ወደ አስተዳደር ክፍል መሩት።* 7. ሌላው ሰው የሱን ሃሳብ፥ ፍላጎት እንዲከተል አደረገ። *እሁቱ በሱ ሃሳብ እንድትመራ ይፈልጋል።* 8. (ቤ.ክህ.) ተመሪው ከመሪው እየተቀበለ እንዲያዜም መሪው ቀደም ቀደም እያለ ለተመሪው ነገረው። 9. አይነስውርን ሬዳ (እጁን ይዞ መንገድ በማመልከት፥ አብሮ በመጓዝ)።

**መሪ** ስ 1. ገዥ፥ አስተዳዳሪ፥ የበላይ አዛዥ። 2. ፊት ፊት ሂያጅ፤ መንገድ የሚያሳይ(ለምሳሌ መንገድ መሪ፥ እውር መሪ)። 3. የመኪና፥ የባቡር፥ የአይሮፕላን፥... አካል የሆነና አቅጣጫውን ለማስያዝ ወይም ለመቀየር የሚያገለግል መዘወሪያ። 4. (ቤ.ክህ.) በማህሌት ወይም በሌላ የዜማ ስነስርአት ላይ የተወሰኑ ዜማዎችን ወይም ቅኔን ለተመሪው እየነገረ እንዲዜም የሚያደርግ የእለቱ ተረኛ ካህን፤ መዘምር። 5. ጠቋሚ፥ አመልካች (ለምሳሌ የሌባ መሪ)። 6. አለቃ፥ አስተባባሪ (የቡድን፥ የስራ፥...)። 7. ሰጭ፥ ደልዳይ (በታን)።

**መሪ ቃል** ስ ብዙውን ጊዜ በሃገር መሪ የሚነገርና እንደመመሪያ ወይም መርህ የሚጠቀስ ንግግር።

**መሪ ተዋናይ** ስ 1. በአንድ ተውኔት ውስጥ አቢዩን ክፍል የሚጫወተው ገፀባህርይ። 2.

ቀንደኛ፥ ዋና::

**መሪ ጌታ** ስ (ቤ.ክህ.) 1. በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚካሄደውን የዜማ ስርአት በቋሚነት እንዲመራ የተመደበ መምህር:: 2. በአንዳንድ የገጠር ቤተክርስቲያን ከማህሌቱ አገልግሎት ስራ በተጨማሪ የአስተዳዳሪነቱን ስራ ደርቦ የሚሰራ የቤተክርስቲያን አለቃ::

**ምሪት** ስ 1. በመንግስት የተሰጠ መሬት:: 2. አንድን የመንግስት ጉዳይ ለማስፈፀም የተላከ ወታደር፥ የመንግስት ባለስልጣን፥ ...በየገበሬው ቤት እየገባ በግዴታ ይስተናገድበት የነበረ ስርአት::

**ተመራ** ግ ወታደር ወይም የመንግስት ጉዳይ የሚያስፈፅም ሰው በየገበሬው ቤት እንዲስተናገድ ተሰማራ (በባላባታዊ ስርአት)::

**መመሪያ** ስ አንድን ስራ ለማካሄድ በቃል የተሰጠ ወይም በወረቀት የሰፈረ ደንብ፥ ትእዛዝ፥ የአሰራር ስልት::

**ተመሪ** ስ 1.የመሪ ተከታይ፥ ታዛዥ፥ ትእዛዝ ፈፃሚ:: 2. መሪው ቀደም ቀደም እያለ የሚናገረውን ዜማ ወይም ቅኔ የሚያዜም መዘምር:: 3. ከቦታ ወይም ከርስት መሪ ቦታ ወይም ርስት የተሰጠው፤ ተደልዳይ:: 4. በየገበሬው ቤት እየገባ በግዴታ ይስተናገድ የነበረ የመንግስት ባለስልጣን ወይም ወታደር::

**አመራ** ግ 1. መጣ ወይም ሄደ:: *ወደ ቤቱ አመራ::* 2. አዝማሚያ፥ አቅጣጫ ያዘ:: *ነገሩ ወዴት እንደሚያመራ አይታወቅም::*

**አመራር** ስ 1. መመሪያ:: *በዚህ ጉዳይ ላይ አመራር ተሰጥቶበታል::* 2. የመንግስት፥ የፖለቲካ ድርጅት፥...የበላይ አካል:: *አመራሩ ያሳለፈው ውሳኔ ተቀባይነት አላገኘም::*

**መራራ** "መረረ" ስር ተመ.

**መራር** ዝ.ከ.

**መራዥ** "መረዘ" ስር ተመ.

**መራጃ** ስ የድንጋይ መፍለጫ ትልቅ መዶሻ::

**መራጊ** "መረገ" ስር ተመ.

**መሬት** ስ 1. ለፀሃይ ባላት ቅርበት ሶስተኛ፥ በመጠን ከፕላኔቶች አምስተኛና ከዘጠኙ አለማት (ፕላኔቶች) አንዷ የሆነች የምንኖርባት አለም፤ ምድር (በተጨማሪ ፕላኔት ስር ተመ.):: 2. አፈር ፥ የብስ የሆነውና ውሃ ያልተኛበት ክፍል:: 3. የቤት ወለል::

**መሬቱ (ማሳው) ለስልሷል** እየተደጋገመ ታርሷል::

**መሬቱ ጦም አደረ** ሳይዘራበት ከረመ::

**መሬት ለቀቀ** 1.ወደላይ ከፍ አለ፥ አየር ላይ ሆነ:: 2. ታበየ፥ ተንቀባረረ::

**መሬት ነው** ቻይ፥ ታጋሽ ነው::

**መሬት አታሚሽም**ለመሞት የመጀመሪያው ሰው አትሆንም::

**መሬት ከዳው** አዙሮት ወይም አንሸራቶት ድንገት ሳያስበው ወደቀ::

**መሬት ያዘ** ተስተካከሎ ተቀመጠ::

**መሬት ይቅለለው** አንዳንድ ሰዎች የሚች ዘመዳቸውን ወይም ወዳጃቸውን ስም በሆነ ምክንያት በሚያነሱበት ጊዜ (የመቃብር ጭንቅ ይቅለልለት፥ መሬት አትክበደው ለማለት) የሚናገሩት የበጎ ምኞት አባባል::

**መሬት ጠበበው**1. በጣም ተደሰተ፥ ፈነደቀ:: 2. በጣም ተጨነቀ፥ አዘነ፥ የሚያደርገው አጣ::

**መሬት ጠብ አይልም** ሳይፈፀም፥ ሳይደርስ አይቀርም (ርግማኑ፥ የተናገረው)::

**ከመሬት ተነስቶ** ያለምንም ምክንያት::

**ከመሬት ደባለቀ** መሬት ላይ ክፉኛ ጣለ፤ አፈረጠ::

**መሬት ቅርቡ** ቅ 1. ድንክ:: 2. ቆጥ ማለት የሚወድ፥ ሰነፍ:: 3. ቶሎ ቶሎ የሚወድቅ::

**የመሬት መንቀጥቀጥ** ስ ድንገተኛና ሃይለኛ የሆነ የመሬት መንቃንቅ፥ መናወጥ::

**የመሬት ምላስ** ስ ሾጠጥ ያለና ወደ ባህር ገባ ብሎ የሚገኝ መሬት፤ ልሳነ ምድር::

**የመሬት ስሪት** የ"ስሪት"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

**መርሃ ሰሚን** ስ የ"ኮምፓስ"ን ፍቺ ተመ.

**መርሃ እውር** ስ የጨረቃ፥ የፀሃይ፥ የቀን፥ የወር፥ የአመት፥ የዘመን አቆጣጠር ያለበት መፅሃፍ::

**መርሃ ግብር** ስ በቅደም ተከተል የተዘጋጀ እቅድ፤ ፕሮግራም::

**መርህ** ስ መመሪያ::

**መርማሪ** "መረመረ" ስር ተመ.

**መርቄ** "ሜርቆ"ን ተመ.

**መርበብተ ሰለሞን** ስ አጋንንትን አጥምዶ ለመያዝና በቁጥጥር ስር ለማድረግ ያስችላል ተብሎ የሚነገርለት አስማት ወይም ድግምት::

**መር አለ** "እመር" ስር "እመር አለ"ን ተመ.

**መርከብ** ስ በነዳጅ ሃይል የሚንቀሳቀስና በመጠን ከጀልባና ከታንኳ የሚበልጥ፥ ሰውን፥ እቃን፥...በባህር ላይ ለማመላለስ የሚያገለግል የውሃ ላይ መጓጓዣ (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)::

**መርከብ አዛዥ** ስ በመርከብ ላይ የመርከብ ሃላፊ ሆኖ የሚሰራ ሹም::

**መርከበኛ** ስ 1. መርከብ ነጂ:: 2. በመርከብ ላይ የሚሰራ ሰው::

**መርዘኛ** "መረዘ" ስር ተመ.

**መርዝ** ዝ.ከ.

**መርጿ** "*ረጻ" ስር ተመ.

**መርጾፋ (መርጹፋ)** ስ አቡጀዲ የሚመስል ወፈር ያለ ቆርፋጻ ጨርቅ።

**መርገም** "ረገመ" ስር ተመ.

**መርገጥ** "ረገጠ" ስር ተመ.

**መርገጫ** ዝ.ከ.

**መርገፍ** "ረገፈ" ስር ተመ.


**መርግ** "መረገ" ስር ተመ.

**መርጦ** ስ ሸርጥ፥ ግልድም (ሃረር አካባቢ የሚነገር)።

**መርፌ** ስ 1.በአንደኛው ጫፍ በኩል ሹል የሆነ፥ በሌላው ጫፍ በኩል ዶልዶም ያለ ሆኖ የክር ማስገቢያ ቀዳዳ ያለውና ለልብስ መስፊያ የሚያገለግል ቀጭን ብረት፤ የእጅ መርፌ። 2. ስሪንጅ ላይ ተሰክቶ ፈሳሽ የሆነ መድሃኒትን በውስጡ ወደ ህመምተኛው ሰውነት ለማስተላለፍ የሚያስችል ቀጭን ብረት። 3. ተነቃይና ተሰኪ የሆነ፥ በሸክላ ላይ የተቀረፀውን ድምፅ ተቀብሎ የሚያስተላልፍ፥ ጫፉ ሹል የሆነ ኤሌትሮኒክስ የሸክላ ማጫወቻ እቃ።

**መርፌ ነኝ** መድሃኒት በመርፌ እየወሰድኩ ስለሆነ ይህንን አልበላም ወይም አልጠጣም ለማለት የሚነገር አባባል።

**መርፌ ቁልፍ** ስ አንዱ ጫፍ ሹል ሆኖ ሁለተኛው ትይዩ ጫፍ ደግሞ እንደክዳን ወይም እንደ መቆለፊያ ሆኖ እንዲያገለግል የተሰራና ለልብስ ማያያዣነት የሚጠቅም መርፌ።



መርፌ ቁልፍ

**የመርፌ እራት** ስ መርፌው እንዳይጠፋ ወይም ከተቀመጠበት ቦታ በቀላሉ እንዲገኝ በመርፌው ቀዳዳ ላይ የምትንጠለጠል ትንሽ ክር።

**መሮ** ስ ለእንጨት ወይም ለድንጋይ መቦርቦሪያ፥ መሰርሰሪያ ወይም መጥረቢያ የሚያገለግል ጫፉ ሹል ወይም ስል የሆነ ብረት።



መሮ

**መሰለ** ግ 1. በመልክ፥ በመጠን፥ በባህርይ፥... ከሌላ ጋር አንድ ሆነ፤ ተቀራረበ። 2. አበረ፥ ተስማማ። 3.አብሮ ሆነ ወይም አብሮ አደረገ፥ ተቀላቀለ። 4. በምሳሌ ተናገረ።

**ለይምሰል** የውሸት፤ ለይስሙላ።

**ምን የመሰለ** በጣም ቆንጆ፥ በጣም ጥሩ፥ ደስ የሚል፥ የሚያረካ።

**ምን ይመስልሃል?** ምን አስተያየት አለህ?

**እንደሚመስለኝ** እንደገባኝ፤ እንደተሰማኝ።

**እንዲህ አይምሰልህ** አንድ ነገር ከሚገመተው በላይ (ጥሩ ወይም መጥፎ) መሆኑን ለመግለፅ የሚነገር አባባል።

**የመሰለኝን** 1. ያሻኝን፥ የፈለግሁትን። 2. የታየኝን፥ የተሰማኝን፥...።

**የማይመስል ነገር** መደረጉ፥ መፈጸሙ፥ እውነትነቱ የሚያጠራጥር ነገር።

**ይህን የመሰለ** 1. ከዚህ ጋር የሚቀራረብ፥ እንዲህ ያለ። 2. ጥሩ፥ ግሩም፥ መልካም የሆነ።

**መሰል** ቅ 1.የሚመስል። *አረንጓዴ መሰል ቀለም ተቀብቷል።* 2. አምሳያ፥ ተወዳዳሪ። *ለክፋቱ መሰል የለውም።*

**__መሳይ** ቅ 1.__የሚመስል። *ወዋ መሳይ።* 2. የሆነ። *ነገረኛ መሳይ።*

**መስሎ አዳሪ** 1. ከሁሉ የሚስማማ፥ የሚግባባ። 2. ተለማማጭ።

**ምሳሌ** ስ 1. ቀደም ሲል የተነገረን ነገር ለማጠናከርና የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የሚቀርብ ሃሳብ፥ ማብራሪያ፥...። 2. አርአያ። *መሪዎች የጥሩ ስነምግባር ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል።*

**ምሳሌያዊ አነጋገር** ስ ቀደም ሲል የተነገረን ነገር ለማጠናከር፥ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግና ለዛ ለመስጠት ሲፈለግ በንግግር ላይ ተጨማሪ ሆኖ የሚቀርብ አጭር አባባል።

**ምስል** ስ 1. በፎቶግራፍ ተነስቶ ወይም በውሃና በመስታወት ውስጥ ተንፀባርቆ የሚታይ የአንድ ነገር መልክ። 2. በድንጋይ፥ በእንጨት፥ በወርቅ፥...ላይ የተቀረፀ የአንድ ነገር መልክ። 3. የመስቀል ቅርፅ ባለው እንጨት ላይ የሚችን ልብስ በማልበስ በለቅሶ ጊዜ ለማልቀሻነት የሚያገለግል ቅርፅ።

**ምስለ ቢስ** ቅ መልከ ጥፉ።

**ምስል አፍሳሽ** ስ ወርቅ፥ ብር፥... እያቀለጠ የተለያዩ ቅርፃቅርፆችንና ጌጣጌጦችን የሚሰራ።

**ምስያ** ቅ አምሳያ።

**ተመሰለ** ግ የሌላ ነገርን መልክ፥ ገፅታ፥ ባህርይ ያዘ።

**ተምሳሌት** ስ በጥሬው ካለው ትርጉም ውጪ ሌላ ነገርን የሚወክል ቃል ወይም ሃረግ። *ሳንበሳ የጀግና ተምሳሌት ነው/ጨለማ የመከራ ተምሳሌት ነው።*

**ተመሳሰለ** ግ በመልክ፥ በመጠን፥በባህርይ፥... ተቀራረበ፣ አንድ ሆነ።

**ተመሳሳይ** ቅ በመልክ፥ በመጠን፥በባህርይ፥... የተቀራረበ፥ አንድ የሆነ።

**ተማሰለ** ግ ተደበላለቀ፥ ተቀላቀለ፥ ተዋሃደ።

**አመሰለ** ግ በሌላው ላይ ክፉ ተመኘ (ላይተኩስ ጠመንጃ ደገነበት/ ላይመታው ዱላ ቃጣበት)።

**አያምስልና** እውነት አያድርገውና፥ አያድርስና።

**አመሳሰለ** ግ 1. ተመሳሳይ፥ ተቀራራቢ ወይም አንድ አይነት አደረገ። *በፊት ከተሰራው ጋር አመሳሰለህ ሰራልኝ።* 2. አነፃፀረ፥ አወዳደረ። *ኢትዮጵያንና አሜሪካን በኢኮኖሚ ደረጃ ማመሳሰል አይቻልም።*

**አማሰለ** ግ አደበላለቀ፥ አቀላቀለ፥ አዋሃደ።

**ማማሰያ** ስ ወጥ፥ ገንፎ፥...ሲሰራ ለማማሰል የሚያገለግል አጠር ቀጠን ያለ እንጨት።

**አምሳል** ስ የአንድ ነገር ተመሳሳይ፥ አምሳያ፥ ምሳሌ።

**አምሳያ** ቅ በመልክ፥ በቀለም፥...ሌላውን የሚመስል፥ ከሌላው ጋር የሚመሳሰል። *አምሳያ ልጅ ናት።*

**አስመሰለ** ግ 1. ያልሆነና ያልተደረገ ነገርን እንደሆነ፥ እንደተደረገ አድርጎ አቀረበ። 2. ተመሳሳይ፥ ተቀራራቢ፥ አንድ አይነት አደረገ።

**አያስመስልብህና** አያምጣብህ፥ አያድርስብህና (ክፉ ነገር)።

**አስመሳይ** ቅ ያልሆነውንና ያልተደረገውን እንደሆነ፥ እንደተደረገ አድርጎ የሚያቀርብ ውሸታም፣ አታላይ።

**መሰለቂያ "ሰለቀ"** ስር ተመ.

**መሰላል** ስ ከፍ ወዳለ ቦታ (ቤት፥ ዛፍ፥...) ላይ ለመውጣትና ለመውረድ የሚያገለግሉ ደረጃ መሰል መረጋገጫዎች ያሉት ባለሁለት ወይም ባለአራት እግር እንጨት፥ ብረት፥ ገመድ፥...።



መሰላል

**መሰል "መሰለ"** ስር ተመ.

**መሰረተ** ግ አቆመ፥ ተከለ፥ አቋቋመ።

**መሰረት** ስ 1. ከላይኛው የመሬት ክፍል በታች የሚሰራ የቤት፥ የህንፃ፥ የግንብ፥...መነሻ፥ መቆሚያ። 2. ውጥን፥ ጅምር። *ነገሩ የተበላሸው ገና ከመሰረቱ ነው።*

**መሰረት ጣለ** ጀመረ። *ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለኢትዮጵያ የዘመናዊ ስልጣኔን መሰረት የጣሉ መሪ ናቸው።*

**መሰረተ ልማት** ስ ለአንድ አገር ልማት በተቀዳሚነት አስፈላጊ የሆነ እንደመገናኛ፥ የትምህርት፥ የጤና ተቋም ያለ የህብረተሰቡ መገልገያ።

**መሰረተ ቢስ** ቅ ተጨባጭ ማስረጃ ወይም እውነትነት የሌለው። *መሰረተ ቢስ ወሬ።*

**መሰረተ ትምህርት** ስ ለመሃይምናን የሚሰጥ የመጀመሪያው የቀለም ትምህርት።

**የመሰረት ድንጋይ** ስ አንድ ድርጅት፥ ተቋም፥...ሊሰራ በታቀደበት ቦታ ላይ የተጋበዘው የክብር እንግዳ በመጀመሪያ የሚያኖረውና ለዚሁ ጉዳይ ተብሎ የተዘጋጀ የድንጋይ ምልክት።

**መሰረታዊ** ቅ ዋና፥ በጣም አስፈላጊ፣ ከሁሉም የሚቀድም።

**መሰረታዊ ለውጥ** ስ ስር ነቀል ለውጥ።

**መስራች ጉባኤ [ስብሰባ]** ስ አንድን ድርጅት ፥ ማህበር ፥... ለማቋቋም የሚደረግ የመጀመሪያ ስብሰባ።

**ምስረታ** ስ አንድን ድርጅት፥ ማህበር፥... የማቋቋም ተግባር።

**መሰሪ (መሰርይ)** ቅ በጣም ተንኮለኛ፣ ሸረኛ።

**መሰርሰሪያ "ሰረሰረ"** ስር ተመ.

**መሰስ አለ** ግ ቀስ፥ ዝግ ብሎ ሄደ ወይም መጣ።

***መሰቀለ**

**ምስቅልቅል** ቅ ዝብርቅርቅ፥ ውጥንቅጥ፥ የተመሰቃቀለ።

**ምስቅልቅል አለ** ግ ተዘበራረቀ፥ ቅጥ አጣ፥ ተደበላለቀ።

**ተመሰቀለ** ግ ተደበላለቀ፥ ቅጥ አጣ።

**አመሰቃቀለ** ግ አወሳሰበ፥ አደበላለቀ፥ ቅጥ አሳጣ።

**አመሳቀለ** ግ አደባለቀ፥ ቅጥ አሳጣ።

***መሰቃ**

**መስቃ** ስ የጡር፥ የግፍ ንግግር። *ተመችቶኛል ብለህ መስቃ አትናገር።*

**ተመሰቃ** ግ ተመፃደቀ።

**መሰቅሰቂያ "ሰቀሰቀ"** ስር ተመ.

**መሰብሰቢያ "ሰበሰበ"** ስር ተመ.

***መሰነ**

**መሰነች** ግ መከነች፥ አልወልድ አለች(ለቀንድ ከብት)።

**መሲና** ስ የማትወልድ (ላም፥ በግ፥...)።

**መሰናክል** “ሰንከለ” ስር ተመ.

**መሰናዘሪያ** “ሰነዘረ” ስር ተመ.

**መሰናዶ** “*ሰነዳ” ስር ተመ.

**መሰንቆ** “ማሲንቆ”ን ተመ.

**መሰንበቻ** “ሰነበተ” ስር ተመ.

**መሰከረ** ግ ስላየው፥ ስለሰማው፥ ስለሚያውቀው ነገር ወይም ድርጊት እውነተኛውን ሁኔታ በቃል ወይም በፅሁፍ አረጋገጠ፥ አስረዳ።

**ምስክር** ስ 1. አንድ ድርጊት ሲፈፀም በቦታው ተገኝቶ ያየ ወይም የሰማ ሰው፤ እማኝ። 2. ስለአየው፥ ስለሰማው፥ ስለሚያውቀው ነገር ህጋዊ በሆነ ቦታ ቀርቦ በመሃላ ቃሉን የሚሰጥ ሰው፤ እማኝ። 3. እንደ ድጓ፥ ቅዳሴ ያሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሚሰጡ ትምህርቶችን ለማስተማር የሚችሉ መምህራንን አስተምሮ ስለብቁነታቸው ማረጋገጫ (የምስክር ወረቀት) የሚሰጥ የመምህራን መምህር (ለምሳሌ የድጓ ምስክር)።

**ምስክር ቆጠረ** 1. አንድ ድርጊት ሲፈፀም በቦታው የነበሩትን ሰዎች እዩልኝ፥ ልብ በሉ፥...አለ። 2. እማኝ ጠራ፤ ምስክሮቼ እነ እገሌ ናቸው ብሎ ተናገረ (ለሽማግሌ ወይም ለዳኛ)።

**የምስክር ወረቀት** ስ 1. አንድን የሙያ ወይም የትምህርት ዘርፍ ተከታትሎ ሳጠናቀቀ ግለሰብ፥ በሰለጠነበት መስክ ብቁ መሆኑን ለመግለፅ፥ ህጋዊነት ወይም ስልጣን ባለው አካል የሚሰጥ የፅሁፍ ማስረጃ። 2. ለአንድ ነገር እንደ ማስረጃ ወይም ማረጋገጫ የሚያገለግል የፅሁፍ ማስረጃ።

**ተመሰከረ** ግ ተያየ፥ ተነፃፀረ፥ ተገናዘበ።

**አስመሰከረ** ግ 1. ድርጊቱን፥ ማንነቱን፥ ችሎታውን አሳየ ወይም አሳወቀ። 2.(ቤ.ክህ.) በተማርከው ትምህርት የሚፈለገውን ችሎታ አግኝተሃል፥ ልታስተምር ትችላለህ የሚል ፈቃድ አገኘ፤ ማስረጃ ተሰጠው። *ድጓ አስመስክሮአል።*

**መሽክ** ስ 1. የሳርን፥ የቡቃያን ስር የሚበላ ነጭ ትል። 2. (ዘይ.) ሀ. ተንኮለኛ፥ ምስጥ። ለ. ቢበላ የማይጠግብ።

**መሰገ** ግ 1. አጎረ። 2. ሰገሰገ፥ ሰካ። 2. ከግጦሽ በሂላ አንድ ቦታ ላይ በመሰብሰብ እንዲተኙ አደረገ (እንደ በግና ፍየል ያሉ የቤት እንስሳትን)።

**ምሳግ** ስ ከብቶች ሳር ከበሉ በሃላ ተሰብስበው የሚተኙበት ከቤት ውጪ ያለ ቦታ።

***መሰገነ**

**ምስጉን** ቅ 1. የተመሰገነ። 2. ጥሩ መስራቱ የታወቀና የተደነቀለት። *ምስጉን ሰራተኛ።*

**ምስጋና** ስ ጥሩ ለሰራ፥ ውለታ ለዋለ፥... የሚቀርብ ሙገሳ፥ ውደሳ።

**ምስጋና ይግባው** ይሞገስ፥ ይወደስ፥ ይመስገን፤ ምስጋና ይድረሰው፥ መመስገን ይገባዋል።

**ምስጋን ይንሳው** 1.ሁለት የተለያዩ ነገር ግን የሚመሳሰሉበት ባህርይ ያላቸውን ነገሮች በማነፃፀር አንዱ ከሌላው ይበልጣል ለማለት የሚነገር አባባል። *ውይ! በርበሬው ሲያቃጥል! ሚጥሚጣን ምስጋን ይንሳው።* 2. ምስጋና አይገባውም፥ ምስጋና ያሳጣው።

**ምስጋና ይድረሰው** ምስጋና ይግባው፥ ምስጋና ለእሱ ይሁን።

**ምስጋና ቢስ** ቅ 1. የማያመሰግን፥ ውለታ ቢስ። 2. መልካም ስራ ሰርቶ ምስጋና የማይሰጠው፥ የማያገኝ (የመቆርቆር አነጋገር)።

**ምስጋና የለሽ** ቅ 1. የማያመሰግን። 2. ውለታ ውሉ የማይመሰገን፥ ምስጋና የማያገኝ ወይም የማይሰጠው (የመቆርቆር አነጋገር)። *ምስጋና የለሽ መሆኔን ባውቅም ደግ ነገር ከመስራት ወደ ሂዋላ አልልም።*

**ተመሰገነ** ግ ተሞገሰ፥ ተመረቀ፥ ተባረከ።

**ተመስገን** ምስጋና ይድረስህ፤ ምስጋና ለአንተ ይሁን (ለእግዚአብሄር)።

**አመሰገነ** ግ ምስጋና አቀረበ፥ አሞገሰ፥ አወደሰ፤ መረቀ፥ ባረከ።

**መሰጠ** ግ ትኩረት ሳበ፥ ሃሳብ ወሰደ።

**ተመሰጠ** ግ በሃሳብ ርቆ ሄደ፤ ትኩረቱ ተሳበ።

**ተመስጦ** ስ ልዩ የአእምሮ ትኩረት።

***መሰጠረ**

**ምስጢር(ሚስጥር)** ስ 1. ይፋ ያልሆነ ነገር፤ ድብቅ ጉዳይ። 2. በቅኔ ውስጥ ሰምና ወርቁ የያዘው ትርጓሜ፥ ፍሬ ነገር። 3. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ በተለይ ቤተልሄም እየተባለች በምትጠራው ቤት ውስጥ የሚከናወን ተግባር (የስርአተ ቁርባን ዝግጅት)።

**ምስጢር አወጣ** ድብቅ የነበረን ነገር ይፋ አወጣ፥ ገለጠ።

**ምስጢር አየ** (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ድቁና ከተቀበለ በሂላ በቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ በምትገኘውና ቤተልሄም ተብላ በምትጠራው ቤት ውስጥ የሚከናወን ተግባር አየ፥ ተረዳ፥ አወቀ።

**ምስጢር ጠበቀ** ምስጢር የሆነን ነገር ለማንም ሳያሳውቅ፥ ሳይናገር ቀረ፤ ደብቆ ያዘ።

**ምስጢረ ስላሴ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የስላሴን የአንድነትና የሶስትነት ምስጢር የሚያስረዳ ትምህርት።

**ምስጢረ ስጋዌ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስለአምላክ (ክርስቶስ) ሰው የመሆንና ስጋ የመልበስ ምስጢር የሚያስረዳ ትምህርት።

**ምስጢረኛ** ስ የልብን የሚነግሩት ወይም

የሚያዋዩት የቅርብ ወዳጅ፥ ጓደኛ።

**ምስጢር ኪስ** ስ በወንድ ሱሪ ፊት ለፊት በቀኝ በኩል ያለ ትንሽ ኪስ።

**ተመሳጠረ** ግ 1. በድብቅ ወይም በስውር፥ በምስጢር ተነጋገረ፥ ተመካከረ። 2. አንድ ተንኮል ወይም መጥፎ ነገር ለመፈፀም በስውር ተመካከረ፤ አሴረ።

**አመሰጠረ** ግ ስውር ወይም ሽፍን የነበረውን ሃሳብ ገለፀ፤ አብራራ(ቅኔ)።

**መሰጥ** ስ በአህያ ወይም በአጋሰስ ሆድ አካባቢ የሚውልና በጀርባቸው ላይ የተጫነውን በደንብ ለማሰርና ለማጥበቅ እንዲያመች ሆኖ ታጥፎ ወረድ ያለ የመጫኛ መጥለፊያ።

**መሲህ** ስ የተቀባ ንጉስ ወይም ካህን ወይም ነቢይ።

**መሲና** "**መሰነ**" ስር ተመ.

**መሳ** ቅ አቻ፥ እኩል።

**መሳ ለመሳ (መሳ በመሳ)** እኩል በኩል።

**መሳለሚያ** "***ሰለመ**" ስር ተመ.

**መሳል** "**ሳለ**[2]" ስር ተመ.

**መሳሪያ** "**ሰራ**[1]" ስር ተመ.

**መሳቂያ** "**ሳቀ**" ስር ተመ.

**መሳቢያ** "**ሳበ**" ስር ተመ.

**መሳድ** ስ በቁቲት ውስጥ ያለች የሽማ መወጠኛ ቀጭን እንጨት (ስእሉን ሽማኔ ስር ተመ.)።

**መሳፍቻ** "**ወሳፍቻ**"ን ተመ.

**መሳፍንት** ስ (ነ.ቁ.**መስፍን**) በቀድሞ ጊዜ ከንጉሱ ጋር በዝምድና የተሳሰሩና በስልጣን ላይ የነበሩ የገዥው መደብ አባላት።

**መስህብ** ስ የሚማርክ ወይም የሚስብ ውበት ያለው ነገር (ቅርሳቅርስ፥ መልክአምድር፥...)።

**መስመር** "***ሰመረ**" ስር ተመ.

**መስሪያ ቤት** "**ሰራ**[1]" ስር ተመ.

**መስቀለኛ** "**ሰቀለ**" ስር ተመ.

**መስቀል** ዝ.ከ.

**መስቀያ** ዝ.ከ.

**መስቃ** "***መሰቃ**" ስር ተመ.

**መስቆር** "**ሰቆረ**" ስር ተመ.

**መስቀርት** ዝ.ከ.

**መስበቂያ** "**ሰበቀ**" ስር ተመ.

**መስተ-** በአንዳንድ ቃላት ላይ ባእድ መነሻ በመሆን እየተቀጠለ እርስ በርስ የ—የሚል ፍቺ። የሚሰጥ ምእላድ፡*፡መስተዋድድ፥መስተፋቅር፥...።*

**መስተሃድርት (መስታድርት)** ስ የጠፋ ከብትን አውሬ እንዳይበላው እየተባለ የሚደገም አስማት ወይም ድግምት።

**መስተባርር** "**በረረ**" ስር ተመ.

**መስተንግዶ** "***ነገደ**" ስር ተመ.

**መስተአምር** በቃላት መጨረሻ እየገባ ነገሩ (ቃሉ) ቀደም ሲል የተጠቀሰ መሆኑን የሚያሳይ ምእላድ መጠሪያ። *መጽሃፉ (መፅሃፍ-ኡ)።* መፅሃፍ የተባለው ቃል ቀደም ሲል የተጠቀሰ መሆኑን የሚያመለክተው መስተአምራዊ ምእላዱ "ኡ" ነው።

**መስተዋት(መስታወት)** ስ 1. መልክን ወይም ከፊት ለፊቱ ያለውን ምስል መልሶ የሚያሳይና ልሙጥ ሆኖ ውሃ መልክ ያለው እቃ። 2. ብርሃን ማስተላለፍ የሚችል፥ ብዙውን ጊዜ በመስኮትና በር ላይ የሚገጠም፥ ጠጣር ሆኖ ግን በቀላሉ ሊሰበር የሚችል የህንፃ መሳሪያ እቃ።

**መስተዋት መሰለ** በጣም ፀዳ፥ አማረ።

**መስተዋድድ** በስምና ስም አከል በሆኑ ቃላት መነሻ ወይም በመነሻና መድረሻ ላይ እየገባ የነገሮችን ዝምድና የሚያመለክት የንግግር ክፍል። (ምሳሌ ወደ፥ ከ...ጋር፥ በ...ላይ)።

**መስተጻድር** "**አደረ**" ስር ተመ.

**መስተፃምር** በግስ ላይ. እየተጨመረ ግሱ እንዳያስር የሚያግድ እንዲሁም ቃላትን፥ ሃረጎችን፥ አረፍተ ነገሮችን የሚያያይዝ የንግግር ክፍል። *አበበና ከበደ ከተዋወቁ ጀምሮ እንደተፋቀሩ ኖሩ።* (መስተፃምሮቹ ከ፥ ና፥ እንደ፥ ናቸው)።

**መስተፋቅር** ስ ወንድና ሴትን ወይም ሰዎችን እርስበርስ ያፋቅራል የሚባል አስማት ወይም መድሃኒት።

**መስቲካ (ማስቲካ)** ስ ከሙጫና ከሌሎች ቅመሞች የሚሰራ መጣብቅነት ያለው የሚታኘክ ጣፋጭ።

**መስታድርት** "**መስተሃድርት**"ን ተመ.

**መስኖ** ስ 1. ከወንዝ፥ ከምንጭ፥... ተጠልፎ ሰው ሰራሽ የሆነ መንገድ ወይም ቦይ ተበጅቶለት ለእርሻ ስራ የሚውል ውሃ። 2. ከወንዝ፥ ከምንጭ፥... ውሃን በቦይ ወይም በሌላ ዘዴ በመጥለፍ መሬትን ውሃ እያጠጡ የሚካሄድ የግብርና ስራ ወይም ዘዴ። 3. በመስኖ የሚለማ ወይም የለማ መሬት።

**የመስኖ መሬት/እርሻ** ውሃገብ የሆነ ወይም የመስኖ ውሃ ያለው መሬት፤ እርሻ።

**የመስኖ ውሃ** (ዘይ.) የራሱ የሆነ ጠንካራ አቋም የሌለው፤ በሌላ ሰው ሃሳብ የሚመራ (ሰው)።

**መስእ** ስ በሰሜንና በምስራቅ መካከል ያለ የአለም ማእዘን አቅጣጫ (በተጨማሪ ማእዘን ስር ተመ.)።

**መስከረም** ስ የአመቱ የመጀመሪያው ወር ስም።
**መስከረም ጠባ** የመስከረም ወር ገባ፥ ተጀመረ።
**መስክ** ስ 1. በለምለም ሳር የተሸፈነ ሰፊ ሜዳ፥ መሬት። 2. የመስክ ስራ።
**መስክ ወጣ** የመስክ ስራን ለማከናወን ሄደ።
**የመስክ ስራ** ስ የተለያዩ ጥናቶችንና ምርምሮችን የሚያካሂድ ሰው ወይም የቢሮ ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ርቆ በመሄድ የሚያከናውነው ጥናት፥ ስራ።
**መስኮት** ስ በቤት ግድግዳ ወይም በተሽከርካሪዎች ጎን ላይ ለአየርና ለብርሃን መግቢያ እንዲሆን የሚሰራና ብዙውን ጊዜ መዝጊያ ያለው ክፍት ቦታ (ስእሉን ቤት ስር ተመ.)።
**መስዋእት** "ሰዋ" ስር ተመ.
**መስጊድ** ስ የሙስሊሞች ቤተ ፀሎት።
**መስፈሪያ** "ሰፈረ[1]" ስር ተመ.
**መስፈርት** ዝ.ከ.
**መስፍ** ስ እንደማረሻ፥ ቢላዋ፥...ያሉ የተለያዩ መሳሪያዎችን የሚሰሩ ባለሙያዎች ተፈላጊውን የብረት ቁራጭ ካጋሉ በሂላ በላዩ ላይ አጋድመው የሚቀጠቅጡበትና ልዩ ልዩ ቅርፅ የሚያወጡበት ጠፍጠፍ ያለ ትልቅ ብረት።
**መስፍን** "መሳፍንት"ን ተመ.
**መሰብ** ስ ከአክርማና ከስንደዶ የተሰፋ ለእንጀራ ማስቀመጫ ወይም ለመብያ የሚሆን የቤት እቃ (ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።
**መሰበ ወርቅ** ስ ልዩ ልዩ ቀለማት ባላቸው አለላዎች ተጊጦ የተሰፋና ረዘም ያለ እግር ያለው መሰብ (ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።
**መሸ** ግ ጨለመ፥ ማታ ሆነ።
**መሸ በከንቱ** ፍሬ ያለው ነገር ሳይሰራ፥ በከንቱ ሲያውደለድል ወይም በግዴለሽነት ጊዜውን የሚያሳልፍ ሰው።
**መሸ አዳሪ** ስ ቋሚ መኖሪያ የሌለውና በደረሰበት ቦታ የሚያድር ሰው።
**ምሽት** ስ ከፀሃይ ጥልቀት በሂላ ጨለማ እስከሚሆን ያለው ጊዜ።
**አመሸ** ግ እስከ ምሽት ወይም እስከ ማታ ወይም እስከ ሌሊት ቆየ።
**ማምሻ** ስ 1. የመኻታ ሰአት እስኪደርስ ለማንደድ የሚለቀም የማገዶ እንጨት (ብዙውን ጊዜ በገጠር አካባቢ)። 2. ምሽት። 3. መቆያ፥ የምሽቱን ጊዜ ማሳለፊያ።
**ማምሻውን** ወደ ማታ ገደማ። *ማምሻውን ወደ ከተማ ብቅ ብሎ ነበር።*
**አመሻሽ** ስ ምሽት።
**አስመሸ** ግ እስከምሽት ወይም እስከ ማታ ወይም እስከ ሌሊት አቆየ።
**መሸለቀ** "ሞሸለቀ"ን ተመ.
**መሸቢያ** "ሸበበ" ስር ተመ.
**መሸተ** ግ ለገበያ የሚሆንና የሚሸጥ ጠላ፥ ጠጅ ወይም አረቄ፥... ጠመቀ፥ አዘጋጀ።
**መሸታ** ስ 1. ለሽያጭ የተዘጋጀ ጠላ ወይም ወይም አረቄ። 2. ቀሉ ለገበያ እንዲደርስ ተብሉ ያለጥንቃቄ የተሰራ መናኛ እቃ፥ ልብስ፥...።
**መሸታ ቤት** ስ እንደ ጠላ ፥ የአገር አረቄ፥ ጠጅ ያሉ መጠጦች የሚሸጡበት ቤት።
**መሸተኛ** ስ 1. ጠላ ወይም ጠጅ ወይም የአገር አረቄ፥... እያዘጋጀች የምትሸጥ ሴት። 2. መሸታ ቤት አዘውትሮ በመሄድ የሚጠጣ (ሰው)።
**መሸንገያ** "ሸነገለ" ስር ተመ.
**መሸኛ** "ሸኘ" ስር ተመ.
**መሸከ** ግ 1. ደቀቀ፥ ነኮተ። 2. ተጥመለመለ፥ ተልወሰወሰ።
**እምሽክ አለ** ግ ስብርብር፥ ድቅቅ አለ።
**አመሸከ** ግ 1. ደቋቆሰ፥ አነኳኮተ። 2. ጥርግ፥ ሙጥጥ ወይም እንክት አድርጎ በላ።
**መሸገ** ግ 1. ከጠላት ጦር ለመከላከል ጉድጓድ በመማስ፥ ድንጋይ በመካብ፥...መሸሸጊያ አበጀ፣ ምሽግ ሰራ። 2. ተደበቀ፥ ተሸሸገ። 3. (ዘይ.) በአንድ ቦታ ወይም አካባቢ ተወስኖ ተቀመጠ ወይም አዘውትሮ ተገኘ።
**ምሽግ** ስ 1. ከጠላት ጦር ለመከላከል ጉድጓድ በመማስ፥ ድንጋይ በመካብ፥... የሚሰራ መከለያ ቦታ፥ ተገን። 2. (ዘይ.) ሁልጊዜ የማይታጡበት ቦታ፥ መገኛ፥ መዋያ። *የእገሌ ምሽግ ያ ጠጅ ቤት ነው።*
**ምሽግ ሰበረ** ምሽግን ጥሶ ገባ፥ አለፈ።
**ተመሸገ** ግ ተከለለ፥ ተደበቀ፥ ምሽግ ውስጥ ሆነ።
**መሸጋገሪያ** "*ሻገረ" ስር ተመ.
**መሸጎሪያ** "ሸጎረ" ስር ተመ.
**መሸፈኛ** "ሸፈነ" ስር ተመ.
**መሹለኪያ** "ሾለከ" ስር ተመ.
**መሹለክለኪያ** ዝ.ከ.
**መሽረብ (መትረብ)** ስ 1. የውሃ ቱቦ። 2. አሸንዳ።
**መሽቀቅ** ስ በሱሪ፥ በቀሚስ፥...ወገብ ዙሪያ የሚገባ ማሰሪያ፣ ጥብጣብ።
**መሿለኪያ** "ሾለከ" ስር ተመ.

**መቀመቅ (መቅ)** ስ በጣም ጥልቅ የሆነ ጉድጓድ፤ አዘቅት::

**መቀመቅ ወረደ** ሲኦል ገባ::

**መቀመጫ** "*ቀመጠ" ስር ተመ.

**መቀራቅር** "ቀረቀረ" ስር ተመ.

**መቀራቅርት**"ቀረቀረ" ስር "መቀራቅር"ን ተመ.

**መቀርሰሚያ** ስ የአረቄ መጠጫ፤ መለኪያ::


**መቀርቀሪያ** "ቀረቀረ" ስር ተመ.

**መቀርቀቢያ** "ቀረቀበ" ስር ተመ.

**መቀርጠፊያ** "ቀረጠፈ" ስር ተመ.

**መቀሰ** ግ በመቀስ ቆረጠ ወይም ቀደደ::

**መቀስ** ስ እጀታ ያላቸው ሁለት ትይዩ የሆኑ ስለታም ብረቶችን በማገጣጠም የተሰራ መቁረጫ፥ መቅደጃ፥ መከርከሚያ፤ መቁረጪት::



መቀስ

**መቀስ ምት** ስ ወደ ላይ በመዝለልና እግርን እንደ መቀስ በማሰባጠር በአንደኛው እግር የሚመቱ እስመስሉ በሁለተኛው እግር የሚመታ የእግር ኳስ አመታት::

**መቀስ ቅድ** ስ አንገትጌው እንደባላ ከስር ጠበብ ከላይ ሰፋ ብሎ የወጣ የልብስ ቅድ::

**መቀቀያ** "ቀቀለ" ስር ተመ.

**መቀነስ** "ቀነሰ" ስር ተመ.

**መቀነሻ** ዝ.ከ.

**መቅነት** "*ቀነተ" ስር ተመ.

**መቀነቻ** ዝ.ከ.

**መቀናጆ** "*ቀነጀ" ስር ተመ.

**መቀንደቢያ** "ቀነደበ" ስር ተመ.

**መቀንጠቢያ** "ቀነጠበ" ስር ተመ.

***መቀኘ**

**ምቀኛ** ስ ሌላው ሰው ጥሩ ነገር እንዲያገኝ የማይፈልግ፥ የማይወድ ወይም እንዳያገኝ የሚጥር ሰው::

**ተመቀኘ** ግ 1. ለሌላው ጥሩ ነገር እንዳይደረግለት ተመኘ አደረገ፥ተከላከለ:: 2. ሌላ ሰው ባለው ወይም ባገኘው ጥሩ ነገር ያላግባብ ቀና::

**መቀየሪያ** "ቀየረ" ስር ተመ.

**መቀየጃ** "ቀየደ" ስር ተመ.

**መቀንጠቢያ** "ቀጠበ" ስር ተመ.

**መቀጣጫ** "ቀጣ" ስር ተመ.

**መቀጫ** ዝ.ከ.

**መቀጮ** "ቀጣ" ስር "መቀጫ" ን ተመ.

**መቀፍቀፊያ** "ቀፈቀፈ" ስር ተመ.

**መቁሊያ** "ቆላ" ስር ተመ.

**መቁረርት** "ቆረረ[1]" ስር ተመ.

**መቁረጪት** "ቆረጠ" ስር ተመ.

**መቁረጫ** ዝ.ከ.

**መቁነን** "ቆነነ" ስር ተመ.

**መቁያ** "ቆላ" ስር "መቁሊያ"ን ተመ.

**መቁጠሪያ** "ቆጠረ" ስር ተመ.

**መቂናጥ** ስ 1.በሶስት በኩል በክር የተያያዘና በሽመና ስራ ጊዜ መኑ ከፍ ዝቅ እንዲል የሚያደርግ እንጨት:: 2. ሞላላ ሆኖ እንደዘንግ የተሰራና በቱቦ መሰል ብረት ውስጥ ገብቶ በአንዳች አይነት ግፊት ወደላይና ወደታች እየተንቃነቀ እንቅስቃሴን የሚሰጥ የሞተር አካል::

**መቃ** ስ ቅጠሉ ሻካራ፥ ቀጫጭንና ረዣዥም፤ ግንዱ አንጓ ያለውና ውስጠ ክፍት የሆነ የእፅዋት አይነት፤ ሸንበቆ::

**መቃ ልቅም** ስ በመቃ ስንጥር እየተለቀመ የሚሰራ የሽማ ጥበብ አይነት::

**መቃ መስዬ** ስ እንደመቃ ያለ ግን ከመቃ የሚቀጥንና የሚጠነክር የእፅዋት አይነት::

**መቃ ብእር** ስ ከመቃ ተቀርፆ የተዘጋጀና ቀለም እየተጠቀሰበት የቁም ፅህፈት ለመፃፊያ የሚያገለግል ብእር::

**መቃረቢያ** "ቀረበ" ስር ተመ.

**መቃብር** "ቀበረ" ስር ተመ.

**መቃን** ስ በቤት በር ወይም መስኮት ግራና ቀኝ ጎበኑን ተሸክሞ የቆመ እንጨት (ቤት ስር የበርን ስእል ተመ.)::

**መቃኛ** ስ 1. አንድ ቤተክርስቲያን ተሰርቶ እስከሚያልቅ ድረስ ታቦቱ የሚቆይበት ጊዜያዊ ቤት:: 2. አንድ ትልቅ ቤት ተሰርቶ እስከሚያልቅ ድረስ አጠገቡ የሚሰራና በጊዜያዊነት የሚያገለግል ትንሽ ቤት::

**መቃወሚያ** "*ቀወመ" ስር ተመ.

**መቃድ** ስ 1. ጫፉ ወደ ደንደሱ በኩል ቆለፍ ያለ የብራና፥ የቁርበት መፋቂያ ቢላዋ:: 2. የመነኩሴ መታጠቂያ፤ ሰቅ::



መቃድ 1ኛ ፍቺ

**መቃጠሪያ** "*ቀጠረ[2]" ስር ተመ.
**መቃጥን** ስ የአሳ ማጥመጃ መንጠቆ::
**መቄ [ወፍ]** ስ በብዛት ሆኖ የሚበር ብዙውን ጊዜ በመቃ ላይ ጎጆ ሰርቶ የሚኖር ቢጫ ወፍ::
**መቅ** "መቀመቅ"ን ተመ.
**መቅለምት** "ወቅለምት"ን ተመ.
**መቅመቆ** ስ ሰፋፊና ለስላሳ ቅጠል ያለው፥ ስሩ ቢጫ የሆነና ቅቤ ሲነጠር ቀለሙን ቢጫ እንዲያደርገው የሚጨመር አነስተኛ የእፅዋት አይነት::
**መቅረዝ** ስ ሻማ፥ ጧፍ፥...በላዩ ላይ ተሰክቶ ለመያዝ የሚያገለግል ከሸክላ፥ ከብረት፥ ከነሃስ፥...የሚሰራ የማብሪያ እቃ፤ ቀንዲል::



መቅረዝ

**መቅረጫ** "ቀረፀ" ስር ተመ.
**መቅሰፍታም** "ቀሰፈ" ስር ተመ.
**መቅሰፍት** ዝ.ክ.
**መቅኒ (መቅን)** ስ እንደቅልጥም ባሉ ክፍት አጥንቶች ውስጥ የሚገኝ የአጥንት ቅባት::
**መቅኖ** ስ እርባና፥ በረከት::
**መቅኖ ቢስ** እርባና፥ በረከት የሌለው::
**መቅኖ የለውም** አይበረክትም::
**መቅዘፊያ** "ቀዘፈ" ስር ተመ.
**መቅደስ** "ቀደሰ" ስር ተመ.
**መቅድም** "ቀደመ" ስር ተመ.
**መቅጃ** "ቀዳ" ስር ተመ.
**መቅጫ** "ቀጣ" ስር ተመ.
**መቆለፊያ** "ቆለፈ" ስር ተመ.
**መቆሚያ** "ቆመ" ስር ተመ.
**መቆርቆሪት** "ቆረቆረ" ስር ተመ.
**መቆስቆሻ** "ቆሰቆሰ" ስር ተመ.
**መቆናቁን** "ቆነቆነ[3]" ስር ተመ.
**መቆናጠጫ** "ቆነጠጠ" ስር ተመ.
**መቆንጠጫ** ዝ.ክ.
**መቆያ** "ቆየ" ስር ተመ.
**መቆጣጠሪያ** "ቆጠረ" ስር ተመ.
**መቆፈሪያ** "ቆፈረ" ስር ተመ.

**መቋሚያ** "ቆመ" ስር ተመ.
**መቋረፊያ** ስ ካህናት የሚለብሱት እጀ ሰፊና ደረተ ክፍት ቀሚስ::
**መቋቋሚያ** "ቆመ" ስር ተመ.
**መቋደሻ** "*ቆደሰ" ስር ተመ.
**መቋጠሪያ** "ቋጠረ" ስር ተመ.
**መበለት** "እመበለት"ን ተመ.
**መበለቻ** "በለተ" ስር ተመ.
**መበያ** "በላ" ስር "ማባያ"ን ተመ.
**መባ** "መብአ"ን ተመ.
**መባቻ** "ባተ" ስር ተመ.
**መብል** "በላ" ስር ተመ.
**መብረቅ** "በረቀ" ስር ተመ.
**መብሩቅ** ስ በጥራቱ ከአቡጀዲና ከመርዱፋ በጣም የላቀ ዘመናዊ ነጭ ጨርቅ::
**መብራት** "በራ[1]" ስር ተመ.
**መብሻ** "በሳ" ስር ተመ.
**መብት** ስ 1. አንድ ሰው ወይም አካል በአንድ ነገር ወይም ጉዳይ ላይ የሚፈልገውን ለማድረግም ሆነ ላለማድረግ የሚያስችለው ስልጣን::2. አንድ ሰው አስፈላጊ ሆኖ ሲያየው ሊያገኘው የሚገባ ነገር፥ አገልግሎት፥ ጥቅም፥...::
**መብቱ ተገፈፈ** በሰብአዊነት ወይም በህግ ያገኘው መብት ሳይከበርለት ቀረ::
**መብቱን አስከበረ** መብቱን አስጠበቀ::
**መብቱን አስጠበቀ** በሰብአዊነቱ ወይም በህግ ያገኘው መብት ህጋዊ በሆነ ወይም በሌላ መንገድ ተጠቅሞ፥ በሌላ ሰው ወይም አካል እንዳይደፈር ወይም እንዳይነጠቅ አደረገ::
**መብትና ግዴታ** ስ አንድ ሰው ወይም አካል ያለው መብትና ከእርሱ የሚጠበቅ ግዴታ::
**የመብት ጥያቄ** ስ በሰብአዊነት ወይም በህግ የተገኘን ወይም ሊገኝ የሚገባን መብት አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ::
**መብአ(መባ)** ስ እንደ ጧፍ፥ እጣን፥ ዘቢብ፥...ያለ ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ ስጦታ::
**መተለገ** ግ 1. ቆነጠጠ:: 2. ራበ፥ ሞረሞረ:: 3. ነጠቀ፥ ሞሸለቀ::
**መተሳለፊያ** "አለፈ" ስር ተመ.
**መተማመኛ** "አመነ" ስር ተመ.
**መተረ[1]** ግ መጥኖ ቆረጠ፥ ከተፈ( ስጋን)::
**መተሮ (እምታሮ)** ስ የተከተፈ ስጋ::
**መተረ[2]** ግ ርዝመትን ለካ::
**ሜትር** ስ የርዝመት መለኪያ (1 ሜትር 100 ሴንቲ ሜትር ይሆናል)::

**ሜትር ኩብ** ስ ርዝመቱ፥ ጎኑና ጥልቀቱ አንድ አንድ ሜትር የሆነ ማንኛውም ነገር።

**ሜትር ካሬ (ካሬ ሜትር)** ስ የስፋት መለኪያ (ርዝመቱ 1 ሜትር፥ ጎኑም 1 ሜትር የሆነ የስፋት መጠን፤መረባ ሜትር።

**መተረቻ "ተረተ"** ስር ተመ.

**መተሬ** ስ ፍሬው የኮሶ መድሃኒት ነው ተብሎ የሚበላ እንደ ሃረግ ያለ የእፅዋት አይነት።።

**መተርኮሻ "ተረኮሰ"** ስር ተመ.

**መተሮ "መተረ[1]"** ስር ተመ.

**መተተ** ግ መተት አደረገ ወይም አስደረገ።

**መተት** ስ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም መተት አድራጊው የሚፈልገው ነገር እንዲፈፀምለት በማለት በተለያዩ ነገሮች ማለትም እንደ ልብስ፥ ምግብ፥ የቤት ቁሳቁሶች በመሳሰሉት ላይ የሚደረግ ድግምት።

**መተተኛ** ስ በሰው ላይ መተት የሚያደርግ ወይም የሚያስደርግ ሰው። 2. (ዘይ.) ጉዳዩን ለማስፈፀም ብዙ ጊዜ የሚሳካለት፤ ከፉም ሰው ገር የሚሆንለት።

**መተከዣ "ተከዘ"** ስር ተመ.

**መተኪያ "ተካ"** ስር ተመ.

**መተኮሻ "ተኮሰ"**ስር ተመ.

**መተያያ "አየ"** ስር **"መታያ"** ን ተመ.

**መተዳደሪያ "አደረ"** ስር ተመ.

**መታ[1]** ግ 1. ደበደበ፥ ገረፈ፥ ገጨ። 2. በጥይት አቆሰለ ወይም ገደለ። 3. ለጋ፥ ጠለዘ (ኳስን)። 4. በጠበጠ፥ ደባለቀ፥ አዋሃደ (ተልባን፥ እንቁላልን፥...)። 5. ደረደረ፥ ከረከረ፥ ተጫወተ (በገናን፥ ክራርን፥ ማሲንቆን፥...)።

**መታ ያለ** አጠርና ወፈር ያለ።

**መምቻ** ስ በድር መሃከል የሚያልፈው ማግ እንዲጠጋጋ ወይም ልስቅ እንዲል የሚመታበት የሸማኔ እቃ።

**መምች** ስ 1. እንደ ብይ፥ አዝራር፥ ቆርኪ ላለ የቁማር ጨዋታ ለመምቻነት ተመርጦ የሚያገለግል ብይ፥ አዝራር፥...። 2. እንደ "ሰኞ ማክሰኞ" ባለ የልጆች ጨዋታ ላይ እየተወረወረ ለመጫወቻ የሚያገለግል የሸክላ ስባሪ ወይም ትንሽ ጠፍጣፋ ድንጋይ።

**ምት** ስ 1. መቶ አመታት። 2. በግጥምና በግጥም መሰል ፅሁፎች ላይ የሚታይ የቀለም ወይም የፊደል አመጣጠን።

**ምች** ስ ቅባት ያለው፥ የሚሸት ምግብ፥... ነካክቶ ወይም ላብ ካላበ በሂላ ለፀሃይ በመጋለጥ ምክንያት ይመጣል የሚባል የበሽታ አይነት።

**ምች መታው** የምች በሽታ ያዘው።

**[የ] ምች መድሃኒት** ስ የምችን ህመም ያድናል ተብሎ ከልዩ ልዩ ቅጠላ ቅጠሎች የሚዘጋጅ መድሃኒት።

**ተመታ** ግ ተሸነፈ፥ ተደመሰሰ (ለምሳሌ በጦርነት)።

**ተማታ** ግ 1. መታ፥ ደበደበ። 2. ተምታታ።

**ተምታታ** ግ 1. ተዘበራረቀ፥ ተደበላለቀ። 2. ተሳከረ፥ ተሳሳተ፥ ተወነባበደ።

**አማታ** ግ 1. አጭበረበረ፥ አታለለ። 2. አዘበራረቀ፥ አደበላለቀ። 3. ምች ተጠናወተ፥ አመመ። *ተልባ በልተህ ሳትታጠብ ለትውጣ ያማታሃል።*

**አምታታ** ግ 1. አጭበረበረ፥ አታለለ። 2. አዘበራረቀ፥ አደበላለቀ።

**አምታች** ቅ አጭበርባሪ፥ አታላይ።

**መታ[2]** ግ ሰረረ (አህያ፥ ፈረስ፥...)።

**መታረሪያ** ስ ጥጥ በሚነደፍበት ጊዜ ደጋኑን ደግፎ ለመያዝ የሚያገለግል ቀጭን እንወት (ስእሉን ደጋን ስር ተመ.)።

**መታሰቢያ "አሰበ"** ስር ተመ.

**መታቀፊያ "አቀፈ"** ስር ተመ.

**መታወቂያ "አወቀ"** ስር ተመ.

**መታያ "አየ"**ስር ተመ.

**መታጠቂያ "ታጠቀ"**ስር ተመ.

**መታጠቢያ "አጠበ"** ስር ተመ.

**መት** ስ መደዳ፥ ረድፍ።

**መትረብ "መሽረብ"**ን ተመ.

**መትረየስ** ስ በተከታታይ ብዙ ጥይቶችን በአንድ ጊዜ ሊተኩሱ ከሚችሉ የጦር መሳሪያዎች አይነት አንዱ።

**መቶ** ስ 1. በዘጠና ዘጠኝና በመቶ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤በአሃዝ ሲፃፍ 100፥፻ ነው። ቅ 2. ብዛቱ አስር አስሮችን የሚያህል። *መቶ ሰዎች።*

**መቶ በመቶ** ሙሉ በሙሉ።

**[የ] መቶ አለቃ** ስ ከሻንበል በታች የሚገኝ ወታደራዊ ማእረግ።

***መቸ**

**ምቹ** ቅ 1. የሚደላ፥ ምቾት ያለው። 2. ተስማሚ የሆነ፤ የሰጠ። *ላካባቢው ትምህርት ቤት ለመስራት ምቹ ነው።*

**ምቾት** ስ ድሎት።

**ተመቸ** ግ 1. ደላ፥ ተስማማ። 2. ተሳካ፥ ሆነ። *ከተመቸኝ እመጣለሁ።*

**ተመቻቸ** ግ 1. ተደላደለ፥ ተስተካከለ። 2. ተዘጋጀ፥ ተሰናዳ።

**አመቸ** ግ ምቹ፥ ተስማሚ ሆነ።

**አመቺ** ቅ ምቹ የሆነ፥ ተስማሚ።

**አመቻቸ** ግ 1. አደላደለ፥ አስተካከለ። 2. አዘጋጀ፥ አሰናዳ።

**መቼ (መች)** ተው.ግ. አንድ ጉዳይ የተከናወነበትን ወይም የሚከናወንበትን ጊዜ ለመጠየቅ የሚያገለግል የጥያቄ ቃል። *መቼ መጣህ?*

**መቼም መች** ምንጊዜም ቢሆን፥ በየትኛውም ጊዜ ቢሆን፥...። *መቼም መች እንደዚህ ሆኖ አያውቅም።*

**መቼም(መቼውንም)** ምንምጊዜ፥ አንድም ቀን። *መቼም እንደዚህ ዓይነት ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም።*

**ከመቼው** ከምንጊዜው (ፍጥነትን ለማድነቅ የሚነገር)። *ከመቼው ሄደህ መጣህ ?*

**ከመቼውም ጊዜ ይልቅ/ይበልጥ/ያነሰ** ከምንጊዜውም፥ ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ ወይም ይበልጥ ወይም ያነሰ። *ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አየሩ ተስማምቶኛል።*

**መነመነ** ግ 1. ቀጠነ፥ ከሰመነ፥ ከሳ። 2. በጣም ትንሽ ሆነ፥ ጠበበ። *ተስፋው መነመነ።*

**መንማና** ቅ ከስማና።

**ተመናመነ** ግ ቀስ በቀስ እያለቀ ሄደ (ገንዘብ፥ እህል፥...)።

**መነሳንስ** "ነሰነሰ" ስር ተመ.

**መነሸ** ግ 1. በታተነ። *የተነጠፈውን አልጋ መነሸው።* 2. በቀንዱ መሬት እየጫረና እየቆፈረ አፈሩን ወደላይ ወረወረ (ውጊያ መግጠም ያማረውና ያሰኘው በሬ)።

**መንሽ** ስ በመወቃት ላይ ያለን እህል ለመበርበሪያ፥ለመበተኛ፥ለማዝሪያ፥... የሚያገለግል ከእንጨት የተሰራና ብዙውን ጊዜ ሶስት ጣት ያለው የአውድማ መሳሪያ።



መንሽ

**ተመነሸ** ግ አውድማ ላይ ያለ እህል በመንሽ ተበረበረ፥ ተበተነ።

**አመነሸ** ግ አውድማ ላይ እየተበራየ ያለን እህል በመንሽ ወደ ላይ በመወርወር በነፋስ አማካይነት ምርቱ ከገለባው እንዲለይ አደረገ።

***መነሸነሸ**

**ምንሽንሽ** ቅ ያጌጠ፥ ሽሙንሙን፥ የተዋበ።

**ተምነሸነሸ** ግ 1. ተሽሞነሞነ፥ አጌጠ። 2. (ገንዘብ ወይም ምግብ፥...) እንደልቡ በብዛት፥ አገኘ ወይም እንደፈለገው በብዛት ተጠቀመበት።

**አምነሸነሸ** ግ 1. አስጌጠ፥ አሽሞነሞነ። 2. አጠገበ፥ በብዛት ሰጠ ወይም ጋበዘ፥... (ምግብን፥ ገንዘብን፥...)።

**መነሻ** "*ነሳ" ስር ተመ.

**መነሾ** ዝ.ከ.

***መነቀ**

**ምንቂያም** ቅ (ስድብ) 1. ምንቅ ምንቅ የሚል። 2. ሲሰኛ።

**ምንቅ ምንቅ አለ** ግ ሲሄድ ወይም ሲራመድ ሰውነቱ ውዝ ውዝ፥ ውንጥ ውንጥ አለ።

**መነቀለ** ግ ከስሩ ነቀለ፥ መነገለ፤ መነቀረ።

**መነቀረ** ግ 1. መነገለ፥ መነቀለ። 2. በተነ፥ አፈረሰ፥ አቀማመጡን አበላሸ፤ መነጨረ።

**መንቃራ** ቅ (ስድብ) 1. ሰውነቱን እያቅበጠበጠና እያወዛወዘ የሚሄድ፥ ርጋታ የሌለው፤ ሲሄድ ወዲያና ወዲህ የሚረግጥ። 2. በሆነ ባልሆነው የቁጣ ስሜት የሚያሳይ፥ ቀልቃላ የሆነ፥ ርጋታ የሌለው።

**ምንቅርቅሩ ወጣ** በስርአት ተቀምጦ የነበረው ነገር ተበታተነ፥ ተበላሸ፥...።

**ምንቅርቅራቸው ወጣ** በከፍተኛ ደረጃ ተጣልተው ወይም ተናቁረው ተለያዩ።

**ተመናቀረ** ግ 1.ተጣላ፥ ተናቆረ። 2. በጥል ተለያየ። 3. ወዲያና ወዲህ ረገጠ፥ ተበራገደ። 4. ርጋታ በሌለው ሁኔታና በቁጣ ስሜት አንድ ድርጊት ፈፀመ (በንግግር፥ በስራ፥...)።

**አመናቀረ** ግ 1. አጣላ፥ አናቆረ። 2. በጥል አለያየ።

**መነባንብ** "ነበነበ" ስር ተመ.

**መነተገ** ግ መነተፈ፥ ቀማ፥ ነጠቀ።

**መነተፈ** ግ 1. ነጠቀ፥ ቀማ። 2. ሰረቀ።

**መነቸከ** ግ 1. በጣም አደፈ፥ ቆሸሸ። 2. በጣም ከማደፉ ወይም ከመቆሸሹ የተነሳ ቢያጥቡት አልፀዳ አለ (ለልብስ)። 3. አልታኘክ፥ አልገራ አለ፤ አኞ ሆነ (ስጋ)። 4. አላቆም ወይም አላባራ አለ (ዝናብ)።

**መንቻካ** ቅ 1. በቀላሉ የማይታኘክ፤ አኞ (ስጋ)። 2. ቶሎ የማያቆም ወይም የማያባራ (ዝናብ)። 3. (ዘይ.) ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ፥ ነገር ከያዘ የማይለቅ፤ ችክ።

**ተመናቸከ** ግ ችክ አለ።

**መነቸፈ** ግ ነጠቀ፥ በጠቀ።

**መነነ** ግ የአለምን ነገር፥ ተድላና ደስታን ንቆና

ትቶ፥ ከሰው ተለይቶ በዱር፥ በጫካ ወይም በገዳም ሊኖር ሄደ።
**መናኝ (መናኒ)** ስ የመነነ መነኩሴ፤ ባህታዊ።
**ምናኔ (ምነና)** ስ (ሃይ.) የአለምን ነገር፥ ተድላ ደስታን ንቆና ትቶ ከሰው በመለየት በዱር፥ በጫካ ወይም በገዳም መኖር።
**መነን** ስ 1. ነጭና ቀጭን የሆነ የፈትል አይነት። 2. (ዘይ.) ሀ. ቆንጆ፥ ውብ (ለሴት)። ለ.በጣም ቀጭን የሆነና ውሃነት ያየለበት (ቡና፥ ጠላ፥...)
**መነከሰ (መለከሰ)** ግ መነኩሴ ሆነ።
**መነኩሴ (መለኩሴ)** (ብ.ቁ. **መነከሳት**) ስ የምድራዊውን አለም ደስታና ድሎት በቃኝ ብሎ፥ ከፍትወተ ስጋ የተገለለና የተፀለየበት ወይም የተባረከ ቆብ የጫነ፥ ለነፍሱ ብቻ ያደረ ሰው (ለሴት መነኩሲት ይባላል)።
**መነኩሲት ወፍ** ስ እንደ ቆብ ያለ ቁንጮ ያላት ወፍ።
**ምንኩስና** ስ በአለም ላይ ያለውን ተድላና ደስታ ትቶና ንቆ በመገለል የመኖር ህይወት።
**አመነከሰ** ግ ቀድሶ ባርኮና ተገቢውን ስርአተ ፀሎት አድርጎ ቆብ ጫነለት ፤ መነኩሴ አደረገ።
**መነዘለ** ግ ሚዛን ደፋ፥ ከበደ፥ ወደ አንድ በኩል አጋደለ፥ አዘነበለ፤ አመዘነ።
**መነዘረ** ግ 1. ጥቅል ገንዘብን ተመጣጣኝ ዋጋ ወደአላቸው ቅንስናሽ ብሮች ወይም ሳንቲሞች ለወጠ፥ ዘረዘረ፥ ሸረፈ። 2. አንድን የሌላ አገር ገንዘብ ወደሌላ የውጭ አገር ገንዘብ ለወጠ፥ ቀየረ፥ ዘረዘረ። 3. ገንዘብ አወጣ፥ አባከነ፥ አጠፋ። *ገንዘቡን በሆነ ባልሆነው መንዝሮ ጨረሰው።* 4. ፀሃይ ወይም ነፋስ እንዲመታው ወይም እንዲያገኘው በተነ፥ ዘረጋ፥ አሰጣ፥ ዘረረ።
**ምንዛሪ** ስ 1. ከተወሰነ ጥቅል ገንዘብ ጋር እኩል ዋጋ የሚኖረው ቅንስናሽ ብር፥ ሳንቲም ወይም ዝርዝር ገንዘብ። 2. ለአንድ አገር ገንዘብ አቻ የሚሆን የሌላ አገር ገንዘብ።
**ምንዝር** ስ 1.በጥንታዊ የመሬት ስሪት ውስጥ በርስት አለቃው ስር ያሉና ዝምድና ያላቸው የርስቱ ተካፋዮች። 2. አለቃ ያልሆነ የበታች ሰራተኛ።
**መነደበ** ግ 1. ደበደበ፥ መታ፥ ነረተ (በዱላ፥ በብትር)። 2. ጎዳ፥ አሰቃዬ (ችግር፥ ረሃብ)።
**መነደገ** ግ በሃይል ነጠቀ፥ መነጨቀ፥ ቀማ።
**ተመነደገ** ግ በፍጥነት አደገ፥ ረዘመ።
**መነጀዘ** ግ በጣም አደፈ፥ ቸከ።
**መጅሊስ** ስ ጉባኤ፥ ሸንጎ፥ ለተወሰነ አላማ

አንድ ቦታ ላይ የተቀመጡ የሰዎች ስብስብ።
**መነገለ** ግ ከስሩ ነቀለ፥ ፈነቀለ።
**መነገጀ** "ነገደ" ስር ተመ.
**መነገገ** ግ መንገጭላ ወይም አገጭ ወይም ጉንጭ አካባቢ ይዞ አፍ አስከፈተ፥ ፈለቀቀ።
**መንጋጋ** በፊደል ተራው ተመ.
**መነጎለ**[1] ግ በሳ፥ ነደለ፥ ሰረሰረ።
**መንጎል** ስ ጠፍርን፥ ቀበቶን፥... ለመብሻ የሚያገለግል እንደ ወስፌ ያለ መሳሪያ።
**መነጎለ**[2] ግ ተናፈጠ፥ ጎልጉሎ አወጣ (ንፍጥን)።
**መንጎል** ስ ተጎልጉሎ የወጣ ወፍራም ንፍጥ።
**መነጠ** ግ በጣም ደሀየ፥ ተቸገረ።
**መናጢ** ቅ 1. ምንም የሌለው፥ ድሃ፥ ምስኪን። 2. ክፉ።
**መነጠረ** ግ 1. ጫካ፥ ዱር፥ ሳር ያለበትን ቦታ በመጨፍጨፍ ወይም በማጨድ አፀዳ፥ ወለል አደረገ። 2.ለይቶ አወጣ፥ አጠፋ። *ህዝቡ ሌቦችን ከያሉበት መነጠረ።* 3. በደንብ፥ ጥርት አድርጎ አጠበ። 4. በአርጩሜ ወይም በአለንጋ ገረፈ።
**መነጠቀ** ግ 1. በድንገት በሃይል ቀማ፥ ነጠቀ፤ መነጨቀ። 2. ነቅሎ፥ ስቦ፥ መዝዞ፥ ጎትቶ አወጣ። 3. ደምን በዋገምት ሳበ፥ ነጠቀ።
**መንጠቆ** ስ ሹልና ቆላፋ የሆነ የአሳ መያዣ ወይም ማጥመጃ ብረት።
**ተመነጠቀ** ግ 1.ድንገት ብድግ ብሎ ሄደ። 2- መጠቀ፥ ራቀ፥ ከፍ አለ ። 3. ፈጣን እድገት አሳየ።
**መነጥር** "መነፅር" ን ተመ.
**መነጨ** ግ 1. ፈለቀ፥ ተንፎለፎለ፥ ፈሰሰ፥ ጎረፈ (ለምሳሌ ውሃ ከመሬት ውስጥ)። 2. ተገኘ፥ ፈለቀ (ሃሳብ)።
**ምንጭ** ስ 1. ከመሬት ውስጥ ውሃ በተፈጥሮ የፈለቀበት ቦታ። 2. የአንድ ነገር መገኛ፥ መነሻ፥ ምክንያት።
**አመነጨ** ግ 1. ውሃ አፈለቀ። 2. አፈሰሰ፥ አወረደ (እንባን)። 3. አገኘ፥ አመጣ፥ አፈለቀ (ሃሳብን፥ መፍትሄን፥...)።
**መነጨረ** ግ 1. በተነ፥ ጫረ። 2. ጠጉርን በሚዶ አበጠረ።
**መንጫራ** ቅ 1. ፀጉሩ የተንጨበረረ። 2. (ዘይ.) ቁጡ፤ ጠባዩ የማይመች።
**መነጨቀ** ግ በሃይል በድንገት ነጠቀ፥ ወሰደ።
***መነጨቀ**
**መንጫቃ** ቅ ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ።
**ተመናጨቀ** ግ ተቆጣ፥ ተቆናጠረ።
**አመናጨቀ** ግ በቁጣና በማጥላላት ወይም

በንቀትና ስነስርአት በጎደለው አኳሂን ተናገረ።

**መነፅር (መነጥር)** ስ ክብ ወይም ሞላላ ወይም አራት ማእዘን ቅርፅ ያላቸው ጥንድ የማሳያ ብርጭቆዎች የተገጠመለት፥ ጆሮዎች ላይ የሚያርፉ ሁለት ዘንግ ያሉትና አፍንጫ ላይ እንዲያርፍ ሆኖ የተሰራ፥ በተለያዩ የአይን በሽታ ምክንያቶች የማየት አቅም ሲደክም ወይም አይንን ከፀሃይ ብርሃን ለመከላከል ሲባል አይን ላይ የሚደረግ መሳሪያ፤ አይነርግብ።



መነፅር

**መነፍ** "ነፈ" ስር ተመ.

**መና** 1. ከንቱ፥ ብላሽ፥ ዋጋ የሌለው። 2. ባዶ። *ገንዘቡን ሳያገኝ መናውን ቀረ።*

**መና ቀረ** 1. ባዶውን ቀረ። 2. ከንቱ፥ ብላሽ ሆኖ ቀረ።

**መና** ስ በመፅሃፍ ቅዱስ እንደተፃፈው እግዚአብሄር ከሰማይ እያወረደላቸው እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ ይመገቡት የነበረ ምግብ።

**መናሀሪያ** ስ 1. የህዝብ ማጓጓገዎች (መኪና፥ ባቡር፥...) መነሻና መድረሻ ጣቢያ። 2. መገናኛ፥ መሰብሰቢያ፥ መከማቻ። *የነጋዴዎች መናሀሪያ /የሌቦች መናሀሪያ።*

**መናሄ** "ምናሄ"ን ተመ.

**መናኛ** ቅ ጥራት የሌለው፥ ተራ።

**መናኝ** "መነነ" ስር ተመ.

**መናጀ** "ነዳ" ስር ተመ.

**መናገሻ ከተማ** "ነገሰ" ስር ተመ.

**መናጢ** "መነጠ" ስር ተመ.

**መናፈሻ** "ነፈሰ" ስር ተመ.

**መናፍቅ** ስ በአንድ ሃይማኖት ውስጥ አጠቃላይ ከሆነው ከእምነቱ ድንጋጌ ውጪ ለየት ያለ መንገድ ይዞ የሚከተልና በእምነቱ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ መሰረታዊ ነጥቦች የማይቀበል፤ ተጠራጣሪ።

**መን** ስ ሸማኔ የግራና የቀኝ እግሩን እያፈራረቀ ሲረግጠው አንዱ ወደ ላይ ሌላው ወደታች በመሆን ድርና ማግን የሚያሰባጥር ወይም የሚያወሳስብ የሸማኔ እቃ።


**መንማና** "መነመነ" ስር ተመ.

**መንስኤ** "*ነሳ" ስር ተመ.

**መንሸላሊት** "እንሸላሊት"ን ተመ.

**መንሽ** "መነሸ" ስር ተመ.

**መንቀል** ስ ረዘም ብሎ ቀጠን ያለ አንገት ያለው የውሃ መያዣ ቅል ወይም ሸክላ።



መንቀል

**መንቀሻ**[1] "ነቀሰ[1]"ስር ተመ.

**መንቀሻ**[2] "ነቀሰ[2]" ስር ተመ.

**መንቃራ** "መነቀረ" ስር ተመ.

**መንቆር** "ነቆረ" ስር ተመ.

**መንበር** ስ 1. መቀመጫ ወይም ወንበር (ለንጉስ፥ ለፓትርያርክ፥...)። 2. እንደ ቀም ሳጥን ሆኖ በአራት ማእዘን መልክ የተሰራ የታቦት ወይም የፅላት ማስቀመጫ።

**መንበረ መንግስት** ስ የንጉስ የክብር መቀመጫ ወይም ወንበር፤ ዙፋን።

**መንበረ ፀባኦት** ስ ሰማያዊ የአምላክ ዙፋን።

**መንታ** ስ 1. በአንድ ጊዜ ከአንዲት እናት የተወለዱ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆች፥ ግልገሎች፥...። ቅ 2. የታችኛው ክፍሉ አንድ ሆኖ ከላይ እንደ ባላ ሁለት የሆነ።

**መንታ መንገድ** ስ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ መንገዶች የሚገናኙበት ወይም አንድ መስመር የነበረው ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች የሚከፋፈልበት መንገድ።

**መንታ ምላስ** 1. ለፍላፊ፤ ተሳዳቢ። 2. አንድን ጉዳይ በሚመለከት አንድ ጊዜ ሌላ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከበፊቱ የተለየ ሌላ ነገር የሚናገር፤ ቀላማጅ።

**መንትያ** ስ ከአንድ እናት ባንድ ጊዜ ከተወለዱት መንታ ልጆች አንዱ።

**መንቻካ** "መነቸከ" ስር ተመ.

**መንከላወሻ** "ከለወሰ" ስር ተመ.

**መንከት** "ነከተ" ስር ተመ.

**መንከፍ** ቅ ቂል፥ ሞኝ፤ እንክፍ።

**መንካ ቁልቋል** የ"ቁልቋል" ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**መንካከ** ስ የበቆሎ ቅንጨ።

**መንኩራኩር** ስ ከመሬት ውጭ ወደ አሉ

ፕላኔቶች ወይም በጠፈር ላይ ለሚካሄዱ ልዩ ልዩ ጥናቶች የሚላኩ ተመራማሪዎች፥ መሳሪያዎች+... የሚጓዙበት ዘመናዊ መሳሪያ::

**መንደልት** "ነደለ" ስር ተመ.

**መንደልቶ** ዝ.ከ.

**መንደሪን** ስ እንደ ብርቱካን ያለ፥ ቅርፊቱ በቀላሉ ሊላጥ የሚችልና ውስጡ ብዙ ፍሬዎች ያሉት የሚበላ የፍራፍሬ አይነት፡፡

**መንደር** ስ በተወሰነ አካባቢ ቤቶች እጅብ ብለው፥ ተቀራርበው የተሰሩበት፥ በገጠር ወይም በከተማ ውስጥ የሚገኝ የመኖሪያ ቦታ፥ ሰፈር፥ አምባ::

**መንደረኛ** ቅ መንደር ለመንደር የሚዞር፥ ስራ ፈት፥ አውደልዳይ::

**መንደርተኛ (መንደረተኛ)** ስ በአንድ መንደር የሚኖሩ ሰዎች::

**መንደርቶ** ስ ራሳም ወይም ቋራም ዱላ፤ መንዶ::

**መንደርደሪያ** "ደረደረ" ስር ተመ.

**መንዲስ** ቅ ወፍራም፥ ደንዳና፥ ግዙፍ::

**መንዶ (ሜንዶ)** ስ መንደርቶ::



መንዶ

**መንጃ ፈቃድ** "ነዳ" ስር ተመ.

**መንገድ** ስ 1. መሂጃ፥ መተላለፊያ፥ መመላለሻ፤ ጎዳና:: 2. ዘዴ፥ ብልሃት፥ አሰራር:: *ችግሩን በሌላ መንገድ ማስወገድ ይቻላል::* 3.አቅጣጫ፥ መልክ፥ በኩል:: *ጉዳዩን በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል::*

**መንገድ ሄደ** ራቅ ወዳለ ቦታ ሄደ::

**መንገድ ለቀቀ** አሳለፈ፥ መተላለፊያ ሰጠ፥ ዞር አለ::

**መንገድ መታው** ብዙ መንገድ በመሄዱ ደከመ፥ ጣመነ::

**መንገድ ሰጠ** 1. አሳለፈ፥ ዞር አለ፥ መንገድ ለቀቀ:: 2. አንድ ነገር እንዲያደርግ አሳየ፤ መራ::

**መንገድ ቀደደ** 1. መንገድ አወጣ፥ አበጀ:: 2. አዲስ ስራን ለመስራት የመጀመሪያው ሰው ሆነ::

**መንገድ አወጣ** በፊት ያልነበረ አዲስ መንገድ ወይም መተላለፊያ ሰራ፤ መንገድ ቀደደ::

**መንገድ አገኘ** 1. ሰበብ፥ ምክንያት አገኘ:: 2. ዘዴ፥ ብልሃት አገኘ::

**መንገድ ከፈተ** 1 አዲስ መንገድ፥ ጎዳና ሰራ፤ መንገድ ቀደደ:: 2 አሳለፈ፥ ዞር አለ፥ መንገድ ለቀቀ:: 3. አዲስ ስራን ለመስራት የመጀመሪያው ሰው ሆነ::

**መንገድ ያዘ** ፈር፥ መስመር ያዘ::

**መንገድ ጠረገ** መንገድ ቀደደ::

**መንገድ ጠራጊ** አንድ አዲስ ስራን ለመስራት የመጀመሪያ የሆነ፥ ጀማሪ::

**የመንገድ አልጋ** ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነና መተጣጠፍ የሚችል፥ ለማጓጓዝ አመቺ የሆነ አልጋ::

**መንገደኛ** ስ 1. በመንገድ ላይ የሚተላለፍ፤ አላፊ አግዳሚ:: 2. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ወይም ለመጓዝ የተነሳ ወይም በመጓዝ ላይ ያለ:: 3. አንድ ቦታ ረግቶ የማይቀመጥና መንገድ የሚያበዛ፤ ሂያጅ::

**መንገጭላ (መንጋጭላ)** ስ የታችኛዎቹ ጥርሶች የሰፈሩበት አካል፤ አገጭ፥ ግንጭል::

**መንጋ** ስ 1. በአንድነት የተሰበሰበ ከብት:: 2.ብዙ፥ አያሌ:: *መንጋ ፈሪ::*

**መንጋጋ** ስ የውሻ ክራንቻ ከሚባለው ጥርስ ኋላ የሚገኝና ምግብ ለማኘክና ለማድቀቅ የሚያገለግል ጠፍጠፍ ያለ ትልቅ ጥርስ::(ስእሉን ጥርስ ስር ተመ.)::

**መንጋጭላ** "መንገጭላ"ን ተመ.

**መንግስት** "ነገሰ" ስር ተመ.

**መንጎል**[1] "መነጎለ[1]" ስር ተመ.

**መንጎል**[2] "መነጎለ[2]" ስር ተመ.

**መንጎል**[3] ስ ቀለም እየተጠቀሰ የሚፃፍበት ብእር የተሰካበት ዘንግ፤ የብእር እጀታ::

**መንጠቆ** "መነጠቀ" ስር ተመ.

**መንጫራ** "መነጨረ" ስር ተመ.

**መንጫቃ** "መነጨቀ" ስር ተመ.

**መንጮረር** "ጮረረ" ስር ተመ.

**መንፈስ** (ብ.ቁ. **መናፍስት**) ስ 1. የማይዳሰስ፥ የማይጨበጥ፥ ረቂቅ ነገር:: 2. ሀሊና፥ አእምሮ:: *የመንፈስ ደስታ አገኘ::* 3. ስሜት፥ ፍላጎት:: *መንፈሱ ተነሳሳቷል::* 4. የነገር፥ የስራ፥ የሃሳብ አዝማሚያ፥ ሁኔታ::

**መንፈሱ ሞተ** ተስፋ ቆረጠ፥ የመንፈስ ብርታት አጣ::

**መናፍስት** ስ 1. የመንፈስ ብዙ ቁጥር:: 2. አጋንንት::

**መንፈሰ ደካማ** ስ ወኔ ቢስ፥ ሃሞተ ቢስ፥

በቀላሉ ተሰፋ የሚቆርጥ።

**መንፈስ ጉባኤ (መንፈሳዊ ጉባኤ)** ስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ተግባር ረገድ ልትፈፅመውና ልትከተለው የሚገባትን ጉዳይ እየመከረ እንዲወስን በ1918 ኣ/ም የተቋቋመ ጉባኤ።

**መንፈስ ጠንካራ** ስ ተስፋ የማይቆርጥ፥ የማይበገር፥ ብርቱ፥ ፅኑ።

**መንፈስ ቅዱስ** ስ 1.የእግዚአብሄር ባህርይ የሆነ፥ የማይዳሰስና የማይጨበጥ ረቂቅ መለኮታዊ ሃይል። 2. ከሶስቱ ስላሴዎች አንዱ የሆነ እግዚኣብሄር ኣምላክ።

**መንፈሳዊ** ቅ 1. ሃይማኖት ነክ። 2. ሃይማኖተኛ፥ ኣማኝ፥ የእግዚኣብሄርን ትእዛዝ የሚያከብር። 3. በሃይማኖቱ ስርኣት መሰረት ከሞት በሂላ ላለው ህይወት ራሱን የሚያዘጋጅ፤ ኣለማዊ ያልሆነ።

**መንፈሳዊ ቅናት** ስ ሌላው ከደረሰበት ደረጃ ለመድረስ፥ ያደረገውን ጥሩ ነገር ለማድረግ፥... የሚፈጠር በምቀኝነት ላይ ያልተመሰረተ የፉክክር ስሜት፥ ፍላጎት።

**መንፈሳዊ ባህል** ስ እንደ ሙዚቃ፥ ስነፅሁፍ፥ ስእል፥ ርእዮተኣለም፥ ስነ ምግባር፥... ያለ የኣንድ ማህበረሰብ ባህል።

**መንፈሳዊ ትምህርት** ስ ሃይማኖት ነክ ትምህርት።

**መንፈቅ** ስ የስድስት ወር ጊዜ ወይም የኣመት ኣጋማሽ።

**መንፈቀ ሌሊት** ስ እኩለ ሌሊት።

**መንፈቀ መኣልት** ስ እኩለ ቀን።

**መኖ** ስ የከብት ቀለብ።

**መኖሪያ** "ኖረ" ስር ተመ.

***መኘ**

**ምኞት** ስ ኣንድን ነገር የማድረግ፥ የማግኘት፥... ፍላጎት፥ ጉጉት፥ ከጃላ።

**ተመኘ** ግ ኣንድን ነገር ለማግኘት፥ ለማድረግ፥... ፈለገ፥ ከጀለ፥ ጓጓ።

**መኝታ** "ተኛ" ስር ተመ.

**መኣልት** ስ ከጠዋት እስከ ማታ ያለው የብርሃን ጊዜ፥ ቀን።

**መኣት** ስ 1. ከፍተኛ እልቂት፥ ችግር፥... የሚያስከትሉ እንደ ረሃብ፥ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ ቃጠሎ፥... የመሳሰለ ኣደጋ፤ መቅሰፍት። 2. (ዘይ.) በጣም ብዙ፥ ኣያሌ። *መኣት ጓደኞች ኣሉት።*

**መኣት ኣወራ** የመከራ፥ የችግር፥... ወሬ ኣጋኖ ነገረ፥ ተናገረ።

**መኣት ኣውሪ** ሁልጊዜ የመከራን፥ የችግርን፥... መምጣት ብቻ የሚናገር።

**መኣተኛ** ቅ 1. ብዙ ጊዜ ስለጭንቅ፥ ስለመከራ፥ ስለችግር፥... ኣጋኖ የሚያወራ። 2. የሚሰራው ሁሉ የሚያስደንቅ፥ የሚያስገርም፤ ተኣምረኛ።

**መኣዛ (ማዛ)** ስ ደስ የሚል ሽታ ወይም ጠረን።

**መከለሻ** "ከለሰ" ስር ተመ.

**መከላ (መከሉ)** ስ ጓል፥ ፍንቃይ።

**መከላከያ** "ከለከለ" ስር ተመ.

**መከመከ** ግ ላላ፥ ለሰለሰ፥ ትምክ ትምክ ኣለ።

**መከረ** ግ 1. እንዲህ ቢሆን ይሻላል ብሎ ለሌላ ሰው ነገረ፥ ሃሳብ ሰጠ። *ለክረምቱ የዝናብ ልብስ እንድገዛ መከረኝ።* 2. ኣስጠነቀቀ፥ ገሰፀ። *ዳግመኛ ኣልኮል እንዳይጠጣ መከረው።* 3. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ሰው ባንድነት ዶለተ፥ ኣሴረ። 4. ተወያየ፥ ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋወጠ። *ከመወሰናችው በፊት በጉዳዩ ላይ ብዙ መከረውበታል።*

**መማከርት** ስ የምክር ቤት ኣባላት።

**መካሪ** ቅ 1. ምክር የሚሰጥ። 2. ተቆጪ፥ የሚገስፅ።

**መካር** ዝ.ከ.

**ምክር** ስ 1. ይጠቅማል ተብሎ የሚቀርብ ሃሳብ፥ አስተያየት፥...። 2. መደረግ ያለበትንና የሌለበትን ለመምረጥ በሰዎች መካከል የሚደረግ ውይይት፥ ንግግር፥ የሃሳብ ልውውጥ። 3. ተግሳፅ፥ ማስጠንቀቂያ። *ይህ ልጅ ፀባዩ እየተበላሸ ነው ምክር ያስፈልገዋል።*

**ምክር ሰማ** የተባለውን፥ የተነገረውን ተቀበለ፥ ፈፀመ፥ በስራ ላይ ኣዋለ።

**ምክር ተቀበለ** ዝ.ከ.

**ምክር ቤት** ስ 1. የተወሰኑ ሰዎች በኣባልነት ተመርጠው ወይም በሙያቸው ተቀጥረው ኣንድ የተወሰነ ስራ የሚያከናውኑበትና ድርጅቱ ወይም ቢሮው የተቋቋመበትን ኣላማ መሰረት በማድረግ ልዩ ልዩ ደንቦች፥ መመሪያዎች፥ ውሳኔዎች የሚያስተላልፉበት ቢሮ ወይም ድርጅት፤ የሰዎቹ ስብሰብም ምክር ቤት ይባላል። ምሳሌ ህግ መወሰኛ ምክር ቤት /ንግድ ምክር ቤት። 2. ፓርላማ።

**ምክክር** ስ መደረግ ያለበትንና የሌለበትን ለመወሰን ከኣንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መሃከል የሚካሄድ ውይይት፥ የሃሳብ ልውውጥ።

**ተመከረ** ግ 1. ምክር ሰማ፥ ተቀበለ። 2. በኣንድ ጉዳይ ላይ ውይይት፥ ምክር ተደረገ።

**ተመክሮ** ስ ምክር። *ተፈጥሮን ተመክሮ ኣይመልሰውም።*

**ተመካከረ** ግ ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋወጠ፥

ተወያየ።

**ተማከረ** ግ አንድን ጉዳይ ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የሌላ ሰውን ሃሳብ፥ አስተያየት ጠየቀ፤ ከሌላ ሰው ጋር ተነጋገረ።

**አመከሮ** ስ ምክር፥ ተግሳፅ፥ ማስጠንቀቂያ። *እስረኞቹ በአመክሮ ተፈቱ።*

**አማከረ** ግ 1. ምክር፥ ሃሳብ፥ አስተያየት ጠየቀ፥ እንዴት ቢሆን ይሻላል አለ። 2. በምክር ረዳ፥ አገዘ፤ ሃሳብ፥ አስተያየት ሰጠ።

**አማካሪ** ቅ 1.አንድን ስራ፥ ጉዳይ፥... በተመለከተ የሙያ ምክር የሚሰጥ ባለሙያ። *የህግ አማካሪ* ስ 2.ሃሳብ፥ አስተያየት፥ ምክር የሚሰጥ።

**መከራ** ስ ፈተና፥ ጭንቅ፥ ስቃይ።

**መከራ ቀመሰ** ችግር፥ ስቃይ ደረሰበት።

**መከራ በላ** ተሰቃየ፥ ተቸገረ።

**መከራ ዛቀ** ብዙ መከራ ደረሰበት።

**መከራውን አየ** 1. ለፋ፥ ማሰነ። 2. ተቸገረ፥ ተሰቃየ።

**መከረኛ** ቅ ችግር፥ ስቃይ፥ መከራ የማይለየው።

**መከር (መሀር)** ስ በክረምት ተዘርቶና በቅሎ የደረሰው እህል የሚታጨድበትና የሚሰበሰብበት ወቅት።

**መከር ተከተተ** በመከር ወቅት የተገኘው ሰብል ታጭዶ፥ ተሰብስቦና ተወቅቶ ወደ ጎተራ ገባ።

**መከተ** ግ 1. ተከላከለ (ጦርን በጋሻ፥ ዱላን በዱላ ወይም በእጅ፥...)። 2. አገደ፥ መለሰ፥ ተቋቋመ። 3. ጋረደ፥ ከለለ፥ ሸፈነ፥ መከታ ሰራ።

**አይመከተውም** 1.አይመልሰውም 2. አይበቃውም፥ አያጠግበውም።

**መከታ** ስ 1.መከላከያ ወይም መመከቻ ጋሻ። 2. በሸንበቆ፥ በጨፈቃ፥... የሚሰራ ከለላ፥ ግርዶሽ።

**ምክቶሽ (ምክት)** ስ ሁለት ሰዎች አንዱ ሌላውን በያዘው ዱላ እንዳይመታው እየተከላከሉ የሚጫወቱት ባህላዊ ጨዋታ።

**መከተቻ** "ከተተ" ስር ተመ.

**መከነ** ግ 1. የማይወልድ፥ ፍሬ የማይሰጥ ሆነ። 2. ጠፋ፥ ሞተ (ሆድ ውስጥ ያለ የኮስ ትል)።

**መካን (መሃን)** ስ መውለድ የማትችል ሴት ወይም ማስወለድ የማይችል ወንድ።

**መካን እንዶድ** ስ የማያፈራ እንዶድ።

**የመሃን ልጅ** ብርቅዬ፥ የሚሳሱለትና ተሞላቆ ያደገ ልጅ።

***መከኘ**

**ምክንያት** ስ 1. አንድ ነገር ሊሆን፥ ሊፈፀም፥ ሊደረግ የቻለበት ወይም የሚችልበት መሰረተ ነገር፥ ሳቢያ፥ መነሻ። 2. ሰበብ። *ላለመስራት ምክንያት አታብዛ።*

**ተመካኘ** ግ 1. በሌላ ተሳበበ፥ ተላከከ። 2. ሰበብ፥ ምክንያት ተሰጠ።

**አመካኘ (አመሃኘ)** ግ 1. በሌላ አሳበበ፥ አላከከ። 2. ሰበብ፥ ምክንያት ሰጠ።

**መከዳ** ስ እንደ ትራስ ሆኖ የተሰራ የእጅ፥ የጎን መደገፊያ።

**መከፍከፊያ** "ከፈከፈ" ስር ተመ.

**መኪና** ስ ሰውን፥ እቃን፥... በመሬት ላይ ለማጓጓዝ የሚያገለግል አራት ወይም ከዚያ በላይ ጎማዎች ሊኖሩት የሚችልና ሞተሩ በነዳጅ ሃይል የሚንቀሳቀስ የተሽከርካሪ አይነት (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

**መኪና ያዘ** የሚነዳው መኪና አገኘ ወይም ባለመኪና ሆነ።

**መኪና ሰፊ** ስ ልብስ ሰፊ።

**መኪና ነጂ** ስ ሾፌር።

***መካ**

**ተመካ** ግ ተማመነ (በሃብቱ፥ በእውቀቱ፥ በወገኑ፥...)።

**መመኪያ** ስ አለኝታ፥ መከታ፥ መኩሪያ።

**ትምክህት** ስ ከመጠን በላይ በራስ መመካት፥ መተማመን፤ ራስን ከፍ አድርጎ የማየት ስሜት።

**ትምክህተኛ** ቅ ከመጠን በላይ በራሱ የሚመካ፥ የሚተማመን፥ ራሱን ከፍ አድርጎ የሚያይ፥ ማንአህሉኝ ባይ።

**አስመካ** ግ አኮራ። *የሚያስመካ ስራ ሰርቷል።*

**መካሪ** "መከረ" ስር ተመ.

**መካር** ዝ.ከ.

**መካተቻ** "ከተተ" ስር ተመ.

**መካኒክ (ሜካኒክ)** ስ ሞተር ነክ የሆኑ ነገሮችን፥ ማሽኖችን፥ መኪናን፥... የማደስ፥ የመገጣጠም፥... ስራ የሚሰራ ባለሙያ።

**መካን** "መከነ" ስር ተመ.

**መካከለኛ** "*ማከለ" ስር ተመ.

**መካከል** ዝ.ከ.

**መካያ** ስ መጨረሻ።

**በመካያው** በስተመጨረሻ፥ በሗላ። *በመካያው ነገሩ ሁሉ እንዲህ ሆነ!*

**መኬ** ስ ዥንጉርጉር መልክ ያለው አደንጓሬ።

**መክሊት** ስ ሰላሳ ኪሎ ግራም ያህል የሚመዝን የክብደት መለኪያ።

**መክሰስ** ስ በምሳና በእራት መካከል ለእራት

መጸረሻ ተብሎ የሚበላ ምግብ፤ መቆያ::

**መከተፊያ** "ከተፈ" ስር ተመ.

**መከደኛ** "ከደነ" ስር ተመ.

**መከድ** ስ የጎራዴ እጀታ::

**መከፈልት** "*ከፈለ" ስር ተመ.

**መከፈቻ** "ከፈተ" ስር ተመ.

**መከፈያ** "ከፈለ" ስር ተመ.

**መኮሮኒ (ማካሮኒ)** ስ ከስንዴ ዱቄት ሊጥ በተለያየ ቅርፅ (ውስጠ ክፍት+ ጥምዝ+...) ሆኖ ባጭሩ የሚዘጋጅና ተቀቅሎ የሚበላ የምግብ አይነት::

**መኮስተሪያ** "ኮስተረ[1]" ስር ተመ.

**መኮትኮቻ** "ኮተኮተ" ስር ተመ.

**መኮንን** ስ 1. በወታደራዊ ስርአት ከምክትል መቶ አለቃ በላይ ያለ ማእረግ ያለው ሰው:: 2. የአንድ ስራ ወይም ጉዳይ የበላይ+ ሃላፊ+ አዛዥ (በወታደራዊ ስርአት):: *የዘመቻ መኮንን::*

**መኳንንት** (ነጠ.ቁ. **መኮንን**) ስ በንጉሳዊው ስርአት ውስጥ ለዙፋኑ ቅርበት ያላቸውና ልዩ ልዩ ማእረግ የሚሰጣቸው ሰዎች ::

**መወልወያ** "ወለወለ" ስር ተመ.

**መወርወሪያ** "ወረወረ" ስር ተመ.

**መወድስ** "ወደሰ" ስር ተመ.

**መወጠሪያ** "ወጠረ" ስር ተመ.

**መወጣጫ** "ወጣ" ስር ተመ.

**መዋስእት** ስ ቅዱስ ያሬድ የደረሰው የዜማ መፅሃፍ ስም፤ በአላትን+ በይበልጥም ደግሞ ሙታንን አስመልክቶ በዜማ የሚባል ምስጋና+ ፀሎት::

**መዋቅር** "ወቀረ" ስር ተመ.

**መዋያ** "ዋለ" ስር ተመ.

**መዋጀ** ስ ቀንበር የሚያርፍበት የበሬ ጫንቃ እንዳይጎዳ ሲባል በቀንበሩ ግራና ቀኝ ላይ የሚደረግ ቆዳ::

**መዋጥ** ስ ኬሻን+ ጆንያን+ ፍራሽንና የመሳሰሉትን ለመስፋት የሚያገለግል በመርፌ ቅርፅ የተሰራ ረዘምና ወፈር ያለ መስፊያ::

**መዋጮ** "ወጣ" ስር ተመ.

**መውረጃ** "ወረደ" ስር ተመ.

**መውቀጫ** "ወቀጠ" ስር ተመ.

**መውዜር** ስ የጠመንጃ አይነት::

**መውደቂያ** "ወደቀ" ስር ተመ.

**መውጅ** ስ ማእበል+ ሞገድ::

**መውጫ** "ወጣ" ስር ተመ.

**መዘለሻ** "ዘለሰ" ስር ተመ.

**መዘለገ** "ለመዘገ" ን ተመ.

**መዘለፊያ** "ዘለፈ[2]" ስር ተመ.

**መዘመዘ** ግ 1. ቆጠቆጠ+ ጠዘጠዘ+ መጠመጠ (ቁስል):: 2. ሰበ+ መጥጦ አወጣ:: *ልብሱን በበረኪና ዘፍዝፈህ ሳቆየው+ ቆሻሻውን በደንብ እንዲመዘምዘው::*

**መዘምር** "ዘመረ" ስር ተመ.

**መዘራዝር** "ዘረዘረ" ስር ተመ.

**መዘርዝር** ዝ.ክ.

**መዘበረ** ግ 1. አፈረሰ+ ናደ+ ገለባበጠ+ አጠፋ+ አወደመ:: 2. ዘረፈ+ በዘበዘ+ ባዶ አስቀረ::

**ምዝበራ** ስ ዝርፊያ+ ብዝበዛ::

**ምዝብር** ቅ የተበዘበዘ+ የተዘረፈ:: *ምዝብሩ ህዝብ+...::*


**ተመዘበረ** ግ ተበዘበዘ+ ተዘረፈ::

**መዘበቻ** "ዘበተ" ስር ተመ.

**መዘባበቻ** ዝ.ክ.

**መዘነ** ግ 1. ለካ+ ሰፈረ+ መጠነ (ክብደትን):: 2. ከሌላው ይበልጥ ከበደ+ ወደ አንድ ወገን አጋደለ:: *ከአንድ ጆንያ ጤፍ አንድ ጆንያ ጨው ይመዝናል::* 3. ገመተ+ ገመገመ:: *የነገሩን አካሄድ መዝና የራሱን ውሳኔ ይወስን::*

**ሚዛን** ስ 1. የክብደት መለኪያ:: 2. የአንድ ነገር ክብደትን ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ::




**ሚዛን** 2ኛ ፍቺ

**ሚዛኑን ጠበቀ** ሳይወድቅ ወይም ሳይንገዳገድ ለመሄድ+ ለመቆም+ ለመቀመጥ+... ተስተካከለ+ ተደላደለ::

**የሚዛን ልሳን** ስ ክብደቱ ወደበለጠበት የሚደፋ ወይም ወደቀለለበት የሚያቀና የሚዛኑ ልክ ማወቂያ ምልክት፤ ላንሲታ::

**የሚዛን ውልብልቢት** ስ የሚዛን ልሳን::

**ተመዘነ** ግ ተለካ+ ተሰፈረ+ ክብደቱ ታወቀ::

**አመዘነ** ግ 1. ወደ አንድ በኩል አጋደለ+ ከበደ+ አዘነበለ:: 2. አደላ:: *ልቡ ወደ እናቱ ያመዝናል::* 3. በለጠ+ ከፍ አለ:: *ከጉዳቱ ጥቅሙ ያመዝናል::*

**በአመዛኙ** በይበልጥ::

**አመዛዘነ** ግ 1. አሰበ+ አወጣ አወረደ+ አሰላሰለ:: 2. አስተያየ+ አነፃፀረ+ አወዳደረ::

**አመዛዛኝ** ቅ የሚያስተውል፥ የሚያስብ።

**አስመዘነ** ገ በሚዛን አስለካ፥ ክብደቱ እንዲታወቅ አደረገ።

**መዘከሪያ** "**ዘከረ**" ስር ተመ.

**መዘክር** ዝ.ክ.

**መዘወሪያ** "**ዘወረ**" ስር ተመ.

**መዘውር** ዝ.ክ.

**መዘዘ** ገ ሰቦ፥ ለይቶ፥ ጎትቶ አወጣ።

**መዝዞ አወጣ** ካለበት፥ ከተደበቀበት ፈልጎ አወጣ፥ አጋለጠ፥ አሳየ።

**መዘዝ** ስ 1.የጠብ፥ የነገር፥ የክፉ አጋጣሚ፥... መነሻ ምክንያት፤ ጦስ፥ ሰበብ። 2. በአንድ ነገር ምክንያት ተያይዞ የሚመጣ ችግር።

**መዘዘኛ** ቅ ጦሰኛ፥ ጠንቀኛ፥ ሰበበኛ።

**መዘዞ** ስ መለሎ፥ ቁመቱ ዘለግ ያለ፥ ሎጋ።

**ተመዘዘ** ገ አደገ፥ ረዘመ፥ ቁመት ጨመረ።

**ተማዘዘ** ገ ከተጣላው ሰው ጋር ለመታኮስ፥ ለመፋለም፥ ለመጋደል፥... ዱላ ወይም ሌላ መሳሪያ አወጣ። *ከባላጋራው ጋር ሽጉጥ ተማዘዙ።*

**አማዘዘ** ገ ሰዎች በዱላ ወይም በሌላ መሳሪያ ለመፋለም እንዲጋበዙ ሰበብ፥ ምክንያት፥...ሆነ፤ አጣላ።

**መዘገበ** ገ 1. በመረጃነት እንዲያገለግል ፃፈ፥ በሰነድ አሰፈረ (አንድን የተወሰነ ጉዳይ) ። 2. በአንድ ቡድን ወይም ተቀም ውስጥ አባል አድርጎ ያዘ ወይም ስሙን ፃፈ።

**መዝገብ** ስ ልዩ ልዩ መረጃዎች (የስም፥ ወይም የሰነድ ዝርዝር ወይም ወጪና ገቢ) ተመዝግበው የሚያዙበት ትልቅ ደብተር።

**መዝገበ ቃላት** ስ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት በፊደል ተራቸው ተመዝግበውና በራሱ ወይም በሌላ ቋንቋ ፍቺ ተሰጥቷቸው የሚገኙበት መፅሃፍ።

**መዝገብ ቤት** ስ አንድ መስሪያ ቤት የሚያከናውናቸው ጉዳዮችና የመስሪያ ቤቱን ሰራተኞች የሚመለከት መረጃ ተመዝግቦ የሚቀመጥበት ክፍል።

**ምዝገባ** ስ ለአንድ ለተወሰነ ተግባር ስምን የመፃፍ ወይም የማፃፍ ተግባር።

**ተመዘገበ** ገ (አንድ መረጃ፥ ስም ዝርዝር፥...) በፅሁፍ ሰፈረ፥ ተፅፎ ተያዘ።

**አስመዘገበ** ገ አንድ ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ወይም ከፍተኛ ተግባር በማከናወን ራሱን አሳወቀ፤ የበላይነቱን አሳየ።

***መዘገዘገ**

**ተምዘገዘገ** ገ እየተወነጨፈ በሃይል ተወረወረ፥ ተስፈነጠረ፥ ተውዘገዘገ።

**ተምዘግዛጊ** ስ ተወንጫፊ፥ ባየር ላይ ሂያጅ ።

**አምዘገዘገ** ገ በሃይል አስፈንጥሮ፥ አሽቀንጥሮ ወረወረ።

**አመዘግዛጊ** ያየር ላይ ጦር መሳሪያዎችን ከምድር ላይ መወንጨፊያ።

**መዛለያ** "**ዘለለ**[1]" ስር ተመ.

**መዛቂያ** "**ዛቀ**" ስር ተመ.

**መዛዝኝ** (**መዛዝይ**) ስ ለማገርነት የሚያገለግል፥ መለል ያለ እሸሃም የእፅዋት አይነት።

**መዝሙረኛ** "**ዘመረ**" ስር ተመ.

**መዝሙር** ዝ.ክ.

**መዝናኛ** "**ዘና**" ስር ተመ.

**መዝገበ ቃላት** "**መዘገበ**" ስር ተመ.

**መዝጊያ** "**ዘጋ**" ስር ተመ.

**መዞሪያ** "**ዞረ**" ስር ተመ.

**መዥረገ** ገ ፍሬን ከዛፍ በብዛት ሸመጠጠ።

**መዥረጠ** ገ ሳበ፥ ጎትቶ አወጣ፥ ነቀለ፥ መዘዘ፥ አወለቀ።

**መዥርጥ** ስ ለኮሶ መድሃኒት ነው ተብሎ የሚወሰድ የእፅዋት አይነት።

**መዥገር** ስ 1 በእንስሳት ላይ በተለይ በጉያቸው አካባቢ የሚጣበቅና ደም የሚመጥ ተባይ። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ከያዘ የማይለቅ፥ መንቻካ ሰው።



መዥገር 1ኛ ፍቺ

**መይሳ** ቅ የሚመልስ፥ ወደሂላ የሚያስኬድ፥ እንዲያፈገፍግ የሚያደርግ። *መይሳው ካሳ።*

**መደለያ** "**ደለለ**[1]" ስር ተመ.

**መደላድል** "**ደለደለ**" ስር ተመ.

**መደመደ** ገ 1. በመደዳ ቆረጠ፥ አጨደ። 2. አሳጥሮ ቆረጠ፥ ከመከመ። 3. አጠፋ፥ አወደመ፥ ደመሰሰ። 4. ምድማድ አበጀ።

**መደመድ** ስ ከአንድ ከነበረ ነገር የቀረ ምልክት፥ ስር፥ ቅሪት።

**ምድማድ** ስ መኖሪያ፥ ማረፊያ (ሰወር ያለ ቦታ)።

**መደመር** "**ደመረ**" ስር ተመ.

**መደረቢያ** "**ደረበ**" ስር ተመ.

**መደርደሪያ** "ደረደረ" ስር ተመ.

**መደቅደቂያ** "ደቀደቀ" ስር ተመ.

**መደቆሻ** "ደቆሰ" ስር ተመ.

**መደበ** ግ 1. መደብ ሰራ (ለመኝታና ለመቀመጫ፥ ለችግኝ ማፍሊያ)። 2. በተወሰነ መጠን ወይም፣ ቁጥር፥ በተፈለገው አይነት ወይም በወገን በወገን ከፋፍሎ አስቀመጠ፥ ለየብቻ አደረገ፤ ደለደለ። 3. ለፈለገው ነገር ወይም ጉዳይ ለማዋል መጥኖ ወይም ወስኖ አዘጋጀ፥ አስቀመጠ። *ለወር ቀለብ መቶ ብር መድቧል።* 4. አሰማራ፥ ቦታ አስያዘ፥ ደለደለ። *የት መስሪያ ቤት መደቡህ?* 5. ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር አስያዘ፥ ሰጠ፥ አስቀመጠ (ለቁማር)።

**መደብ** ስ 1. ልዩ ልዩ አትክልቶችን ለመዝራት ወይም ችግኞችን ለማፍላት ተቆፍሮ የለሰለሰና ከፍ ብሎ የተደለደለ መሬት ወይም አፈር። 2. (በተለይ በገጠር ቤቶች ውስጥ) በግድግዳ ጥግና በምሰሶ ዙሪያ ከመሬት ከፍ ብሎ ከጭቃ የሚሰራ መቀመጫ፥ መኝታ፥ ድልዳል። 3. በገበያ ቦታ አነስተኛ ነጋዴዎች ሸቀጣቸውን የሚደረድሩበትና የሚቀመጡበት ከፍ ተደርጎ የተደለደለ ስፍራ። 4. በተወሰነ ልክ ወይም መጠን ከተሸነሸነ፥ ከተከፈለ ነገር አንዱ ክፍል (ለምሳሌ የቅርጫ ስጋ መደብ)። 5. ከእቁብ፥ ከቁማር፥… ላይ ለአንድ ሰው የሚደርስ የአንድ ጊዜ ክፍያ። 6. *ምራን የሚያርፍበት* የቀንበር አማካይ ቦታ። 7. በንግግር ወይም በፅሁፈት ጊዜ ስሙ፥ ተውላጠ ስሙ፥ ግሱ፥… የሚያመለክተው ሰው ደረጃ (አንደኛ መደብ እኔ፥ እኛ፤ ሁለተኛ መደብ አንተ፥ አንቺ፥ እናንተ ወዘተ. እንደሚለው ያለ)። 8. በላዩ ላይ ሌላ ነገር የሚሰራበት የመጀመሪያ ወይም ታችኛው መልክ። *መደቡ ጥቁር ሆኖ ቀይ አበባ ያለበት ጨርቅ።* 9. (ፓ.ኢኮ.) በአንድ በተወሰነ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ ህብረተሰብ ውስጥ በማምረት ተግባር ላይ ባለው ሚና፥ ከማምረቻ መሳሪያ ጋር ባለው ግንኙነት፥ ምርትን በመከፋፈል ረገድ ባለው ድርሻና ድርሻውን በሚያገኝበት ዘዴ አንዱ ከሌላው የሚለይበት የሰዎች ቡድን ወይም ክፍፍል። *የሳብ አደሩ መደብ።*

**መደበኛ** ቅ ቋሚ፥ ዋነኛ። *ከመደበኛ ስራው ውጪ ይነግዳል።*

**መደበኛ ስብሰባ** ስ አንድ የፖለቲካ ወይም ሌላ ድርጅት ወይም ማህበር በተወሰነ ጊዜ በቋሚነት የሚያደርገው ስብሰባ። *በምክር ቤቱ 10ኛ መደበኛ ስብሰባ ብዙ ውሳኔዎች ተላልፈዋል።*

**መደበኛ ቋንቋ** ስ በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና የህብረተሰቡ አብዛኛው ክፍል የሚጠቀምበት ቋንቋ።

**ምድብ** ስ የስራ ቦታ፥ ክፍል።

**ተመደበ** ግ 1. በተወሰነ መጠን፥ በተፈላጊው አይነት ወይም በወገን በወገኑ ተከፋፍሎ ተቀመጠ፥ ለየብቻ ተደረገ። 2. ለተፈለገው ነገር ወይም ጉዳይ ለማዋል ተመጥኖ፥ ተወስኖ ተዘጋጀ፤ ተቀመጠ። 3. ስፍራ ያዘ፥ ተደለደለ።

**መደብር** ስ ሱቅ።

**መደንቀሪያ** "ደነቀረ" ስር ተመ.

**መደንቆያ** "ደነቆለ" ስር ተመ.

**መደንጎሪያ** "ደነጎረ" ስር ተመ.

**መደወሪያ** "ደወረ" ስር ተመ.

**መደወተ** ግ በሃይል መታ፥ ጠለዘ፥ ደወለ።

**መደደቂያ** "ደደቀ" ስር ተመ.

**መደዳ** ስ ተርታ፥ መትር፥ ረድፍ።

**መደዴ** ስ (የን.አነ.) ያልተማረ፥ ያልሰለጠነ፥ ያልተገራ፥ ተራ ሰው።

**መደገሻ** "ደገሰ" ስር ተመ.

**መደጎሻ** "ደጎሰ" ስር ተመ.

**መዲና**[1] ስ 1.ዋና ከተማ።2. ዋና መገኛ ማእከል። *አዲስ አበባ የቆንጆዎቹ መዲና ናት።*

**መዲና**[2] ስ ብዙውን ጊዜ ይዘቱ ሃዘንና እንጉርጉሮ የሆነ ባለአራት ስንኝ የግጥም አይነት።

**መዳ** ስ ጣቃ፥ ጥቅል ጨርቅ።

**መዳመጫ** "ዳመጠ" ስር ተመ.

**መዳረሻ** "ደረሰ[1]" ስር ተመ.

**መዳሪያ** "ዳረ" ስር ተመ.

**መዳሻ** "ዳሰ" ስር ተመ.

**መዳብ** ስ ቀይ ቡናማ መልክ ያለውና የኤሌክትሪክ ሃይልን በጥሩ ሁኔታ ሊያስተላልፉ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ የሆነ የማእድን አይነት።

**መዳኛ** "ዳነ" ስር ተመ.

**መዳፍ** ስ ከወደ አውራ ጣት አካባቢ ያለው የውስጥ እጅ ታችኛው ክፍል።(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

**መድሃኒተኛ** "ዳነ" ስር ተመ.

**መድሃኒት** ዝ.ከ.

**መድህን** ዝ.ከ.

**መድሎ** "አደላ" ስር ተመ.

**መድረሻ** "ደረሰ[1]" ስር ተመ.

**መድረክ** ስ 1. በራፍ፥ ደፍ አጠገብ ያለ ቦታ። 2. በስብሰባ፥ በትያትር፥… አዳራሽ ውስጥ ተናጋሪው፥ ተዋናዩ፥… ለሁሉም እንዲታይ ለማድረግ ከወለሉ ከፍ ብሎ የተሰራ ቦታ። 3. በአንድ ጉዳይ ላይ ለመወያየት፥ ሃሳብ ለመስጠት፥… የተዘጋጀ ወይም የሚዘጋጅ አመቺ ሁኔታ።

**መድበል** ስ ጥንቅር፥ ስብስብ፥ ክምችት(ለምሳሌ

የቃላት መድበል)።


**መድን (መድህን)** "ዳነ" ስር ተመ.

**መድፍ** ስ አፈሙዙ ሰፊ የሆነ፥ ትልቅ ጥይት የሚጎርስና በርቀት ለመምታት የሚያስችል ከባድ መሳሪያ።

**መድፈኛ** ስ መድፍ የሚተኩስ ወይም የሚያስተኩስ የወታደር ክፍል።

**መድፍን ፀር** "ደፈነ" ስር ተመ.

**መዶሻ** ስ ብዙውን ጊዜ ከባድ የብረት ጭንቅላትና የብረት ወይም የእንጨት እጀታ ያለውና ምስማር ለመምታት፥ ድንጋይ ለመፈርከስ፥ የጎበጠ ብረትን ለማቃናት፥... የሚያገለግል የተለያየ መጠን ያለው መሳሪያ።



መዶሻ

**መጀመሪያ** "ጀመረ" ስር ተመ.

**መጅ** ስ 1. በወፍጮ ላይ ወደ ፊትና ወደ ሂላ በማመላለስ እህልን ለመከካት ወይም ለመፍጨት የሚያገለግል ትንሽ የወፍጮ ድንጋይ(ስእሉን ወፍጮ ስር ተመ.)። 2. በመፈጋፈግ የተነሳ የጠነከረ ወይም የደደረ የሰውነት ቆዳ። 3. በብጉንጅ ወይም በሌላ የቁስል አይነት ውስጥ የሚፈጠር የጠጠረ እብጠት።

**መገለ** ግ መግል ወጣ፥ ፈሰሰ።

**መግል** ስ ከቁስል ወይም በተለያየ ምክንያት ከተመረዘ የሰውነት ክፍል የሚወጣ ቢጫማ መልክ ያለው ወፈር ያለ ፈሳሽ።

**አመገለ** ግ መግል የያዘውን የሰውነት ክፍል በመጫን ወይም በማፍረጥ ፈሳሹ እንዲወጣ ወይም እንዲፈስ አደረገ።

**መገለጢጥ** "ገለጠጠ" ስር ተመ.

**መገመገ** ግ መጠመጠ፥ ለገለገ፥ ጠባ።

**መገበ**[1] ግ ቀለበ፥ አበላ፥ አጠጣ።

**መጋቢ** ስ የአበምኔት ምክትል የሆነ የገዳም ሹም።

**መጋቢ ወንዝ** ስ ወደ ትልቅ ወንዝ የሚቀላቀል ትንሽ ወንዝ።

**መጋቢት** ስ በሴት ገዳም ውስጥ የመጋቢነት ማእረግ ያላት ሴት መነኩሲት።

**ምግብ** ስ 1. ሰዎች፥ እንስሳትና ተክሎች በህይወት ለመቆየትና ለማደግ የሚበሉት፥ የሚጠጡትና የሚወስዱት ማንኛውም ነገር። 2. እንደ መጠጥ፥ ውሃ፥ ያሉትን የሚጠጡ ነገሮችን የማይጨምር ማንኛውም የሚበላ ነገር።

**ምግብ ቤት** ስ 1. በማንኛውም ቤት ውስጥ ሊኖር የሚችልና ለምግብ መብያ ተብሎ የተዘጋጀ ክፍል። 2. ምግብ እየተዘጋጀ የሚሸጥበት ቤት፤ ሆቴል።


**የምግብ ሸቀጥ** ስ ለምግብነት የሚውል ሸቀጥ።

**የምግብ ጠረጴዛ** ስ ምግብ የሚበላበት ጠረጴዛ።

**ተመገበ** ግ በላ፥ ጠጣ።

**መገበ**[2] ግ ገባ፥ ታየ (ኮከብ)። *ላቅራብ የተባለው ኮከብ የጥቅምትን ወር ይመግባል።*

**መግብተ አውራህ** ስ የአስራ ሁለቱ ወራት ኮከቦች መጠሪያ። (እነዚሁም ሚዛን፥ አቅራብ፥ ቀውስ፥ ጀዲ፥ ደለዊ፥ ሁት፥ ሃመል፥ ሰውር፥ ገውዝ፥ ሸርጣን፥ አሰድና ሰንቡላ ናቸው)።




መግብተ አውራህ

**መገበሪያ** "ገበረ" ስር ተመ.

**መገተሪያ** "ገተረ" ስር ተመ.

**መገናኛ** "*ገነኘ" ስር ተመ.

**መጋላ** ቅ ጠይም (ለከብት)።

**መጋልማ** ቅ ጠይምነት ያለው (ለከብት)።

**መጋረጃ** "ጋረደ" ስር ተመ.

**መጋቢ** "መገበ[1]" ስር ተመ.

**መጋቢ ሃምሳ አለቃ** ስ በወታደር ክፍል ውስጥ ከአስር አለቃ በላይና ከሃምሳ አለቃ በታች ያለ ማእረግ።

**መጋቢት**[1] ስ ከየካቲት ወር ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ሰባተኛ ወር ስም።

**መጋቢት**[2] "መገበ[1]" ስር ተመ.


**መጋኛ** ስ 1. የተዘጋን ቤት ከፍቶ በድንገት በመውጣት ወይም በመግባት፥ ክፍቱን ባደረ ውሃ በመታጠብ፥... የተነሳ ይመጣል ተብሎ

የሚታመንበት በሽታ፡፡ 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ከፉ፥ ተንኮለኛ፡፡

**መጋዘን** ስ የእቃ ማስቀመጫ ወይም ማከማቻ ክፍል፡፡

**መጋዝ** ስ እንደ ማጭድ ጥርስ ያለውና እንጨት፥ ብረት፥... ለመቁረጥ የሚያገለግል፥ ሳሳ ካለ ብረት የተሰራና እጀታ ያለው መሳሪያ፡፡

መጋዝ



**መጋዥ** ስ 1.ለግልቢያ የማይሆን፥ ሰጋርነት የሌለው የጭነት ፈረስ፤ ኣጋሰስ፡፡ 2. (ዘይ.፥ስድብ) መብላት የሚወድ፥ ሆዳም፡፡

**መጋፊያ** "ጋፈ" ስር ተመ.

**መግለቦ** ስ የኣሳ ማጥመጃ፡፡

**መግለጫ** "ገለጠ" ስር ተመ.

**መግላሊት** ስ የማሰሮ ወይም የቶፋ ወይም የምንቸት ክዳን፡፡

**መግል** "መገለ" ስር ተመ.

**መግቢያ** "ገባ" ስር ተመ.

**መግነዝ** "ገነዘ" ስር ተመ.

**መግዣ** "ገዛ" ስር ተመ.

**መግፊያ** "ገፋ" ስር ተመ.

**መግነጢስ** ስ ማግኔት፡፡

**መጎናጠፊያ** "ጎነፀፈ" ስር "መጎናፀፊያ"ን ተመ.

**መጎዛ** ስ ቀፎ እየደፋ ማር የሚበላ፥ ከውሻ የሚያንስና ከድመት የሚበልጥ ኣራት እግር ያለው የዱር ኣውሬ፡፡

**መጎጥ** ስ ኣይጠ መጎጥ፡፡

**መጎጥ አፍ** ቅ (ስድብ) ኣፉ እንደ ኣይጠ መጎጥ ያሞጠሞጠ፡፡

**መጓጓዣ** "*ጓዘ" ስር ተመ.

**መጠለያ** " ጠለለ" ስር ተመ.

**መጠመጠ** ግ 1. በጣም ጠባ፥ መገመገ፥ ለገለገ፡፡ 2. መጠጠ፡፡ 3. ኣጥብቆ ሳመ፡፡

**መጠቀ** ግ 1. ከፍ ኣለ፥ ርቆ ወደላይ ወጣ፥ ኣረገ፡፡ 2. ረቀቀ፥ ጥልቀት ኣገኘ (በኣስተሳሰብ በእውቀት፥...)፡፡

**ምጥቀት** ስ ጥልቀት፥ ብስለት፡፡

**ኣመጠቀ** ግ ተኮሰ፥ ወደ ሆዋ ላከ (መንኮራኩርን)፡፡

**መጠቅለያ** "ጠቀለለ" ስር ተመ.

**መጠባበቂያ** "ጠበቀ$^3$" ስር ተመ.

**መጠነ** ግ 1. በቂ፥ ልክ ነው ብሎ ያሰበውን ያህል ሰፈረ፥ ገመተ፡፡ 2. ልክ ሆነ፥ በቃ፡፡ *ሱሪሉ ልብስ አልመጠነውም! ሰፍቶቢታል*፡፡ 3. ኣቻ፥ ተስማሚ፥ እኩያ ሆነ፡፡ *ከማይመጥነው ሰው ጋር ጓደኝነት ጀምሯል፡፡*

**መጠን** ስ 1.ልክ፡፡ 2.የኣንድ ነገር ርዝመት ወይም እጥረት፥ ስፋት ወይም ጥበት፥ ውፍረት ወይም ቅጥነት፥ ብዛት ወይም ማነስ፡፡

**መጠን የሌለው** በጣም ብዙ፥ ስፍር ቁጥር የሌለው፡፡

**በመጠኑ** ተው.ግ. ሳይበዛ ወይም ሳያንስ በልኩ፡፡

**ኣለመጠን** በብዛት፥ ኣለልክ፡፡ *ያለመጠን በልቼ ሆዴን ኣመመኝ፡፡*

**ከመጠን በላይ** ከሚያስፈልገው በላይ፤ በብዛት፡፡

**የመጠን ለውጥ** ስ ኣንድ ነገር በኣይነት ሳይሆን መጠኑን በመጨመር ወይም በመቀነስ የሚያሳየው ለውጥ፡፡

**መጠነኛ** ቅ ያልበዛ ወይም ያላነሰ፥ ልከኛ፡፡

**ምጣኔ ሃብት** ስ የኣንድ ኣገር ጠቀላላ ሃብትና ቅስቃሴው፥ ኢኮኖሚ፡፡

**ምጥን** ቅ 1. ያልበዛ ወይም ያላነሰ፥ ልከኛ፡፡ ስ 2.ምጥን [ሽሮ]ጨው፥ በርበሬ፥ ሽንኩርትና ቅመማቅመም ገብቶበት የተዘጋጀ የሽሮ ዱቄት፡፡

**ተመጠነ** ግ ተለከቶ፥ ልኩ ተወስኖ ተዘጋጀ፡፡

**የተመጠነ** በልክ ተወስኖ የተዘጋጀ፡፡

**ተመጣጠነ** ግ ተቀራረበ፥ ተስተካከለ፥ ተነፃፀረ (በመጠን፥ በጉልበት፥ በችሎታ፥...)፡፡

**የተመጣጠነ** ሊይዝ የሚገባውን ኣስፈላጊ ነገሮች በውስጡ በተገቢው መጠን የያዘ (ምግብ፥ መጠጥ፥...)፡፡

**የተመጣጠነ ምግብ** ስ ለሰውነት እድገትና ጤንነት ኣስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ የያዘ ምግብ፡፡

**ተመጣጣኝ** ቅ የተቀራረበ፥ የተስተካከለ (በመጠን፥ በጉልበት፥ በችሎታ፥...)፡፡

**መጠይቅ** "ጠየቀ" ስር ተመ.

**መጠወተ** "መፀወተ" ን ተመ.

**መጠጊያ** "*ጠጋ" ስር ተመ.

**መጠጠ** ግ 1. ጠባ፥ መጠመጠ፥ ሳበ፡፡ 2. ፈሳሽ

የሆነን ነገር ስቦ ወይም መጥጦ አደረቀ:: 3. ጠፈፈ፥ ደረቀ:: 4. ምጥምጥ አድርጎ ሳመ:: 5. በጠቅላላ ጨረሰ፥ ፈጀ::

**መጣጣ** ቅ ወዝ የሌለው፥ ደረቅ::

**ምጣጭ** ስ ታኝኮ፥ ተመጦ የተተፋ፥ ብላቶ::

**መጠጥ አለ** ግ ጠፈፍ አለ፥ መድረቅ ጀመረ (ጭቃ፥ የታጠበ ልብስ፥...)::

**መጠጥ ያለ** 1. ጠፈፍ፥ ደረቅ ያለ:: 2. በእድሜ በሰል ያለ::

**ምጥጥ ያለ** መጣጣ::

**ምጥጥ አደረገ** ግ1. በጣም አከሳ፥ ወዝ አሳጣ:: 2. በሙሉ ጨረሰ::3.መጥምጦ ሳመ::

**ተመጠጠ** ግ ፈሳሹ ተስቦ ወጣ፥ ባዶ ቀረ፥ ደረቀ::

**አመጠጠ** ግ አደረቀ:: *ጠረጴዛው ላይ የፈሰሰውን ውሃ በጨርቅ አምጥጭው::*

**መጠጥ** "ጠጣ" ስር ተመ.

**መጠጫ** ዝ.ከ.

**መጡብሽ** "መጣ" ስር ተመ.

**መጢቃ** ስ ዲቃላ (ለበግ፥ ለፍየል)::

**መጣ** ግ 1. ተናጋሪው ወይም "መጣ" ባዩ ወዳለበት አካባቢ ተራመደ፥ ተጓዘ፥ ቀረበ፥ ተጠጋ:: 2. ቀድሞ ከሚገኝበት ወይም ከነበረበት ቦታ ተናጋሪው ባለበት አካባቢ ተገኘ:: *ቤት ቀይሮ ከናዝሬት እዚህ መጥቷል*:: 3. ከሄደበት ተመለሰ:: 4. ተቃረበ፥ ተዳረሰ (ጊዜ):: *ክረምት መጣ::* 5. ትዝ አለ፥ ታወሰ፥ ፈለቀ (ሃሳብ):: *አንድ ሃሳብ መጣልኝ!* 6. ሆነ (የስሌት ውጤት):: *ሁለት ና ሁለት ሲደመር አራት ይመጣል::* 7. ያዘ፥ ሊወጣ ተቃረበ:: *ሽንቱ መጣ::* 8. ተፈጠረ፥ አጋጠመ፥ ደረሰ (ችግር፥ መከራ፥...)::

**መጣበት** ትነሳበት፥ ጀመረው (ጉዴት፥ ቁጣ፥...)::

**መጡብሽ** ስ 1. ወደ ተረኛው ማህበረተኛ ቤት የሚገባ ወይም የገባ ፀበል ፀዲቅ:: 2. ቶሎ የምትገል ስስ ምጣድ::

**በሚመጣው** በሚቀጥለው:: *በሚመጣው ሳምንት እንገናኛለን::*

**የመጣው ቢመጣ** የሆነው ቢሆን፥ የፈለገው ችግር ቢደርስ::

**መጣተኛ (መፃተኛ)** ስ ለአገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ የሆነ፥ ስደተኛ፥ ባይተዋር የሆነ (ሰው)::

**መጤ** ቅ 1. የአገር ተወላጅ ያልሆነ፥ ከሌላ ቦታ መጥቶ የሰፈረ:: 2. አገር በቀል ያልሆነ::

**አማጭ (አማጪ)** ስ ለሴት ባል ወይም ለወንድ ሚስት የሚያመጣ፥ የሚያገናኝና የሚያጋባ ሰው አማላጅ፥ ሽማግሌ ::

**አስመጭ** ስ የተለያዩ ሸቀጦችን ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ ለንግድ የሚያስገባ ግለሰብ ወይም ድርጅት::

**አስመጭና ላኪ** ስ የተለያዩ ሸቀጦችን በንግድ መልክ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባና ከአገር ውስጥ ደግሞ ወደ ውጭ አገር የሚልክ ግለሰብ ወይም ድርጅት::

**መጣብር** ስ ከነሃስ፥ ከብር፥ ከወርቅ ተሰርተው በፈረስ እቃ ላይ የሚሰፉ ጌጦች::

**መጣብቅ** "*ጠበቀ" ስር ተመ.

**መጣያ** "ጣለ" ስር ተመ.

**መጣጣ[1] (መፃፃ)** ስ ሆምጣጣ::

**መጣጣ አይብ** ስ በሶብላ፥ ሽንኩርትና ሌሎች ቅመማት ተጨምረውበት ለጥቂት ቀናት በደንብ በተከደነ እቃ ውስጥ ከቆየ በሁዋላ ለምግብነት የሚያገለግል አይብ::

**መጣጣ[2]** "መጠጠ" ስር ተመ.

**መጣፍያ** "ጣፈ" ስር ተመ.

**መጣፍጥ** ስ የወጥ ማጣፈጫ ቅመም፤ ነጭ አዝሙድ፥ ጥቁር አዝሙድ::

**መጤ** "መጣ" ስር ተመ.

**መጥለቂያ** "ጠለቀ[2]" ስር ተመ.

**መጥረቢያ** "ጠረበ" ስር ተመ.

**መጥረጊያ** "ጠረገ" ስር ተመ.

**መጥሪያ** "ጠራ[1]" ስር ተመ.

**መጥበሻ** "ጠበሰ" ስር ተመ.

**መጥኔ** "ጠና" ስር ተመ.

**መጥፎ** "ጠፋ[1]" ስር ተመ.

**መጨለስ (ሞጨለሰ)** ግ ፀጉርን አስተኛ፥ ለሸ አደረገ (በቅባት፥ በውሃ፥...)::

**መጭላሳ (ምጭልስ)** ቅ (በቅባት፥ በውሃ፥...) የተኛ፥ ለጥ ያለ ፀጉር::

**ተመጨለሰ** ግ ተኛ፥ ለጥ አለ (ፀጉር)::

**መጨለፊያ** "ጨለፈ" ስር ተመ.

**መጨረሻ** "ጨረሰ" ስር ተመ.

**መጨቃ** ስ ነጭና ጠንካራ ድንጋይ::

**መጨቅጨቂት** "ጨቀጨቀ[1]" ስር ተመ.

**መጨበጫ** "ጨበጠ" ስር ተመ.

**መጩኔ** ስ 1. የፈረስ፥ የበቅሎ ቀላቢና ለጓሚ:: 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ያጋፋሪ ምክትል::

**መጨጊያ** ስ መከዳ::

**መጫሚያ** "ጫማ[1]" ስር ተመ.

**መጫሪያ** "ጫረ" ስር ተመ.

**መጫኛ** "ጫነ" ስር ተመ.

**መጫወቻ "*ጫወተ"** ስር ተመ.

**መጭ** ስ ግንዱም ሆነ ቅጠሉ ባጠቃላይ ኑግ የሚመስል የአረም አይነት::

**መጭ** በቅሉን "ሂጂ" ለማለት የሚነገር ቃል::

**መጭ አለ** ግ 1. በቅሉን "ሂጂ" አለ:: 2. (ዘይ.) ፈጥኖ፥ ሮጦ ሄደ::

**መጭላሳ "መጨለሰ"** ስር ተመ.

**መጭመቂያ "ጨመቀ"** ስር ተመ.

**መፀዳጃ "ፀዳ"** ስር ተመ.

**መፀዳጃ ቤት** ዝ.ከ.

**መፀወተ (መጠወተ)** ግ ለድሃ፥ ለችግረኛ ቸረ፥ ሰጠ፣ ተዘከረ::

**ምፅዋት (ምጥዋት)** ስ ለተቸገረ፥ ለድሃ ወይም ለለማኝ የሚሰጥ ገንዘብ፥ ምግብ፥ ልብስ፥...::

**ምፅዋተኛ (ምጥዋተኛ)** ቅ ምፅዋት የሚሰጠው ድሃ፥ ችግረኛ፣ ለማኝ፣ ተመፅዋች::

**ተመፀወተ (ተመጠወተ)** ግ ምፅዋት ተቀበለ (ድሃ፥ ችግረኛ፣ ለማኝ)::

**ተመፅዋች (ተመጥዋች)** ቅ ምፅዋት ተቀባይ፥ ድሃ፥ ችግረኛ፥ ለማኝ፣ በምፅዋት የሚተዳደር (ሰው)::

***መፀደቀ**

**ተመፃደቀ** ግ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፥ አኩራራ፣ ራሱን በራሱ አደነቀ፥ አመሰገነ (እንዲህ አድርጌ፥ እንዲህ ሰርቼ፥... በማለት)::

**ተመፃዳቂ** ቅ እንዲህ አድርጌ፥ እንዲህ ሰርቼ እያለ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፥ ራሱን የሚያደንቅ፥ የሚያመሰግን፣ ግብዝ::

**አመፃደቀ** ግ እንዲህ አድርጌ፥ እንዲህ ሰርቼ እያለ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፥ አደነቀ፥ አመሰገነ::

**መፀው** ስ ከመስከረም 26 እስከ ታህሳስ 25 ቀን ያለው ወቅት፥ ጊዜ::

**መፃተኛ "መጣ"** ስር ተመ.

**መፃጉእ** ስ 1. የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የሚኖር በሽተኛ፣ ሽባ:: 2. ሰውነቱ እንደልቡ የማይታዘዝለት፣ በደረቱ ወይም በጀርባው አካባቢ እብጠት ያለበት አጭር፥ ጎበጥ ያለ ሰው::

**መፃፃ "መጣጣ[1]"** ን ተመ.

**መፅሃፍ "ፃፈ"** ስር ተመ.

**መፈናፈኛ "*ፈነፈነ"** ስር ተመ.

**መፈንቅለ መንግስት "ፈነቀለ"** ስር ተመ.

**መፈክር "ፎከረ"** ስር ተመ.

**መፋቂያ "ፋቀ[1]"** ስር ተመ.

**መፍሉስ "ፈለሰ"** ስር ተመ.

**መፍትሄ "ፈታ"** ስር ተመ.

**ሙ** የ"መ" ፊደል ካእብ ዘር::

**ሙሃሂት (ሙሃይት)** ስ በስተጎን ያለ የጭንና የዳሌ መገናኛ (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)::

**ሙሉ "ሞላ"** ስር ተመ.

**ሙላ** ስ የጭንና የዳሌ መገናኛ፣ መታጠፊያ (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)::

**ሙልሙል "ሞለሞለ"** ስር ተመ.

**ሙልጭልጭ "*ሞለጨለጨ"** ስር ተመ.

**ሙሬ (ሙሪ)** ስ 1. ፍሬው ጥቁር የሆነና ጤፍ የሚመስል የሳር አይነት:: 2. ከሙሬ ወይም ከንሳ፥... የተበጀ መጥረጊያ ወይም ኖራ መቀቢያ ቡሩሽ)::



ሙሬ 2ኛ ፍቺ

**ሙር** ቅ የተማረና እውቀት ያለው ሆኖ ወፈፍ ስለሚያደርገው ብዙ የሚለፈልፍና የሚናገር፥ ንግግሩ ግን ፍሬ ነገር ያዘለ (ሰው)::

**ሙርሙርት "ሞረሞረ[2]"** ስር ተመ.

**ሙርዝኝ** ቅ ችኮ፥ ነዝናዛ፥ ነገር ከያዘ የማይለቅ::

**ሙርጥ** ስ 1.ቂጥ:: (ጎጃም):: 2. (ነውር) የወንድ ብልት::

**ሙርጥ አወጣ** ተሰነጠቀ (ምጣድ፥ ድስት)::

**ሙሴ** ስ 1. አምስቱን የኦሪት መፃህፍት የፃፈ የእስራኤል ነቢይ:: 2- የሰንበቴ ወይም የፅዋ ማህበርተኞች ሊቀመንበር፥ አለቃ:: 3. የመስፈሪያ አይነት (አስራ ስድስት ሙሴ አንድ ማድጋ ይሆናል)::

**ሙስሊም "ሰለመ[1]"** ስር "እስላም"ን ተመ.

**ሙስና[1]** ስ ውበት፥ ደምግባት፥ ላህይ::

**ሙስና[2]** ስ ለኮሶ ትል መድሃኒት ይሆናል የሚባል በቆላ የሚበቅል የእፅዋት አይነት::

**ሙስና[3]** ስ በስልጣን ወይም በስራ ድርሻ አላግባብ የመገልገል፥ የመጠቀም ወይም የመጥቀም ድርጊት::

**ሙሻ ዘር[1]** ስ አንድ ላይ ተጣምረው የሚነገሩ ድርብ ስሞች:: ለምሳሌ ጥርስ ወርቅ/ቤተ መፃህፍት::

**ሙሻ ዘር[2]** ስ ወጣትነት:: *ሙሻዘሩ ረገፈ::*

**ሙሻ ዘር[3]** ስ በጠመንጃ ወይም በሽጉጥ ቧንቧ ውስጥ የሚገኝ ክብ ሆኖ ክርክር ያለውና ጥይቷ ስትተኮስ እየተሽከረከረች እንድትሄድ የሚያደርግ

ነገር።

**ሙሽ** ስ በደጋማ አካባቢ የሚበቅል እንደ ቄጠማ ያለ ውስጠ ክፍት ሳር።

**ሙሽሪት** "ሞሸረ" ስር ተመ.

**ሙሽራ** ዝ.ከ.።

**ሙሽሮ** "ምሽሮ" ን ተመ.

**ሙሽት** "ሚሽ" ስር ተመ.

**ሙሾ** ስ ሰው በሞተ ጊዜ በአውራጅና በተቀባይ አማካይነት በግጥምና በዜማ እየታጀበ የሚካሄድ ለቅሶ።

**ሙሾ አውራጅ** ስ አልቃሽ፥ የለቅሶ ግጥምን በዜማ እያሰማ የሚያስለቅስ ሰው።

**ሙቀት** "ሞቀ" ስር ተመ.

**ሙቀጫ** "ወቀጠ" ስር ተመ.

**ሙቅ** "ሞቀ" ስር ተመ.

**[የ ] ሙቅ መሬት** ስ ወላጅ ከልጆቹ መሃል አንዱን በመምረጥ የሚያወርሰውና ወራሹ ከሌሎቹ ልጆች ጋር የማይካፈለው ለመኖሪያው ቅርብና ጥሩ የሆነ አነስተኛ መሬት።

**ሙታንታ (ሙታንቲ)** ስ ከቀሚስ ወይም ከሱሪ ስር የሚለበስ፥ ገላ ላይ የሚያርፍ የውስጥ ሱሪ፤ ሃፍረተ ስጋን መሸፈኛ።

**ሙት** "ሞተ" ስር ተመ.

**ሙትቻ** ዝ.ከ.

**ሙና** ቅ ቆንጆ (ለትንሽ ልጅ)።

**ሙናና** "ሚነነ" ስር "ሞናና" ን ተመ.

**ሙከራ** "ሞከረ" ስር ተመ.

**ሙክት** "ሞከተ" ስር ተመ.

**ሙክክ አለ** "ሞከከ" ስር ተመ.

**ሙዚቀኛ** "ሞዘቀ" ስር ተመ.

**ሙዚቃ** ዝ.ከ.

**ሙዚየም** ስ የተለያዩ የታሪክ፥ የስነጥበብ፥ የሳይንስ፥… ቅርሶች ተሰብስበው የሚቀመጡበትና ለህዝብ እይታ የሚቀርቡበት ቤት።

**ሙዜ** "ሚዜ" ን ተመ.

**ሙዝ** ስ ሞለል ያለና ተልጦ የሚበላ ጣፋጭ የፍራፍሬ አይነት፤ ሙዙን የሚያፈራው ተክልም ሙዝ ይባላል።

**ሙዝኝ** "ሞዘዘ" ስር ተመ.

**ሙያ (ሞያ)** ስ 1. በአንድ በተወሰነ ስራ ላይ በልምድ ወይም በስልጠና የሚገኝ እውቀት፥ ችሎታ። 2. ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚሰሩት ስራና የሚሰጡት አገልግሎት (ለምሳሌ እንደ ቅፅል፥ ስም፥… በመሆን)።

**ባለሙያ** ስ 1. በአንድ በተወሰነ ስራ ላይ በልምድ፥ በስልጠና የተገኘ እውቀት፥ ችሎታ ያለው ሰው። 2. በቤት ባልትና ጥሩ ችሎታ ያለው ሰው (ብዙውን ጊዜ ለሴት)።

**ሙያተኛ** የ "ቀን ሙያተኛ"ን ተመ.

**ሙያውን** "ዋለ" ስር ተመ.

**ሙዳ [ስጋ]** ስ እየተመጠነ የተቆረጠ የስጋ ጉማጅ፥ ቁርጥ።

**ሙዳይ** ስ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ለጌጣጌጥ፥ ለብርጉድ፥… ማስቀመጫ የሚገለገሉበት፥ በአገልግል ቅርፅ የምትሰራ አነስተኛ የስፌት እቃ።

**ሙጃ** ስ በክረምት ወራት በብዛት የሚበቅል የሳር አይነት።

**ሙጃሌ (ሞያሌ)** ስ ብዙውን ጊዜ እጅና እግር ቆዳ ውስጥ ሰርስራ የምትገባና የምታሳክክ ቁንጫ የምትመስል ተባይ።

**ሙገሳ** "*ሞገሰ" ስር ተመ.

**ሙገጫ** "ወቀጠ" ስር "ሙቀጫ"ን ተመ.

**ሙጋድ (የሙጋድ እንጨት)** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተክርስቲያን ለመስዋእት መስሪያና ለማእጠንት ፍም የሚያገለግል የማገዶ እንጨት።

**ሙግት** "ሞገተ" ስር ተመ.

**ሙግድ (ሞክድ፥ ሞግድ)** ስ አክንባሎ።

**ሙጎጎ** "ምጎጎ" ን ተመ.

**ሙጢ** "*ሞጠሞጠ" ስር ተመ.

**ሙጣጭ** "ሚጠጠ"ስር ተመ.

**ሙጥልቅ** "ሞጠለቀ" ስር ተመ.

**ሙጥኝ**

**[የ] ሙጥኝ አለ** ግ 1. አድኑኝ፥ አስጥሉኝ ብሎ ተጠጋ። 2. አልለይ አለ፥ ተቆራኘ።

**ሙጫ** "ሞጨጨ" ስር ተመ.

**ሙጫሌ** ስ ትንሽ የሆነ ጨቅላ ልጅ (ሴቷ ሙጫሊት ትባላለች)።

**ሙጭ** ስ እንደ ገና ዱላ ከጫፉ ቆልመም ያለ የጤፍ መውቂያ እንጨት።

**ሙጭራጭ** ቅ አጭርና ቀጭን የሆነ፥ ከሳሳ።

**ሙጭርጭር** "ሚጨረ" ስር ተመ.

**ሙጭጭ አለ** "ሞጨጨ" ስር ተመ.

**ሚ** የ"መ" ራደል ሳልስ ዘር።

**ሚሊ**

**ሚሊ ሊትር** ስ የፈሳሽ መጠን መለኪያ (1000 ሚሊ ሊትር 1 ሊትር ይሆናል)።

**ሚሊ ሜትር** ስ የርዝመት መለኪያ(1000 ሚሊ ሜትር 1 ሜትር ይሆናል)።

**ሚሊግራም** ስ የክብደት መለኪያ(1000 ሚሊ ግራም 1 ግራም ይሆናል)።

**ሚሊዮነር** ስ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ያለው በጣም ሃብታም ሰው::

**ሚሊዮን** ስ አንድ ሺህ ጊዜ አንድ ሺህ (በቁጥር ሲፃፍ 1,000,000 ነው)::

**ሚካኤል** ስ በፀደይ ወቅት የሚታይ የኮከብ ስም::

**ሚሲዮን (ሚሽን)** ስ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በተለየ መልክ የክርስትና ሃይማኖትን የሚከተሉና የሚያስፋፉ የውጭ ዜጎች የመሰረቱት የሃይማኖት ማስፋፊያ ድርጅት::

**ሚሳይል** ስ አንድን ነገር ለመደምሰስ የሚተኮስና ረጅም ርቀት ለመጓዝ የሚችል ተምዘግዛጊ የጦር መሳሪያ::

**ሚስማር** "ምስማር"ን ተመ.

**ሚስት (ምሽት)** ስ ከወንድ ጋር በህጋዊ ጋብቻ የተጣመረች ሴት፣ የወንድ የትዳር ጓደኛ::

**ሚስጥር** "*መስጠረ" ስር "ምስጢር"ን ተመ.

**ሚኒ** "ሚኒስከርት"ን ተመ.

**ሚኒስቴር** ስ በስሩ የተወሰኑ የስራ ዘርፎችን አካቶ የያዘና የመንግስትን ኣላማዎች፥ ህጎች፥ ደንቦችና መመሪያዎች የሚያስፈፅም የመንግስት መስሪያ ቤት:: (ለምሳሌ የባህልና ማስታወቂያ ሚኒስቴር)::

**ሚኒስትር** ስ አንድን የሚኒስቴር መ/ስሪያ ቤት ለማስተዳደርና ለመምራት በመንግስት የሚሾም ከፍተኛ ባለስልጣን::

**ሚኒስትሮች ምክር ቤት** ስ የተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፥ ሚኒስትሮች አባል የሆኑበትና በጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ የመንግስት አካል፥ ጉባኤ::

**ሚኒስከርት (ሚኒ)** ስ ከጉልበት በላይ የሚውል በጣም አጭር ቀሚስ::

**ሚና** ስ 1.ቦታ፥ ጎራ:: 2. የስራ ድርሻ::

**ሚናውን ለየ** ከሚመስለው፥ ከሚፈልገው ወገን በኩል ሆነ፣ አቋም ያዘ (በአስተሳሰብ፥ በድርጊት)::

**ሚናውን ተጫወተ** የሚጠበቅበትን የስራ ድርሻ አበረከተ::

**ሚን ሚን አለ** ግ ወዲያ ወዲህ አለ፣ ተወዛወዘ::

**ሚክሮብ** ስ በሽታን የሚያመጡና ለአይን የማይታዩ ጥቃቅን ህዋሳት::

**ሚዛን** "መዘነ"ስር ተመ.

**ሚዛን ነፉስ** ስ በመስከረም ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት፣ በተጨማሪ "ኮከብ ቆጠራ"ን ተመ.

**ሚዜ (ሙዜ)** ስ ከሙሽሮች ጎን በቅርብ በመሆን የሰርጉን ስነ ስርአት የሚያካሂድ የሙሽሮች የቅርብ ጓደኛ::

**ሚያው** ድመት ስትጮህ የምታሰማው ድምፅ::


**ሚያው አለች** (ነውር) የወሲብ ስሜቷ በመነሳሳቱ ተቅበዘበዘች፥ ተባእት ፈለገች(ለሰው)::

**ሚያው ብትል አታገኝም** ምንም ብትሞክር፥ ብትለፋ አታገኝም::

**ሚያዝያ** ስ ከመጋቢት ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ስምንተኛ ወር ስም::

**ሚዳቋ** ስ ፍየል የምትመስል አነስተኛ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)::

**ሚዶ** ስ ከእንጨት፥ ከብረት ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራ የፀጉር ማበጠሪያ::



ሚዶ

**ሚጥሚጣ** ስ 1. መጠኑ አነስተኛ የሆነና ሲበሉት በጣም የሚያቃጥል የበርበሬ ቃሪያ አይነት፣ ተክሉም ሚጥሚጣ ይባላል:: 2. ከሚጥሚጣ (ከጨው፥ ከኮረሪማና ከሌሎች ቅመማ ቅመሞች ድብልቅ ጋር ተፈጭቶ) የሚዘጋጅ ማባያ:: 3. (ዘይ.) ለፍላፊ ፥ ነገረኛ::

**ማ**[1] የ "መ" ፊደል ራብእ ዘር::

**ማ**[2] "ማን"ን ተመ.

**ማ__** "መ__" ን ተመ.

**–ማ**[1] አንድ ነገር ያለበት ወይም የበዛበት መሆኑን ለማሳየት በቃል መጨረሻ የሚቀጠል ምእላድ:: *ድንጋያማ፣ ፀሃያማ ::*

**_ማ**[2] የሚመስል ለማለት በቃል መጨረሻ ላይ የሚቀጠል ምእላድ:: *ቡናማ፣ ነብርማ::*

**ማህሌት** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በከበሮና በፀናፅል እየታጀበ በዜማ የሚባል መንፈሳዊ መዝሙር፣ ምስጋና፥ ፀሎት::

**ማህሌት ቆመ** በማህሌት ስነ ስርአት ላይ ተገኝቶ ከመዘምራኑ ጋር አብሮ ዘመረ፥ አመሰገነ::

**ማህበር** ስ 1.ተመሳሳይ እምነት ያላቸው የተወሰኑ ሰዎች በፈጣሪ ወይም በሌላ ቅዱስ ስም በየተራ እያዘጋጁ በበአሉ ቀን አንድ ላይ በመገናኘት የሚቀምሱት የፀበል ፀዲቅ ዝግጅት፥ ግብዣ::2.የተወሰነ አላማን በአንድነት ለማራመድ ተመሳሳይ ፍላጎትና አቋም ያላቸው ሰዎች

ስብስብና የተሰባሰቡበት ድርጅት (ለምሳሌ የሴቶች፥ የነጋዴዎች፥... ማህበር)።

**ማህበር ይጠጣል** የፅዋ ማህበር አለው።

**ማህበር ገባ** የማህበር አባል ሆነ።

**ማህበረሰብ** (ማህበራዊ ትስስር ያለው) በተወሰነ አካባቢ ወይም ቦታ የሚኖር ህዝብ።

**የቆሎ ማህበር** ስ የጠላ፥ የቆሎና የዳቦ ዝግጅት ብቻ የሚጠይቅ የፅዋ ማህበር።

**የእንጀራ ማህበር** ስ ድግሱ ዳቦና ጠላ ብቻ ሳይሆን እንጀራንም የሚጨምር የፅዋ ማህበር።


**የፅዋ ማህበር** የ"**ማህበር**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ማህበረተኛ** ስ የማህበር አባል።

**ማህበራዊ** ቅ 1. የህብረት፥ የጋራ። 2. የህዝብ።

**ማህደር** ስ 1. አንድን ነገር ለማስቀመጫ ተብሎ ከቆዳ ወይም ከሌላ ነገር የተበጀ ሳጥን፥ ኪስ። 2. የመፅሃፉን ቅርፅ ይዞ ከቆዳ የሚዘጋጅ ባለማንጠልጠያ የመፅሃፍ መከተቻ፥ መያዣ (ለምሳሌ የዳዊት፥ የዜማ መፅሃፍ ማህደር)። 3. አንድን ሰው ወይም አንድን ጉዳይ ብቻ የሚመለከቱ ደብዳቤዎች፥ ሰነዶች፥... የሚቀመጡበት ፋይል፥ ዶሴ።

**ማህፀን** ስ በሴትና በአጥቢ እንስሳት ሆድ ውስጥ የሚገኝ፥ ፅንስ ለማደግና በህይወት ለመቆየት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ከእናቱ እያገኘ የሚቆይበት የሰውነት ክፍል።



ማህፀን

**ማህፀነ ክፉ** የክፉ ወይም የመጥፎ ልጅ እናት።

**ማህፀነ ደግ** ጥሩ ጠባይ ያለው ወይም የደግ ልጅ እናት።

**ማህፀኗ ተዘጋ/ተደፈነ** 1. እንዳትወልድ ተደረገች። 2. መከነች።

**ማህፀኗ ተፈታ** መውለድ ቻለች።

**ማለ** ግ 1. የተናገረው እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ወይም ለማሳመን እንዲህ ያድርገኝ፥ እንዲህ ይድረስብኝ ወይም እገሌ ይሙት፥... አለ። 2. አንድን ነገር ደግሜ አላደርግም በማለት በሚያመልከው ወይም በሚወደው ስም ተገዘተ፥ እርም አለ፥ ቃል ገባ።

**ማላ (መሃላ)** ስ አንድ ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ፥ ለማሳመን እንዲህ ያድርገኝ፥ እንዲህ ይድረስብኝ፥ እገሌ ይሙት፥... በማለት ወይም አንድን ነገር ደግሜ አላደርግም በማለት በሚያመልኩት ወይም በሚወዱት ስም፥... የሚገባ ቃል።

**ማላ አፈረሰ** አላደርግም ወይም አደርጋለሁ ብሎ በመሃላ የሰጠውን ቃል ተወ፥ አፈረሰ።

**ማላ ፉቴ** በሆነ ባልሆነው በሃሰት የሚምል፥ መሃላ የማይፈራ።

**ማለኛ** ቅ ማላ የሚያበዛ።

**ማለለ** ግ ለመነ፥ ተማፀነ (ብዙውን ጊዜ በፀሎት)።

**ተማለለ** ዝ.ከ.

**ማለቂያ** "**አለቀ**" ስር ተመ.

**ማለት** "**አለ**" ስር ተመ.

**ማለኛ** "**ማለ**" ስር ተመ.

**ማለዋወጫ** "**ለወጠ**" ስር ተመ.

**ማለደ**[1] ግ በጠዋት ተነሳ።

**ማለዳ** ስ በጣም ጠዋት።

**ማላጅ** ቅ በጠዋት መነሳት የሚወድ፥ የሚያዘወትር።

**ማለደ**[2] ግ ለመነ፥ ደጅ ጠና።

**መማለጃ** ስ ጉቦ፥ እጅ መንሻ።

**ምልጃ** ስ ልመና፥ ደጅ ጥናት።

**ተማለደ** ግ ተለመነ፥ ይቅር አለ።

**አማለደ** ግ 1. አስታረቀ፥ ሸመገለ። 2. አንዱ ለሌላው ተለማኙ ለለማኙን ይቅርታ እንዲያደርግ ወይም የሚፈልገውን ጉዳይ እንዲፈፅምለት በለማኙ ስም ከተለማኙ ጠየቀ፥ ለመነ (ሶስተኛ ወገን በመሆን)።

**አማላጅ** ስ 1. አስታራቂ፥ ሽማግሌ። 2. አንዱ ለሌላው (ተለማኝ ለለማኝ) ይቅርታ እንዲያደርግ ወይም የሚፈልገውን እንዲፈፅምለት በለማኙ ስም ተለማኙን የሚጠይቅ፥ የሚለምን ሶስተኛ ወገን።

**ማለዳ** "**ማለደ**[1]" ስር ተመ.

**ማለገ** ግ 1. ተዝለገለገ፥ ተሳበ (ፈሳሽነት ያለው ነገር)። 2. (ዘይ. ፥ስድብ) ማገጠ፥ ተሞላፈጠ።

**ማላጋ** ቅ 1. ዝልግልግ ያለ፥ የሚሳብ (ፈሳሽነት ያለው ነገር)። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ማጋጣ፥ ሞልፋጣ።

**ማለፊያ** "**አለፈ**" ስር ተመ.

**ማላ** "**ማለ**" ስር ተመ.

**ማላሻ** "**ላሰ**" ስር ተመ.

**ማላቀቂያ** "**ለቀቀ**" ስር ተመ.

**ማላበሻ** "ለበሰ" ስር ተመ.
**ማላጅ** "ማለደ[1]" ስር ተመ.
**ማላጋ** "ማለገ" ስር ተመ.
**ማልቀሻ** "*ለቀሰ" ስር ተመ.
**ማልድያ (ማልደያ)** ስ ገዳዮች (ኣዳኞች) በእጃቸው ያደርጉት የነበረ ከመዳብ ወይም ከነሃስ÷... የሚሰራ የግዳይ ምልክት÷ ኣምባር።
**ማመላለሻ** "መለሰ" ስር ተመ.
**ማመልከቻ** "*መለከተ" ስር ተመ.
**ማማ** ስ ለጥበቃ ወይም ኣካባቢውን ለመቃኘት እንዲያመች ተብሎ በሰብል÷ በኣዝመራ÷... መሃከል የሚተከል ረዥም ቆጥ።
**ማማሰያ** "መሰለ" ስር ተመ.
**ማማት** "ህማማት" ን ተመ.
**ማምለኪያ** "መለከ"ስር ተመ.
**ማምለጫ** "*መለጠ" ስር ተመ.
**ማምረቻ** "መረተ[1]" ስ ስር ተመ.
**ማምሻ** "መሸ" ስር ተመ.
**ማሚጠጫ** "ሚጠጠ" ስር ተመ.
**ማሚጫ** " ሚጨ" ስር ተመ.
**ማረ** ግ በማዘን ወይም በመራራት ይቅር ኣለ÷ ተወ÷ ምህረት ኣደረገ (በደልን÷ እዳን)።
**መሃሪ (ማሪ)** ቅ ይቅር ባይ÷ ምህረት የሚያደርግ።
**ምህረት (ምረት)** ስ ይቅርታ።
**ማረሚያ** "ኣረመ" ስር ተመ.
**ማረሚያ ቤት** ዝ.ከ.
**ማረረ** ግ ዞሮ ለመነ÷ ቃረመ።
**ማራሪ** ቅ ቃራሚ÷ ለማኝ።
**ማረሳሻ** "ረሳ" ስር ተመ.
**ማረሻ** "ኣረሰ[1]" ስር ተመ.
**ማሪሻ** "ኣረሰ[2]" ስር ተመ.
**ማረበላ** "ማር" ስር ተመ.
**ማረከ** ግ 1. በጦርነት ወይም በውጊያ ላይ ጠላቱን በቁጥጥር ስር ኣደረገ። 2. በምርኮ ወሰደ። 3. መሰጠ÷ ሳበ።
**ምርኮ** ስ በጦርነት ጊዜ በቁጥጥር ስር የዋለ የጠላት ወታደር÷ መሳሪያ÷ ንብረት።
**ምርኮኛ** ቅ 1. በጦርነት÷ በውጊያ ላይ በቁጥጥር ስር የዋለ የጠላት ወገን። 2. (ዘይ.) በኣንድ ነገር ፍቅር የተያዘ÷ የተጠመደ።
**ማረፊጅ** "ማር" ስር "ማረበላ"ን ተመ.
**ማረፊያ** "ኣረፈ" ስር ተመ.
**ማሪ** "ማረ" ስር "መሃሪ"ን ተመ.

**ማራምጣ** "ማርኣምጣ" ን ተመ.
**ማራሪ** "ማረረ" ስር ተመ.
**ማራቶን** ስ ከ42 ኪሎ ሜትር ጥቂት በለጥ የሚል ርቀት የሚሸፍን ከኣለም ኣቀፍ ኦሎምፒክ የሩጫ ውድድሮች መካከል ኣንዱ።
**ማራገቢያ** "*ረገበ" ስር ተመ.
**ማር** ስ ንቦች ኣበባን በመቅሰም የሚያዘጋጁትና ወፍራም ፈሳሽ የሆነ ጣፋጭ ነገር። 2- (ዘይ.) ጣፋጭ÷ ደስ የሚል ÷ የሚጥም።
**ማር ቆረጠ** ማርን ከቀፎው ውስጥ በስለት እየቆረጠ ኣወጣ።
**ማር ተላሰ** በበሰለ ወይም በኮመጠጠ ጠላ ወይም በደረቀ ጠጅ ውስጥ ጠላውን ወይም ጠጁን ለማደስ ሲባል ማር ተጨመረበት።
**ማር ነው** ይጣፍጣል፤ ቆንጆ÷ ጥሩ ነው።
**ማር ማር ኣለ** ጣፈጠ።
**ማርም ኣልስ** በቃኝ÷ ጠግቤኣለሁ÷ ከዚህ በላይ ምንም ኣልጨምርም።
**ማረበላ (ማረፊጅ)** ስ ማር የሚበላ ቀይ ጉንዳን።
**ማርማሽላ** ስ ባር ማሽላ፤ በቆሎ።
**የማር ልጅ** ስ የጡት ልጅ።
**የማር እሸት** ስ 1. ኣዲስ የተቆረጠ ትኩስ ማር። 2. በሰው መሬት ላይ ቀፎውን የሰቀለ ሰው ለባለ መሬቱ የሚሰጠው ማር።
**የማር እንጀራ** ስ ንቦች የሚጋግሩት (የሚያዘጋጁት) እንደእንጀራ ኣይን ያለው የማሩ ግግር።



የማር እንጀራ

**ማርመላታ** ስ እንደብርቱካን ወይም ሎሚ ወይም እንጆሪ÷... የመሳሰሉ ፍራፍሬዎችን ከስኳር ጋር ደባልቆ እስኪለደልድ በመቀቀል የሚዘጋጅ የዳቦ ማባያ።
**ማርመጃ** "ኣረመደ" ስር ተመ.
**ማርስ** ስ ከፀሃይ ጀምሮ ሲቆጠር በርቀት ኣራተኛ ሆና የምትገኝና በፀሃይ ዙሪያ ከሚሽከረከሩት ኣለማት ወይም ፕላኔቶች ኣንዷ።("ፕላኔት"ን ተመ.)።
**ማርሻል** ስ ከጀኔራል በላይ የሆነ ከፍተኛው

የወታደራዊ ማእረግ ስም።

**ማርሽ[1]** ስ የተሽከርካሪን ፍጥነት ለመለዋወጥ የሚያስችል ጥርሶች ያሉት የተሽከርካሪ ክፍል።

**ማርሽ[2]** ስ በአንድ ወታደራዊ ክፍል ውስጥ የሚገኝ የሙዚቃ ባንድ፥ የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም በህብረት የሚጫወተው ሙዚቃ።

**ማርትሬዛ** ስ ማሪያ ቴሬዛ በተባለችው የነምሳ (ኦስትሪያ) ንግስት ስም በኦስትሪያ የተሰራ፥ በ19ኛው መቶ አመትና በ20ኛው መቶ አመት መጀመሪያ በኢትዮጵያ ይሰራበት የነበረ የመገበያያ ገንዘብ፤ ጠገራ ብር።

**ማርኣምጣ (ማራምጣ)** ስ መንታ ጫፍ ያለው አለንጋ።

**ማርከሻ "ረከሰ"** ስር ተመ.

**ማርክ** ስ ለፈተና ውጤት የሚሰጥ ነጥብ።

**ማርክሲዝም** ስ በካርል ማርክስና በፍሬድሪክ ኢንግልስ የተቀመረ የሶሻሊዝም ፍልስፍና።

**ማርክሲዝም ሌኒኒዝም** ስ በካርል ማርክስና በፍሬድሪክ ኢንግልስ የተቀመረና በሂላ በሌኒን የዳበረ የሶሻሊዝም ፍልስፍና።

**ማርያም (ድንግል ማርያም)** ስ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት።

**ማርያም በሽልም ታውጣሽ** (ምር.) ጠያቂዎች አራስ ሴትን ጠይቀው በሚወጡ ጊዜ ከአራስ ቤት በደህና አምረሽ ውጭ በማለት ለአራሷ የሚመኙላት የመልካም ምኞት መግለጫ።

**ማርያም ጭንሽን ታሙቀው** (ምር.) አራስ ሴት የአራስነት ጊዜዋን ጨርሳ በድጋሚ ለወሲባዊ ግንኙነት ብቁ እንድትሆን በመመኘት የሚነገር የመልካም ምኞት መግለጫ።

**ማርያም የሳመችው** በሰውነት ላይ በተፈጥሮ ጥቁር ሆኖ የሚገኝ እንደነጥብ ያለ አነስተኛ ምልክት።

**በማርያም እጅ ተይዛለች** እርጉዝ ነች።

**የማርያም መቀነት** ስ ቀስተዳመና።

**የማርያም ምሳ** ስ ሴት ስትወልድ የምትበላው የመጀመሪያው ገንፎ።


**የማርያም ስፌት** ስ ከብልት በታች ከፊንጢጣ በላይ የሚገኝ የተሰፋ የሚመስል የሰውነት ክፍል።

**የማርያም ዘንግ** ስ ቸርንችር፥ በትረሙሴ (በተለይ መነኩሲቶች እንደምርኩዝ ወይም እንደ መቋሚያ የሚጠቀሙበት የእፅዋት አይነት)።

**የማርያም ግርዝ** ስ በተፈጥሮው የተገረዘ ሆኖ የሚገኝ የሴት ብልት።

**የማርያም ጠላት** ስ 1.አባጨጓሬ። 2. (ዘይ.) ሰው ሁሉ የሚጠላው ወይም ሰው ሁሉ ተሰብስቦ የሚደበድበው ሰው።

**የማርያም ፈረስ** ስ ከአንበጣ አነስ የሚልና ፌንጣ የሚመስል ነፍሳት።



የማርያም ፈረስ

**ማርዬ** ስ ከፊንጣጣ በሽታ አይነቶች የአንዱ ስም።

**ማርዳ** ስ ከብርና ከብርጭቆ መሰል ጌጥ የሚሰራ የልጆች የአንገት ጌጥ።

**ማርገብገቢያ "*ረገበ"** ስር ተመ.

**ማርገጃ "ረገደ"**ስር ተመ.

**ማርጋሪን** ስ ቅባትነት ካለው ስጋ ወይም ከአትክልት የሚሰራ ቅቤ።

**ማርጣ** ስ የዝሆን ጭራ።

**ማስ** ግ ቆፈረ፥ ጉድጓድ አበጀ።

**ማሳ** ስ የታረሰ መሬት፥ እርሻ።

**ማስሮ** ስ ለውሃ ማሞቂያ፥ ለንፍሮ መቀቀያ፥... የሚያገለግል የሸክላ እቃ፤ ምንቸት፤ ቶፋ (ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.)።

**ማሰሻ** ስ **"አሰሰ"** ስር ተመ.

**ማሰነ** ግ ለፋ፥ ደከመ።

**ማሲንቆ(መሰንቆ)** ስ ከእንጨት፥ ከፍየል ቆዳና ከፈረስ ጭራ የሚሰራ ባለአንድ ክር ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**ማሳ "ማሰ"** ስር ተመ.

**ማሳሰቢያ "አሰበ"** ስር ተመ.

**ማስለቀሻ "*ለቀሰ"** ስር ተመ.

**ማስለቀቂያ "ለቀቀ"** ስር ተመ.

**ማስመሪያ "*ሰመረ"** ስር ተመ.

**ማስረጃ "*ረዳ"** ስር ተመ.

**ማስተንፈሻ "ተነፈሰ"** ስር ተመ.

**ማስተዛዘኛ "አዘነ"** ስር ተመ.

**ማስቲካ "መስቲካ"** ን ተመ.

**ማስታወሻ "*ታወሰ"** ስር ተመ.

**ማስታወቂያ "አወቀ"** ስር ተመ.

**ማስታገሻ** "ታገሰ" ስር ተመ.

**ማስገንዘቢያ** "*ገነዘበ" ስር ተመ.

**ማስጠንቀቂያ** "ጠነቀቀ" ስር ተመ.

**ማስጫ** "*ሰጣ" ስር ተመ.

**ማስፈራሪያ ፊት** "ፈራ" ስር ተመ.


**ማሻሻያ** "*ሻለ" ስር ተመ.

**ማሽላ** ስ የፍሬው ቅርፅ ዘንጋዳ የሚመስልና የሚያክል ለእንጀራ÷ ለንፍሮ÷ ለጠላ የሚሆን በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል የአገዳ እህል::

**ማሽን** ስ 1. አንድን ተግባር በቀላሉና በፍጥነት ለማከናወን የሚያስችል÷ በነዳጅ÷ በኤሌክትሪክ÷... ሃይል የሚንቀሳቀስ ዘመናዊ መሳሪያ (ለምሳሌ የሹራብ መስሪያ÷ የጫማ መስፊያ ማሽን):: 2. ለዚህ ስራ ተብሎ በተዘጋጀ መሳሪያ ሽብሽቡ ከካውያ ስፌት ይበልጥ ጥቅጥቅ ብሎ የተሰራ ጉርድ ወይም ሙሉ ቀሚስ::

**ማሽንክ** ስ ሽረኛ÷ ተንኮለኛ÷ መሰሪ::

**ማሾ** ስ እንደፋኖስ ያለ ሆኖ ብርሃኑ ግን ከፋኖስ የሚበልጥ÷ በነጭ ጋዝ የሚሰራ መብራት::



ማሾ

**ማቀቀ** ግ በበሽታ÷ በችግር÷... ተሰቃየ÷ መከራ አየ::

**ማቀባበያ** "*ቀበለ" ስር ተመ.

**ማቀናነሻ** "ቀነሰ" ስር ተመ.

**ማቀዝቀዣ** "ቀዘቀዘ" ስር ተመ.

**ማቀፊያ** "አቀፈ" ስር ተመ.

**ማቁላሊያ** "ቆላ[1]" ስር ተመ.

**ማቁረጫ** "ቆረጠ" ስር ተመ.

**ማቅ** ስ ከጥቁር በግ ፀጉር ተፈትሎ የሚሰራ እንደ ብርድ ልብስ ያለ ልብስ::

**ማቅ ለበሰ** ራሱን በመጉዳት÷ በማጎሳቆል በጣም አዘነ::

**ማቅረቢያ** "ቀረበ" ስር ተመ.

**ማቋቻ** "ቋተ" ስር ተመ.

**ማበረታቻ** "በረታ" ስር ተመ.

**ማበቻ** "አበተ[1]" ስር ተመ.

**ማበጠሪያ[1]** "*በጠረ[1]" ስር ተመ.

**ማበጠሪያ[2]** "*በጠረ[2]" ስር ተመ.

**ማቡኪያ** "በካ" ስር ተመ.

**ማባበያ** "*ባበለ" ስር ተመ.

**ማባዛት** "በዛ" ስር "ማብዛት"ን ተመ.

**ማብረጃ** "በረደ" ስር ተመ.

**ማብሪያና ማጥፊያ** "በራ" ስር ተመ.

**ማብራሪያ** ዝ.ከ.

**ማብሰያ** "በሰለ" ስር ተመ.

**ማብዛት** "በዛ" ስር ተመ.

**ማተሚያ** "አተመ" ስር ተመ.

**ማተረ** ግ 1. ቃኘ÷ ዙሪያውን አየ:: 2. አሻግሮ አየ÷ ተመለከተ::

**አማተረ** ግ አሻግሮ አየ÷ ተመለከተ::

**ማተብ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) አንድ ሰው ክርስትና ሲነሳ ለሃይማኖት ምልክትነት በአንገቱ ላይ የሚያስረው ክር::

**ለማተቡ ሲል** ለሃይማኖቱ÷ ለእምነቱ ሲል::

**ማተቡን በጠሰ** 1. ካደ÷ እምነት አጎደለ:: 2. ሰለመ::

**ማተበ ቢስ** እምነተ ቢስ÷ ከሃዲ::

**ማተብ የለሽ** ዝ.ከ.

**ማቲ** ስ ብዛት ያላቸው ትንንሽ ልጆች ፤ ውሪ::

**ማታ** ስ ጀንበር ከጠለቀችበት አንስቶ እስከ ምሽቱ አምስት ሰአት ገደማ ያለው የጨለማ ጊዜ::

**የማታ ማታ** የሂላ ሂላ÷ በስተመጨረሻ::

**የማታ ትምህርት** ስ በትምህርት ቤት ውስጥ ማታ ማታ የሚሰጥ ትምህርት::

**የማታ እንጀራ** እድሜ ከገፋ በኋላ የሚገኝ ሃብት÷ ንብረት::

**ማታለያ** "*ታለለ" ስር ተመ.

**ማትሪክ** ስ የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ብሄራዊ ፈተና::

**ማቶት** ስ ክብ ሆኖ የተሰራ የእንስራ ወይም የጀበና÷...መቀመጫ::

**ማነቆ** "አነቀ" ስር ተመ.

**ማን (ማ)** ተው.ስ. 1. የትኛው ሰው ብሎ ለመጠየቅ የሚያገለግል ቃል:: *ማን መጥቶ ነበር?* 2. መጠሪያ ስምን መጠየቂያ ቃል:: *ስምህ ማን ነው? ዛሬ ማን ነው?*

**ማን ላከብኝ** ማን ሰደደብኝ÷ አዘዘብኝ (መጥፎ ነገር ወይም ጉዳት እንዲያደርስብኝ)::

**ማንአለብኝነት** ከኔ በላይ ማንም የለም÷ ማን ያዘኛል፣ ማን ይደፍረኛል ባይነት÷ ትእቢተኝነት::

**ማን አባቱ(ማናባቱ)** የትኛው÷ እንዴት ያለው ጎበዝ ለማለት የሚሰነዘር የንቀት÷ የማስፈራሪያ÷ የድንፋታ አባባል::

**ማንዘራሽ** 1. (ስድብ) የመጣበትና የወለደው ሰው የማይታወቅ÷ ምናምንቴ ብሎ ሰውን ለማኮሰስ የሚሰነዘር የንቀት አነጋገር:: 2. መደዴ÷ ዱርዬ፣ ስነስርአት የጎደለው::

**ማናቸውም(ማንኛቸውም)** አንዳቸውም::

*ማናቸውም መሄድ አይፈልጉም።*

**ማንም** 1. የትኛውም፥ ማንኛውም፤ ሁሉም። 2.የማይታወቅ ሰው። *ማንም በወሰደው እኔ አልጠየቅም።* 3. ተራ ሰው፥ መደዴ። *ማንም ተነስቶ ላዋቂ ነኝ ይላል።*

**ማንም የለም** አንድም ሰው የለም።

**ማንትስ (ማንትሴ)** ተው.ስ. በአደናጋሪና አሊታወስ ባለ ስም ምትክ በመግባት የሚያገለግል ቃል።

**ማንነት** ግለሰባዊ ምንነት (በባህርይ፥ በጠባይ፥ በችሎታ፥...)።

**ማንነቱ ያልታወቀ** ማን መሆኑ ያልታወቀ።

**ማንነቴን አሳይሃለሁ** ሃይሌን ወይም ችሎታዬን፥... አሳይሃለሁ፤ እንድታውቅ አደርግሃለሁ።

**ማንኛቸው (ማናቸው)** ከሁለቱ ወይም ከብዙዎቹ ውስጥ የትኛው።

**ማንኛቸውም** ማናቸውም።

**ማንኛው** የትኛው፥ የቱ።

**ለማንኛውም** 1. ማንንም ሳይለይ፥ ለሁሉም። *ለማንኛውም ሰው ይሸጣል።* 2. ቢሆንም ባይሆንም፥ ለሁሉም። *ለማንኛውም ሄደን ማየቱ ይሻላል።*

**በማንኛውም መንገድ** በየትኛውም አይነት፥ ሁኔታ።

**ማንቀርቀቢያ "*ቀረቀበ"** ስር ተመ.


**ማንቁርት** ለ በሰዎች ጉሮሮ (በተለይ በወንዶች) ላይ በውጭ በኩል እንደ ጉጥ ወጣ ብሎ የሚታየው የሰውነት ክፍል (ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።

**ማንቁርቱን ያዘው** በሃይል አስጨንቆ ያዘው፥ አስገደደው (አንድን ነገር እንዲፈፅም)።

**ማንቁርታም** ቅ ማንቁርቱ ትልቅ የሆነ ሰው።

**ማንቆርቆሪያ "*ቆረቆረ"** ስር ተመ.

**ማንኪያ** ለ ከብረት ወይም ከእንጨት ወይም ከነሃስ ወይም ከፕላስቲክ፥... በአንድ በኩል እጀታ ኖሮት በሌላ በኩል ቀነፍና ጎድጎድ እንዲል ተደርጎ የተሰራ ለመቆንጠሪያ፥ ለመመገቢያ፥ ለመለወሻ፥... የሚያገለግል እቃ።



ማንኪያ

**ማንደጃ "ነደደ"** ስር ተመ.

**ማንገቻ "አነገተ"** ስር ተመ.

**ማንጎ** ለ በውስጡ ጠፍጠፍ ያለ ጠንካራ ፍሬ ያለው፥ እንደኮክ ተልጦና ተግጦ የሚበላ ጣፋጭ ፍሬ፤ ማንጎውን የሚያፈራው ተክልም ማንጎ ይባላል(ስእሉን ፍራፍሬ ስር ተመ.)።

**ማንጓጠጥ "*ጓጠጠ"** ስር ተመ.

**ማኛ [ጤፍ]** ለ በጣም ነጭ የሆነ ጤፍ።

**ማእረግ** ለ 1. ሹመት፥ ስልጣን፥ ደረጃ። 2. ክብር።

**ማእረገቢስ** ውርደት እንጂ ክብር የማይወድ፤ ክብረቢስ።


**ማእረግ እሌቱ** ዝ.ከ.

**ማእበል** ለ ሃይለኛ ነፋስ በባህር፥ በውቅያኖስ፥... ላይ የሚፈጥረው የውሃ መናወጥ፤ ሞገድ።

**ማእከላዊ "*ማከለ"** ስር ተመ.

**ማእከል** ዝ.ከ.

**ማእዘን** ለ 1. የግድግዳ መጨረሻ ወይም መታጠፊያ ጥግ ወይም የግድግዳዎቹ መገናኛ። 2. ሁለት መስመሮች የሚገናኙበት ቦታ። 3. አራት ገፅ ያለው ወፍራም ጥርብ እንጨት። 4. አቅጣጫ (ምስራቅ፥ ምእራብ፥ ሰሜን፥ ደቡብ)።



ማእዘን

**የማእዘን ምት** ለ (ስፖ.) በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ፥ ኳስ በራስ ግብ አካባቢ ከግራው የማእዘን መታጠፊያ እስከ ቀኙ የማእዘን መታጠፊያ ባለው መስመር፥ በራስ ተጫዋቾች ወደ ውጪ ሲወጣ ለተቃራኒው ቡድን የሚሰጥ የቅጣት ምት።

**ምእዙን** ቅ አራት ማእዘንነት ያለው።

**ማእድ(ማድ)** ለ ለመብል የቀረበ ምግብ እስከ ማቅረቢያው፤ ገበታ።

**ማእድ ረገጠ** አብሮ ሲበላ ቆይቶ ማእዱ ሳይነሳ አቋርጦ ተነሳ፥ ሄደ።

**ማእድ ወርዷል** ምግብ ቀርቧል።

**ማእድ(ማድ) ቤት** ለ ምግብ የሚዘጋጅበት፥

የሚበስልበት ቤት፣ ኩሽና።

**ማደኛ** ስ ብዙ ጊዜ አብሮ የሚበላ የቅርብ ጓደኛ።

**ማእድን** ስ እንደወርቅ፥ ብር፥ ነሃስ፥ ብረት፥... ያለ ከመሬት ውስጥ የሚገኝ ንጥረ ነገር።

**ማእዶት** ስ በፋሲካ ማግስት የሚውለው ሰኞ።

**ማእጠንት "አጠነ"** ስር ተመ.

***ማከለ**

**መካከል (መሃከል፥ መሃል)** ቅ 1.አንድ ክብነት ያለው ነገር ከተለያዩ ጫፎች ወደ ውስጥ ሲለካ ሁሉም ጫፎች እኩል ርቀት ላይ የሚገናኙበት ቦታ። 2. የአንድ ነገር አጋማሽ፥ አማካይ ቦታ። 3. ጻር ያልሆነ፣ በሌሎች ጣልቃ ያለ።

**በመሃሉ (በመካከሉ)** 1. አንድ ነገር በመከናወን ወይም በመካሄድ ላይ እያለ። *ስብሰባው እየተካሄደ በመሃሉ ተነስቶ ሄደ።* 2. በጣልቃ። *በመሃሉ (በመካከሉ) ነጭ ያለበት ቢጫ ጨርቅ።* 3. ከሁለት የተለያዩ ወይም ተቃራኒ ወገኖች በኩል ሳይሆን፥ በተገኘው አጋጣሚ። *እነሱ ሲጣሉ በመሃሉ እሱ ተጠቀመ።*

**በመሃል ቤት** ከሁለት የተለያዩ ወይም ተቃራኒ ወገኖች ወይም ጉዳዮች በኩል ሳይሆን፥ በመሃል።

**መሃል ራስ** ስ አናት፥ እርግብግቢት።

**መሃል ሰፋሪ** ቅ ከተቃራኒ ወገኖች ያንደኛውንም አቋም የማይከተል ወይም የማይደግፍ፥ ገለልተኛ፥ ከሁለቱም ያልወገነ።

**መሃል አገዳ** ስ 1. መሃል አጥንት (የቅልጥም፥ የጭን፥ የክንድ)። 2. በፊት እግር ቅልጥም መሃል ላይ የሚገኝ የከብት ስጋ።

**መሃል እጅ** ስ በመዳፍና በጣት መካከል ያለው ውስጠኛው የእጅ ክፍል።

**መሃል ዳኛ** ስ ችሎት ላይ ሆነው ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ በግራና በቀኝ ዳኞች መካከል የሚቀመጥና በስልጣን ከሁለቱ ዳኞች የሚበልጥ ዳኛ።

**መካከለኛ (መሃከለኛ)** ቅ 1.በመካከል የሚገኝ ወይም ያለ። 2. አይነቱ ወይም መጠኑ ወይም ሁኔታው፥... ከፍተኛ ያልሆነ ወይም ያልበዛ ወይም ያላነሰ፣ መጠነኛ።

**ማእከል** ስ 1. የተለያዩ እንቅስቃሴዎችና ተግባራት በከፍተኛ ደረጃ የሚከናወንበት ቦታ። *የንግድ ማእከል።* 2. ተቋም። *የባህል ማእከል፣ የጤና ማእከል።*

**ማእከላዊ** ቅ 1. ለተለያዩ ወገኖች የጋራ የሆነ። 2. ለተለያዩ ወገኖች የበላይ የሆነ።

**ማእከላዊ መንግስት** ስ የተለያዩ አስተዳደሮችን፥ የፌዴራል ግዛቶችን፥... በበላይነት የሚያስተዳድር ወይም የሚመራ የአንድ አገር መንግስት።

**ማእከላዊ አሰራር** ስ ለተለያዩ ወገኖች የጋራ የሆነና አንድ አይነት መስመር የተከተለ አሰራር።

**ተማከለ** ግ የተለያዩ ድርጅቶች፥ አካላቶች፥... አሰራር በአንድ አይነት የበላይ አመራር ስር እንዲውል ተደረገ።

**አማከለ** ግ በሁለት የተለያዩ ወይም ተቃራኒ ነገሮች መሃል እንደ አገናኝ፥ አዛማጅ፥... ሆኖ ተገኘ፥ በመሃል ሆነ።

**አማካይ** ቅ 1. ለሁሉም የጋራ የሆነ፥ በመሃል ያለ። 2. አጋማሽ።

**በ___ አማካይነት** 1. በ___ ምክንያት። *በቫይረስ አማካይነት የሚመጣ በሽታ።* 2.በ___ በኩል። *በወንድሙ አማካይነት ጉዳዩ ተፈፀመለት።*

**ማከፋፈያ "ከፈለ"** ስር ተመ.

**ማኩታ** ስ 1. ስእለት፥ መማለጃ። 2. መቆያ፥ መክሰስ።

**ማኪያቶ** ስ መጠኑ በርከት ባለ የፈላ ቡና ውስጥ ትንሽ ወተት ተደባልቆበት የሚዘጋጅ የመጠጥ አይነት።

**ማካፈል "ከፈለ"** ስር ተመ.

**ማክሰኞ** ስ በሰኞና በረቡእ መካከል ያለው ቀን ስም፣ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ ሶስተኛ ቀን።

**ማኮብኮቢያ "*ኮበኮበ"** ስር ተመ.

**ማወራረጃ "ወረደ"** ስር ተመ.

**ማዋለጃ ክፍል "ወለደ"** ስር ተመ.

**ማውጫ "ወጣ"** ስር ተመ.

**ማዘንት** ስ ክብ ሆኖ ከጭቃ የሚሰራ አመድ አቃፊ የምድጃ ዙሪያ።

**ማዘያ "አዘለ"** ስር ተመ.

**ማዘዣ "አዘዘ"** ስር ተመ.

**ማዘጋጃ ቤት "*ዘገጀ"** ስር ተመ.

**ማዝ "አይን"** ስር **"አይነ ማዝን"** ተመ.

**ማዞሪያ "ዞረ"** ስር ተመ.

**ማዥራት "ማጅራት"** ን ተመ.

**ማይል** ስ የርቀት መለኪያ። *አንድ ማይል 1.6 ኪሎሜትር ያህል ነው።*

**ማይም "መሃይም"** ን ተመ.

**ማይካ** ስ እንደሳህን፥ ኩባያ፥ ባልዲ ያሉትን ቁሳቁሶች ለመስራት የሚያገለግል፥ መለመጥና ብርሃን ማሳለፍ የሚችል ጥሬ እቃ።

**ማይክሮስኮፕ** ስ በጣም ጥቃቅንና ረቂቅ የሆኑ

ነገሮችን አጉልቶ የሚያሳይ መነፅር።

**ማደሪያ** "አደረ" ስር ተመ.

**ማደሪያ መሬት** ስ በቀድሞ የመሬት ስሪት ስርአት ውስጥ መተዳደሪያ እንዲሆን ለንጉስ አገልጋዮች ከንጉስ ይሰጥ የነበረ፥ አፅመ ርስት ያልሆነ መሬት።

**ማደንዘዣ** "ደነዘዘ"[1]ስር ተመ.

**ማደኛ** "ማእድ" ስር ተመ.

**ማደያ** "አደለ" ስር ተመ.

**ማደጎ** "አደገ" ስር ተመ.

**ማዳበሪያ** "ዳበረ" ስር ተመ.

**ማዳወሪያ** "ደወረ" ስር ተመ.

**ማድ** "ማእድ" ስር ተመ.

**ማድቤት** ዝ.ከ.

**ማድያት** ስ የፊት ቆዳን የተፈጥሮ ቀለም የሚለውጥና የሚያጠቁር በሽታ።

**ማድጋ** ስ 1. ከእንስራ ከፍ ከጋን አነስ የሚል የሸክላ እቃ። 2. አስር ቁና ያህል የሚይዝ የእህል መስፈሪያ፥ መለኪያ።

**ማዶ** ስ 1. በወዲያ በኩል (ከወንዝ፥ ከተራራ፥...) አልፎ ወይም ተሻግሮ ያለ ቦታ። 2. ራቅ ብሎ ያለ ቦታ።

**ማጀት** ስ ብዙ ጊዜ በአነስተኛ ጎጆ ቤቶች ውስጥ በመከታ የተከለለ የእቃ መቀመጫ፤ ጓዳ።

**ማጅራት (ማዥራት)** ስ የአንገት ሂላ ክፍል፤ ደንደስ። (ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።

**ማጅራት መቺ** ቅ ብዙውን ጊዜ በጨለማ ቦታ አድፍጦና ደብድቦ የሚዘርፍ ቀማኛ።

**ማገ** ግ 1. ስቦ፥ ምጥጥ አድርጎ ጠጣ። 2. ወደ ውስጥ ሳበ፥ አስገባ (ለምሳሌ አየርን)። 3. ፈሳሽ ነገርን መጠጠ፥ ያዘ፤ ራሰ።

**አማገ** ግ 1. ምግብ በሚበላበት ጊዜ የሚጠጣ ነገርን (ውሃ፥ ወተት፥...) ፋት እያለ ተመገበ።

**ማገረ** ግ ለግድግዳ፥ ለአጥር ተብሎ በቆመ እንጨት ላይ ማገርን በገመድ፥ በልጥ፥... በማሰር ወይም በምስማር በመምታት አያያዘ።

**ማገር** ስ በግድግዳ፥ በአጥር፥... ላይ አግድም የታሰረ ወይም በምስማር ወይም በሌላ ነገር የተያያዘ እንጨት፥ ብረት፥...።

**ተማገረ** ግ በማገር ታሰረ (ግድግዳ፥ጣራ፥...)።

**ማገደ** ግ 1. እሳት ውስጥ ከተተ፥ አነደደ። 2. ለአደጋ ወይም ለችግር ዳረገ።

**ማገዶ** ስ ለማብሰል፥ ለመቀቀል፥... የሚነድ እንጨት፥ ኩበት፥ ከሰል፥...።

**ማገገሚያ** "*ገገመ" ስር ተመ.

**ማገጠ** ግ 1. ባለገ፥ ተበላሸ፥ ዋልጌ ሆነ።2. አመነዘረ። 3. ጥሩ ሆኖ ሳይታረስ ቀረ (መሬት)።

**አማገጠ** ግ 1. ስራፊት አደረገ፥ አሰነፈ፤ አባለገ፥ አበላሸ። 2. ወሲብ ፈፀመ፥ ወሸመ፥ አባለገ።

**ማገጥ** ስ መጠኑም ሆነ ቅጠሉ እንደ አብሽ ያለ፥ አብዛኛውን ጊዜ ከሳር ጋር አብሮ የሚበቅል፥ ፍሬው በደንብ ከመብሰሉ በፊት ከብቶች ከበሉት ሆዳቸውን የሚነፋና ለሞት የሚያደርስ የእፅዋት አይነት።

**ማጉሊያ** "ጎላ[1]" ስር ተመ.

**ማግ** ስ 1. በእጅ እየተፈተለ በእንዝርት ላይ የሚጠመጠም፥ ከድር የሚወፍርና ላላ ያለ የጥጥ ክር። 2. በጣቃ ወይም በጥቅል መልክ እየተመረተ በሚወጣ ጨርቅ ላይ በወርዱ በኩል ከድሩ ጋር ተሰባጥሮ የሚገኘው ፈትል ወይም ክር።

**ማግስት** ስ ቀጥሎ የሚመጣው ቀን፥ በበነጋው። *ልጁ በመጣ በማግስቱ ላባትየው ሄደ።*

**ማግኔት** ስ ብረትን የሚስብ ብረት።

***ማጠ**

**ምጥ** ስ 1. ለመውለድ የደረሰች እንስት በመውለጃዋ ሰአት ልጁ ከማህፀኗ እንዲወጣ የምታደርገው ወደ ታች የመጫን፥ የመግፋትና እህ የማለት ጥረት። 2. (ዘይ.) ጭንቀት፥ ጥበት።

**አማጠ** ግ 1.ከሆዱ ውስጥ ወደ ውጭ ገፋ፥ እህ አለ (አይነምድርን)። 2. (ዘይ.) ተጨነቀ፥ ተጠበበ።

**አማጠች** እርጉዝ በወሊድ ጊዜ ልጇን ከማህፀኗ ለማስወጣት ወደታች ገፋች፥ እህ አለች።

**አስማጠ** ግ አልወጣም በማለት በጣም እህ አሰኘ፥ አስጨነቀ (አይነምድር)።

**ማጠቃለያ** "ጠቀለለ" ስር ተመ.

**ማጠናከሪያ** "ጠነከረ"ስር ተመ.

**ማጠንት** "አጠነ" ስር "ማእጠንት"ን ተመ.

**ማጠንፈፊያ** "ጠነፈፈ" ስር ተመ.

**ማጠፊያ** "አጠፈ"ስር ተመ.

**ማጣሪያ** "ጠራ[2]" ስር ተመ.

**ማጣበቂያ** "*ጠበቀ" ስር ተመ.

**ማጣፊጫ** "ጣፈጠ" ስር ተመ.

**ማጣፊያ** "አጣፋ" ስር ተመ.

**ማጥ** ስ አረንቋ፥ ረግረግ።


**ማጥለያ** "ጠለለ" ስር ተመ.

**ማጨሻ** "ጨሰ" ስር ተመ.

**ማጩራ** ስ በሽንብራ እሸት ቅጠልና በፍሬው ሽፋን ላይ የሚገኝ ጨው ጨው የሚል ወዝ።

**ማጫ** "አጨ" ስር ተመ.

**ማጫወቻ** "**ጫወተ**" ስር ተመ.
**ማጫጫሻ** "**ጨሰ**" ስር ተመ.
**ማጭዴ** ስ የቂጥኝ በሽታ አይነት።
**ማጭድ** "**አጨደ**" ስር ተመ.
***ማፀነ**
**ተማፀነ (ተማጠነ)** ግ አጥብቆ ለመነ፥ ተማለዱኝ አለ።
**አማፀነ (አማጠነ)** ግ 1. ለሌላ ለመነ፥ አማለደ። 2. ተማፀነ።
**ማፅናኛ** "**ጠና**" ስር ተመ.
**ማፈሪያ** "**አፈረ**" ስር ተመ.
**ማፈኛ** "**አፈነ**" ስር ተመ.
**ማፉዳ** ስ ከቆዳ የተሰራ ኮረጆ፥ ከረጢት፥ ቦርሳ።
**ማሟያ** "**ሞላ**" ስር ተመ.
**ሜ** የ "**መ**" ፊደል ሃምስ ዘር።
**ሜል** ስ የሰባ በሬ፥ ሰንጋ።
**ሜርቆ (መርቄ)** ስ በወይናደጋ አካባቢ የሚበቅል ሰይፍ የሚመስል ረዣዥም ቅጠል ያለው ዛፍ።
**ሜርኩሪ**[1] ስ ፈሳሽ የሆነና ብርማ ነጭ መልክ ያለው ማእድን፤ ባዙቃ።
**ሜርኩሪ**[2] ስ ለፀሃይ ቅርብ ሆና የምትገኝና ፀሃይን ከሚዞሩት ዘጠኙ ፕላኔቶች አንዷ ፕላኔት (በተጨማሪ ፕላኔት ስር ተመ.)።
**ሜሮን** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) አዲስ አባል ክርስትና ሲነሳ፥ ካህን ሲሾም፥ ንጉስ ሲነግስ፥... በካህናት እጅ የሚቀባው ቅባት፤ ቅብአ ቅዱስ።
**ሜትር** "**መተረ**[1]" ስር ተመ.
**ሜንዶ** "**መንዶ**"ን ተመ.
**ሜንጦ** ስ ስጋን ወይም ልዩ ልዩ እቃዎችን እንዲያንጠለጥል ሆኖ የተሠራ ቆላፋ ብረት፥ እንጨት፥... ወይም በግንዱ ጫፍ ላይ የበቀሉ በርካታ የባላ ጣቶች ያሉት የእንጨት መስቀያ።


ሜንጦ

**ሜካኒክ** "**መካኒክ**"ን ተመ.
**ሜዳ** ስ 1. ዳገት ቁልቁለት፥ ጫካ የሌለው ለጥ ያለ ሰፊ መሬት። 2. ከቤት ውጪ፥ የትም ቦታ። *የጠፋው ሰላት ሜዳ ላይ ወድቆ ተገኘ።*
**ሜዳ ሙሉ** ብዙ፥ አያሌ።
**ሜዳ ወጣ** ሜዳ ላይ፥ ጫካ ውስጥ ተፀዳዳ።
**ሜዳ ወጣች** ጉያዋን፥ ብልቷን ታጠበች፤ የግብር ውሃ ወጣች፤ ተፀዳዳች።
**የሜዳ አህያ** ስ መላ አካሉ በነጭና ጠቆር ባለ የቀለም ስብጥር የተሸለመለመ፥ ቁመቱ ከአህያ ከፍ የሚል የዱር እንስሳ።(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።
**የሜዳ ፍየል** ስ ረዣዥም ቀንዶች ያሉትና ፍየል የሚመስል የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።
**ሜዳይ (ሜዳልያ)** ስ ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሃስ፥... የተሰራ፥ በተለያዩ የሙያ መስኮች ወይም ውድድሮች ብልጫ ሳሳዩ ወይም ጥሩ ለሰሩ ሰዎች ከመንግስት፥ ከድርጅት፥... የሚሰጥ ሽልማት፤ ኒሻን።
**ሜጀር ጄኔራል** ስ ከብርጋዲየርና ሌፍቴናንት ጄኔራል መሃል የሆነ ወታደራዊ ማእረግ።
**ም** የ "**መ**" ፊደል ሳድስ ዘር።
**_ም** 1. እንዲሁም፥ በተጨማሪ። *ደብተር ብቻ ሳይምሰልህ፥ እርሳስም ግዛሁ።* 2. ሌላው ቀርቶ፤ እንኳን። *በስብሰባው ላይ ሳንድም ሰው ሳልተገኘም።*
**ምሁር** "**መሃረ**" ስር ተመ.
**ምህላ** ስ ፀሎት፥ ምልጃ፥ ልመና።
**ምህረት** "**ማረ**" ስር ተመ.
**ምህንድስና** "**መሃንዲስ**" ስር ተመ.
**ምህዋር** ስ መዞሪያ፥ መሄጃ መስመር (የፕላኔቶች)።
**ምህፃረ ቃል** ስ በሙሉ ቃል ፋንታ በአጭሩ የሚፃፍ፥ የሚነገር ቃል (ለምሳሌ ወዘተርፈ በማለት ፈንታ ወዘተ.)።
**ምላስ** "**ላሰ**" ስር ተመ.
**ምላሽ** "**መለሰ**" ስር ተመ.
**ምላት** "**ሞላ**" ስር ተመ.
**ምላጭ** "**ላጨ**" ስር ተመ.
**ምልመላ** "**መለመለ**[2]" ስር ተመ.
**ምልማይ** "**መለመለ**[1]" ስር ተመ.
**ምልምል**[1] ዝ.ከ.
**ምልምል**[2] "**መለመለ**[2]" ስር ተመ.
**ምልሰት** "**መለሰ**" ስር ተመ.
**ምልስ** ዝ.ከ.
**ምልአተ ጉባኤ** "**ሞላ**[1]"ስር ተመ.
**ምልአት** ዝ.ከ.
**ምልኩስና** "**መነኮሰ**" ስር "**ምንኩስና**"ን ተመ.
**ምልኪ** "**መለከ**" ስር ተመ.
**ምልክት** "**መለከተ**"ስር ተመ.
**ምልጃ** "**ማለደ**[2]" ስር ተመ.

**ምረቃ** "መረቀ" ስር ተመ.
**ምሩቅ** ዝ.ከ.
**ምረት** "መራ" ስር ተመ.
**ምራቅ** ስ ከአፍ የሚወጣ አረፋነት ያለው ፈሳሽ ነገር።
**ምራቁን ዋጠ** ጎመጀ፥ ጓጓ።
**ምራቁን የዋጠ** በእድሜ የበሰለ፥ የሰከነ ሰው።
**ምራት** ስ የልጅ ሚስት።
**ምራን** "መረነ" ስር ተመ.
**ምራጭ** "መረጠ" ስር ተመ.
**ምሬት** "መረረ" ስር ተመ.
**ምር** ዝ.ከ.
**ምርመራ** "መረመረ" ስር ተመ.
**ምርምር** ዝ.ከ.
**ምርቃት** "መረቀ" ስር ተመ.
**ምርቃና** "መረቀነ" ስር ተመ.
**ምርቅ** ስ በስንዴ፥ በገብስ፥... እህል ፍሬ ጫፍ ላይ የሚገኝ እሾሃማ ጭገር።
**ምርቅና ፍትፍት** ጥሩና መጥፎ።
**ምርታማ** "መረተ[1]" ስር ተመ.
**ምርት** ዝ.ከ.
**ምርኩዝ** "*መረኰዘ" ስር ተመ.
**ምርኮ** "ማረከ" ስር ተመ.
**ምርኮኛ** ዝ.ከ.
**ምርጊት** "መረገ" ስር ተመ.
**ምርግ** ዝ.ከ.።
**ምርጥ** "መረጠ" ስር ተመ.
**ምርጫ** ዝ.ከ.
**ምርፋቅ** "ረፈቀ" ስር ተመ.
**ምሰሶ (ምሶሶ)** ስ 1. በገጠር አካባቢ በተለይ ክብ ቅርፅ ይዞ በሚሰራ የሳር ቤት ውስጥ፥ ከቤቱ ወለል መካከል ላይ ተተክሎ፥ ጣሪያውን ተሸክሞ የሚቆም፥ ቀጥ ያለ፥ ረዥምና ጠንካራ የሆነ ግንዲላ። 2. የኤሌክትሪክ፥ የስልክ፥... ሽቦ የሚታሰርበት ረዥምና ወፍራም እንጨት። 3. ለጣሪያ ወይም ለታዛ መደገፊያ ተብሎ በበረንዳ ወይም በቤት ውስጥ የሚተከል የእንጨት፥ የብረት ወይም የድንጋይ ቋሚ። 4. (ዘይ.) ዋነኛ፥ ድጋፍ፥ መሰረት። *ታላቅ ወንድማቸው የቤቱ ምሰሶ ነው።*
**ምሳ** ስ እኩለ ቀን ላይ የሚበላ ምግብ።
**ምሳ ቋጠረ** ለምሳ የሚሆነውን ምግብ በአገልግል ወይም በሰሃን፥... ያዘ።

**ምሳሌ** "መሰለ" ስር ተመ.
**ምሳሌያዊ ንግግር** ዝ.ከ.
**ምሳር** "ጠገረ[2]" ን ተመ.
**ምሳና** "ብሳና" ን ተመ.
**ምሳግ** "መሰገ" ስር ተመ.
**ምስ** ስ 1. ለሰይጣን፥ ለዛር፥ ለቡዳ፥... የሚሰጥ ድርጎ፥ ግብር። 2. ቅጣት። *ምሱን አገኘ።*
**ምስለቢስ** "መሰለ" ስር ተመ.
**ምስለኔ** ስ በባላባቱ ስርአት የመሬት ስሪት ውስጥ መንግስት ወይም መልከኛ፥... የሚወክለው፥ ስልጣኑ ከጭቃ ሹም በላይ የነበረ ሹም።
**ምስል** "መሰለ" ስር ተመ.
**ምስማር (ሚስማር)** ስ በአንድ በኩል ሹል ጫፍ በሌላ በኩል ጠፍጣፋ አናት ያለው፥ እንጨትና ቆርቆሮ የመሳሰሉትን ለማያያዝ የሚያገለግል ትንሽ የብረት ዘንግ።



ምስማር

**ምስማክ[1]** "ሰበከ" ስር "ምስባክ" ን ተመ.
**ምስማክ[2]** ስ በመፅሃፍ ገፆች መጋጠሚያ ግራና ቀኝ ላይ ያለ ባዶ ቦታ።
**ምስረታ** "መሰረተ" ስር ተመ.
**ምስራቅ** ስ ከአራቱ ማእዘናት አንዱ የሆነና በፀሃይ መውጫ በኩል ያለ አቅጣጫ፤ የምእራብ ተይዩ።
**ምስራቃዊ** ቅ 1. በስተምስራቅ አቅጣጫ ያለ፥ የሚገኝ። 2. የምስራቅ።
**ምስራች** ስ የደስታ ወሬ፥ ዜና።
**የምስራች** 1. አንድን የደስታ ወሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመናገር ወይም ለማብሰር እንደመግቢያ ወይም እንደመንደርደሪያ ሆኖ የሚነገር ቃል (ለምሳሌ ተናጋሪ "የምስራች" ሲል ሰሚ "ምስር ብላ" ብሎ ይመልሳል)። 2. እንደ ቡና፥ ብርቱካን፥ ወይን፥ ትርንጎ፥... ያለ ተክል ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያፈራው ፍሬ። *ቡናው የምስራች ሰጠ።*
**ምስር** ስ ከአተር በመጠን የሚያንስ፥ ጠፍጣፋና ክብ የሆነ፥ ለወጥ፥ ለንፍሮ፥... የሚሆን ከጥራጥሬ እህሎች አንዱ፤ ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ምስር ይባላል።
**ምስር ብላ** የደስታ ወሬ ለመንገር "የምስራች" ላለ ሰው የሚሰጥ ምላሽ።
**ምስር ጥርስ** ስ 1. የወተት ጥርስ። 2. በጣም ትንንሽ የሆነ ጥርስ።

**ምስሬ** ስ የቂጥኝ አይነት።

**ምስርቃና (ምስረቃና)** ስ እምቢልታ ወይም መለከት።

**ምስርች** ስ ቅጠሉ እንደምስር ቅጠል ያለ ሆኖ እንጨቱ መለል ብሎ ረዘም ያሉና ለጨፌቃነት የሚያገለግል የእፅዋት አይነት።

**ምስቅልቅል** "*መሰቀለ" ስር ተመ.

**ምስባክ** "ሰበከ" ስር ተመ.

**ምስኪን** ቅ 1. ያጣ የነጣ፥ ጠም አዳሪ፥ የተቸገረ ደሃ። 2. አሳዛኝ (ሰው፥ እንስሳ፥...)። 3. የዋሀ።

**ምስክር** "መሰከረ" ስር ተመ.

**ምስያ** "መሰለ" ስር ተመ.

**ምስጉን** "*መሰገነ" ስር ተመ.

**ምስጋና** ዝ.ከ.

**ምስጋን የለሽ** ዝ.ከ.


**ምስጢረ ስላሴ** "*መሰጠረ" ስር ተመ.

**ምስጢረ ስጋዌ** ዝ.ከ.

**ምስጢረኛ** ዝ.ከ.

**ምስጢር** ዝ.ከ.

**ምስጥ** ስ 1. እንጨትን እየበላና እየሰረሰረ የሚገባ፥ በመሬት ውስጥ ለውስጥ መሄድ የሚችል፥ ቅርፁ ጉንዳን የሚመስል ቀይ ነፍሳት። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ማንም ሳያውቅበት አንድን ነገር ውስጥ ለውስጥ የሚፈፅም፤ ማሽንክ።



ምስጥ 1ኛ ፍቺ

**ምሰሶ** "ምሰሶ"ን ተመ.

**ምሸሸ** ስ ከስንደዶና ከአክርማ የሚሰራ የእህል መስፈሪያ፥ ሳጥን።

**ምሸሮ (ሙሸሮ)** ስ ካንገት ላይ የሚወጣ፥ ቶሎ የማይሽር ቁስል፤ ነቀርሳ።

**ምሽት** "ሚስት"ን ተመ.

**ምሽት** "መሸ" ስር ተመ.

**ምሽግ** "መሸገ" ስር ተመ.

**ምቀኛ** "*መቀኘ" ስር ተመ.

**ምት** "መታ[1]" ስር ተመ.

**ምትሃት (ምታት)** ስ ድግምት፥ አስማት ወይም ሌሎች ነገሮችን በማድረግ በአይን ብቻ ሊታይ የሚቻል አስገራሚ ድረጊት ሆኖ ነገር ግን ወዲያው የሚጠፋ ወይም እውነትነት የሌለውና የማይጨበጥ ነገር።

**ምትሃተኛ** ቅ ምትሃት የማድረግ ወይም የመስራት ችሎታ ያለው (ሰው)።

**ምትክ** "ተካ" ስር ተመ.

**ምቹ** "*መቸ" ስር ተመ.

**ምች** "መታ" ስር ተመ.

**ምቾት** "*መቸ" ስር ተመ.

**ምነና** "መነነ" ስር "ምናኔ" ን ተመ.

**ምናሄ (መናሄ)** ስ ለመድሃኒትነት ያገለግላል የሚባል፥ ቅርፊቱ ነጭ የሆነና በቆላ የሚበቅል አነስተኛ ዛፍ።

**ምናልባት** "ምን" ስር "ምንአልባት"ን ተመ.

**ምናምን** "ምን" ስር ተመ.

**ምናምንቴ** ቅ የማይረባ፥ ተልካሻ፥ ልክስክስ።

**ምናኔ** "መነነ" ስር ተመ.

**ምኔት** ስ ገዳም።

**አበምኔት** ስ የወንዶች ገዳም አለቃ፥ ሹም ወይም አስተዳዳሪ።

**እመምኔት** ስ የሴቶች ገዳም ሹም ወይም አስተዳዳሪ (መነኩሲት)።

**ምን (ምንድን፥ ምንድር)** ተው.ስ. 1. ያልታወቀን ነገር ማንነት፥ ምንነት፥ አይነት፥... ለማወቅ ሲፈለግ ጥያቄ ማቅረቢያ ሆኖ የሚያገለግል ቃል። *ሀ. የምታነበው ምን መፅሃፍ ነው? ለ. ምን እየሰራህ ነው?* 2. በጣም፥ የትኛውንም ያህል። *መንገዱ ምን ቢርቅ ከሁለት ሰአት በላይ አያስኬድም።*

**ምነው** ለምን፥ በምን ምክንያት። *ምነው ቀረህ።*

**ምኑ ቅጡ** ብዛትን በማጋነን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *የልብሱ፥ የወርቁ ፥ አረ ምኑ ቅጡ!*

**ምኑ ነች** 1. ያላቸው ግንኙነት፥ ዝምድና እንዴት ነው? 2. አትበቃውም፥ ታንሰዋለች፥ ቅምም አትለው። *ለምስት እንጀራ ለሱ ምኑ ነች።*

**ምኑንም ምኑንም** የተገኘውን ሁሉ (ሳይመርጥ)።

**ምን ሆነ** ምን አጋጠመው፥ ምን ነካው።

**ምን መሆኑ ነው** 1. ምንድን ነው። *ይሄ እቃ ምን መሆኑ ነው?* 2. ምን ማድረጉ ነው? *ምን መሆኑ ነው ስራውን ትቶ የሄደው?*

**ምን መጣ** 1. የመጣው ምንድነው? 2.

በምን ምክንያት (የእምቢታ አገላለፅ)።

**ምንመጣብኝ** እንዴት አይነት መጥፎ ነገር ገጠመኝ!

**ምን ቆርጦኝ** 1. በምን ምክንያት (አላደርገውም፥ ምን በወጣኝ የማለት የእምቢታ መልስ)። 2. ምን አስገድዶኝ፥ ምንአግብቶኝ።

**ምን በላው** የት ሄደ፥ የት ደረሰ።

**ምን በወጣኝ** ምን ባደረግሁ፥ ምን ባጠፋሁ፥ በምን ምክንያት፥ ለምን።

**ምንቤት ነህ** ምን አገባህ፤ ምን ጥልቅ አደረገህ።

**ምንተዳዬ** ምንቸገረኝ፤ ግድ የለኝም።

**ምንቸገረኝ** 1. ምን አገባኝ። 2. ግዴለኝም፥ ይሁን፤ እሺ።

**ምንአለበት (ምናለበት)** ምን ይጎዳል፥ ምን ያስቸግራል (አይጎዳም፥ አያስቸግርም፥ ይሁን ለማለት የሚነገር)።

**ምንአልባት** የግምት፥ የጥርጣሬ፥ የይሆን ይሆናል አነጋገር። *ምናልባት እመጣ ይሆናል።*

**ምንአባቱ(ምናባቱ)** 1. የስድብ ቃል። 2. የተስፋ መቁረጥ፥ የንዴት፥... መግለጫ ቃል። *ምናባቱ ቢቀርስ! ምናባቴ ላድርግ።* 3. የፍርሃትና የአክብሮት መግለጫ ቃል። *ምናባቴ ቆርጦኝ ነው እሱን የምናገረው!*

**ምንአውቄ (ምናውቄ)** እኔ አላውቅም፥ እኔ እጃ።

**ምንአውቅልህ (ምናውቅልህ)** በእንቆቅልሽ ጥያቄ ጊዜ ተጠያቂው ለመልስ መዘጋጀቱን ለመግለፅ የሚናገረው ቃል (ለምሳሌ ጠያቂ "እንቆቅልህ" ሲል መላሽ "ምን አውቅልህ" ይላል። ትርጉሙ "ምን ልወቅልህ" ማለት ነው)።

**ምንአገባኝ (ምናገባኝ)** ምንቸገረኝ፥ ጉዳዩ አይመለከተኝም።

**ምንከፋኝ** እሺ፥ ይሁን፥ እንደተባለው ይፈፀም፥ ይደረግ።

**ምንወሰደው** የት ጠፋ፥ የት ነው ያለው፥ የት ሄደ።

**ምን ዋጠው** ዝ.ከ.

**ምን ያህል** ስንት።

**ምን ይሆናል** 1. ምን ይጠቅማል፥ ምን ያገለግላል። 2. የፀፀት ስሜትን ለመግለፅ የሚያገለግል አባባል። *ምን ይሆናል ሁሉም አለፈ!*

**ምንገዶኝ** 1. ምንቸግሮኝ። 2. ለምን እምቢ እላለሁ።

**ምንጊዜ (ምነዜ፥ ምነዬ፥ምኔ)** መቼ፥ በየትኛው ጊዜ፥ በስንት ሰአት።

**[ለ] ምንጊዜም** 1. ሁልጊዜ። 2. በማንኛውም ጊዜ።

**ምን ጥልቅ አደረገህ** ምን አገባህ።

**ከምንጊዜው (ከምኔው)** ከመቼው፥ እንዴት ባለ ፍጥነት።

**ምንና ምን** የትና የት፥ ወዴትና ወዴት፥ ሩቅ ለሩቅ፥ የማይገናኝ፥ የማይወዳደር፥ የማይመሳሰል። *ዝሆንና ትንኝ ምንናምን ናቸው።*

**እንደምን ነህ** ጤንነትህ፥ ኑሮህ፥ በምን አይነት ሁኔታ ላይ ነው ለማለት የሚነገር የሰላምታ ቃል።

**ምንነት** የአንድ ነገር (ባህሪ፥ አመጣጥ፥ ተፈጥሮ፥...) መታወቂያ፥ መለያ።

**ምንኛ** በጣም፥ በሃይል። *ምንኛ ከብሯል!*

**ምናምን** የሆነ ነገር፥ አንድ ነገር።

**ምናምን በለኝ** አንድ ነገር ጋብዘኝ፥ ስጠኝ።

**ምናምኒት** አንድም ነገር፥ ላመል ታህል እንኳን። *የሚበላ ምናምኒት የለኝም።*

**ምንም** ቅ ባዶ፥ አንድም፥ ትንሽም። *ምንም የለኝም።*

**ምንም አይቀረው** የማያደርገው ወይም የማይበላው ወይም የማይጠጣው፥... ነገር የለም።

**ምንም አይቀራት** ውብ ፥ ቆንጆ ናት።

**ምንም አይወጣው** 1. ምንም አይናገር። 2. እንከን አይገኝበትም።

**ከምንም አይቆጥረው** 1. ይንቀዋል፥ አይፈራውም። 2. አያስቸግረውም፤ አቅልሎ ይመለከተዋል።

**ምንም ቢሆን** የሆነው፥ የፈለገው ቢሆን።

**ምንም አይል** 1. ደህና ነው፤ መጠነኛ፥ መካከለኛ ነው። 2. አይጎዳም። 3. አይናገርም፥ አይቆጣም። *ልጁ ቢያመሽ አባቱ ምንም አይልም።*

**ምንም አይደል** ግዴለም፥ አያስወነቅም፥ አያሳስብም።

**ምንም [እንኳን]** ቢሆንም ቅሉ።

**በምንም አይነት** ፈፅሞ፥ በጭራሽ፥ የፈለገው ቢሆን።

**እንደምንም** በተቻለ መጠን፥ በጥረት።

**ምንሽር** ስ የጠመንጃ ስም።

**ምንሽንሽ** "መነሽነሽ" ስር ተመ.

**ምንሸ** ስ ተቅማጥ።

**ምንቂያም** "*መነቀ" ስር ተመ.

**ምንቃር** "* ነቀረ" ስር የ"መንቆር"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ምንቅ ምንቅ አለ** "*መነቀ"ስር ተመ.

**ምንባብ** "*ነበበ" ስር ተመ.

**ምንተ__** ስለ____:: *ምንተማርያም::*

**ምንተእፍረቱን** ስላፈረ:: *በሰዎች ፊት ስለጠየቅሁት ምንተእፍረቱን ገንዘቤን ሰጠኝ::* .

**ምንትስ** የአንድ ነገር ስም ሲረሳ ወይም ስሙን ለመጥራት ባልተፈለገ ጊዜ በምትኩ እየገባ የሚያገለግል ቃል::

**ምንቸት** ስ ለወጥ መስሪያ፥ ለንፍሮ፥ ለጎመን፥... መቀቀያ የሚያገለግል የማሰሮ አይነት(ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.)::

**ምንቸት አብሽ** ስ በጣም ደቆ ከተከተፈ ስጋ የሚዘጋጅ የወጥ አይነት::

**ምንኩስና "መነኮሰ"** ስር ተመ.

**ምንዛሪ "መነዘረ"** ስር ተመ.

**ምንዝር "መነዘረ"** ስር ተመ.

**ምንዳ** ስ የድካም ወይም የስራ ዋጋ፤ ደመወዝ::

**ምንደኛ** ቅ 1. ተቀጥሮ የሚሰራ፥ ደመወዝተኛ:: ስ 2. ቅጥረኛ፥ ለገንዘብ የሚሰራ::

**ምንድር "ምን"** ን ተመ.

**ምንዝላት (ምዝላያት፥ ምንዥላት)** ስ የሸማቅ_ አባት ወይም እናት፤ 5ኛው አያት::

**ምንጣፍ "*ነጠፈ"** ስር ተመ.

**ምንጭ "መነጨ"** ስር ተመ.

**ምንጭር** ስ የላይኛው ከንፈር (ብዙ ጊዜ ለከብት)::

**ምንጭራም** ቅ (ስድብ) የላይኛው ከንፈሩ ትልቅ የሆነ::

**ምንጭርር** ስ ስሩ ተቀጥቅጦ ለማቅለሚያነት የሚያገለግል እፅ::

**ምኞት "*መኘ"** ስር ተመ.

**ምእላድ** ስ ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደ ሆነ ሌላ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊከፈል የማይችል የመጨረሻ ንኡስ አሃድ ወይም ክፍል (ለምሳሌ "ሆድ" ራሱን የቻለ ቃል ወይም ምእላድ ሲሆን "ሆዳም" ግን የ"ሆድ" እና የቅፅል መስራቹ "-ም" ጥምረት ማለትም የሁለት ምእላዶች ጥምረት የፈጠረው ቃል ነው)::

**ምእመን "አመነ"** ስር ተመ.

**ምእራብ** ስ ከአራቱ ማእዘናት አንዱ የሆነና በፀሃይ መጥለቂያ በኩል ያለ አቅጣጫ፤ የምስራቅ ትይዩ (በተጨማሪ ማእዘንን ተመ.)::

**ምእራባዊ (ብ.ቁ. ምእራባውያን)** ቅ 1. በምእራብ አቅጣጫ በኩል ያለ፥ የሚገኝ:: 2. የምእራብ:: ስ 3. (ለብዙ ቁጥር ሲሆን) የምእራብ አውሮፓና የሰሜን አሜሪካ አገሮች በአንድ ላይ የሚጠሩበት ስም::

**ምእራፍ** ስ 1. በመፅሃፍ ውስጥ ያለ የመፅሃፉ መከፈያ (ብዙውን ጊዜ በቁጥር ይጠራል፤ ለምሳሌ ምእራፍ አንድ፥ ምእራፍ ሁለት):: 2. በረዥም የቦታ ርቀት መሃል የሚገኝ የተወሰነ አጭር የቦታ ርቀት:: 3. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ወደ ቀብር ቦታ የሚጓዝ ሬሳን በየመንገዱ እያሳረፉ የጉዞ ፍታት ወይም ፀሎት የሚያደርጉበት ስፍራ:: 4. አንድ ክንዋኔ ወይም ሁኔታ አልፎ ሌላ የሚጀመርበት ወቅት:: *በኢኮኖሚ እድገት አዲስ ምእራፍ ጀምረናል::*

**ምእዙን "ማእዘን"** ስር ተመ.

**ምኩራብ** ስ 1. የአይሁድ ፀሎት ቤት:: 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የሁዳዴ ፆም ሶስተኛው ሳምንት::

**ምክር "መከረ"** ስር ተመ

**ምክትል "*ከተለ"** ስር ተመ.

**ምክቶሽ "መከተ"** ስር ተመ.

**ምክንያት "*መከኘ"** ስር ተመ.

**ምክክር "መከረ"** ስር ተመ.

**ምዝላያት "ምንዝላት"** ን ተመ.

**ምዝራጥ (ምዥራጥ)** ስ ትልቅ አንካሴ፤ ሽብዳ::

**ምዝበራ "መዘበረ"** ስር ተመ.

**ምዝብር** ዝ.ክ.

**ምዝገባ "መዘገበ"** ስር ተመ.

**ምዥራጥ "ምዝራጥ"**ን ተመ.

**ምድማድ "መደመደ"** ስር ተመ.

**ምድር** ስ መሬት::

**ምድር ሰማይ ዞረበት** 1. ነገሩ ሁሉ ተሳከረበት፥ ተምታታበት፥ መለየት አቃተው:: 2. በበሽታ ወይም ከመጠን በላይ የሚያስክር መጠጥ በመጠጣቱ ሰማዩም ምድሩም፥ በአካባቢው ያለው ነገር ሁሉ የሚሽከረከር፥ የሚገለባበጥ መሰለው::

**ምድር ቀለጠች** በደስታ፥ በፈንጠዝያ፥ በጨዋታ ወይም በጠብና በጦርነት ምክንያት ትርምስ፥ ድብልቅልቅ ሆነ::

**ምድር አለፈ (አለፈች)** ዝ.ክ.

**ምድር ከዳችው** ድንገት ሳያስበው ወደቀ (አዙሮት፥ አዳልጦት ወይም አንሸራትቶት)::

**ምድር ፊት** አስቀያሚ::

**ከምድር ተነስቶ** ያለምንም ምክንያት::

**ምድረ__** __ሁሉ፥ ማንም፥ አንድም ሳይቀር:: *ምድረ ኩታራ ተሰብስቦ ሲንጫጫ ዋለ::*

**ምድረ በዳ (በዳ)** ስ 1. እፅዋትና ውሃ የማይገኝበት ደረቅ ቦታ፤ በረሃ:: 2. ሰው የማይኖርበት ጭር ያለ ቦታ፥ አካባቢ::

**ከምድረ ገፅ (ከገፀ ምድር)** ከምድር ላይ::

*በአሁኑ ጊዜ ፈንጣጣ ከምድረ ገፅ ጠፍቷል።*

**ምድር ቤት** ስ ፎቅ ሆኖ በተሰራ ቤት ውስጥ ከመሰረቱ በላይና ከአንደኛው ፎቅ ስር ያለው ቤት።

**የምድር ሰላጤ** ስ ከሜፉ ሾልና ሾጠጥ ብሎ ወደባህር የሚገባ የመሬት አካል፥ ጠርዝ።

**የምድር ሰቅ/ወገብ** ስ በምስራቅና በምእራብ አቅጣጫ በምድር ወገብ ዙሪያ የተሰመረ የሃሳብ መስመር።

**የምድር በርበሬ** ስ ወደ ቅላት የሚያደላ ቢጫ አበባ ያለው፥ እንጥል ሲወርድ መድሃኒት ነው ተብሎ የሚበላ፥ የሚያቃጥል የእፅዋት ሕይነት።

**የምድር እንቧይ** ስ ቅጠሉና የፍሬው ሽፋን ጭገራም የሆነ፥ ሲበስል ቀይ የሚሆን፥ ኮክ የሚያካክል ፍሬ ያለውና መሬት ላይ የሚተኛ አነስተኛ ሃረግማ የእፅዋት አይነት።

**የምድር ዋልታ** ስ የምድር ሰሜናዊ ወይም ደቡባዊ ጫፍ።

**የምድር ዝላይ** ስ (ስፖ.) ከአንድ ከተወሰነ መነሻ ቦታ ላይ ተነስቶ በአየር ላይ አግድም በመወርወር የሚደረግ ዝላይ።

**የምድር ጉድ** በጣም አጭር፥ ድንክ።

**የምድር ጦር** ስ እግረኛን፥ ታንከኛን፥ መድፈኛን፥... የሚያጠቃልል በመሬት ላይ እየተጓዘ የሚዋጋ ወታደራዊ ክፍል።

**ምድራዊ** (ብ.ቁ. **ምድራውያን**) ቅ 1. አለማዊ፥ ስጋዊ፤ መንፈሳዊ ያልሆነ። 2. በምድር ላይ ያለ፥ የሚገኝ፥ የሚኖር (ፍጡር)።

**ምድብ "መደበ"** ስር ተመ.

**ምድጃ "ነደደ[1]"** ስር ተመ.

**ምግባር "*ገበረ[1]"** ስር ተመ.

**ምግብ "መገበ"** ስር ተመ.

**ምጎጎ (ሙጎጎ)** ስ ከሸክላ የሚሰራ የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ።

**ምጣት "መጣ"** ስር ተመ.

**ምጣኔ "መጠነ"** ስር ተመ.

**ምጣድ "ጣደ"** ስር ተመ.

**ምጣጭ "መጠጠ"** ስር ተመ.

**ምጥ "*ማጠ"** ስር ተመ.

**ምጥማቅ "ጠመቀ[2]"**ስር ተመ.

**ምጥማጥ (ሽለምጥማጥ)** ስ 1. መጠኑ ድመት የሚያክል፥ ጅራቱ ረዥምና እግረ አጫጭር የሆነ አውሬ። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) በጣም ጥቁር (ለመልክ)።(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ምጥቀት "መጠቀ"** ስር ተመ.

**ምጥን "መጠነ"** ስር ተመ.

**ምፀት** ስ በቀጥታ የቀረበውን ወይም የተነገረውን ሃሳብ ትርጉም ተቃራኒ የሚያሳይ የንግግር ስልት፤ የዘይቤያዊ አነጋገር አይነት።

**ምፅአት** ስ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አለም የሚመጣበት ጊዜ።

**ምፅዋት "መፀወተ"** ስር ተመ.

**ሞ** የ"መ" ፊደል ሳብአ ዘር።

**ሞሆዶ "መሆዶ"** ን ተመ.

**ሞለለ** ግ የክብነት ቅርፅ ይዞ ቁመቱ ረዘመ፥ ሞላላ ሆነ።

**ሞላላ** ቅ ቅርፁ ክብ ሆኖ ቁመቱ ረዘም ያለ።

**ሞለሞለ** ግ ሾጠጥ፥ ሞለል አለ።

**ሙልሙል** ስ ሞለል ያለ ህብስት፥ ጢቢኛ (ብዙውን ጊዜ ለቡሄ በአል የሚዘጋጅ)።

**አሞለሞለ** ግ 1. ሙልሙል ጋገረ። 2. ሞላላ አደረገ። 3. አበጠ፤ አሞጠሞጠ (ለምሳሌ ለመፍረጥ የደረሰ ብጉንጅ፥ እባጭ፥...)።

**ሞለሰሰ** ግ 1. በብዛት ነጨ፥ ነቀለ፥ መዘዘ። 2. አስተኛ፥ አጋደመ፥ ለጠሰ።

**ሞለቀቀ** ግ 1. ፈለቀቀ፥ ከፈተ። 2. ገፈፈ፥ገሸለጠ።

***ሞለቀቀ**

**ሞልቃቃ** ቅ ስርአት የሌለው፥ ቀበጥ።

**ተሞላቀቀ** ግ 1. ተንቀባረረ፥ ተንደላቀቀ፥ ተቀማጠለ። 2. ስርአት አጣ፥ ቀበጠ።

**አሞላቀቀ** ግ 1. አንቀባረረ፥ አቀማጠለ። 2. አባለገ፥ ስነስርአት የለሽ አደረገ።

**ሞለገገ** ግ ቂለ፥ ጀለ።

**ሞለገግ (ሞልጋጋ)** ቅ ቂል፥ ጅል።

**ሞለጨ** ግ 1. ምንም ሳያስቀር ጠራርጎ ወሰደ፥ ሟጠጠ፥ ባዶ አደረገ። 2. ሰረቀ። 3. ገረፈ፥ ቀጣ (እንደ አለንጋ፥ ጅራፍ፥ አርጩሜ ባለ)። 4. በጣም ተሳደበ።

**ሙልጩን (ሙልጭ) ሄደ** 1. ባዶ እጁን ቀረ፥ ምንም አጣ፥ ከሰረ። 2. ምንም ሳያገኝ፥ ምንም ሳይደርሰው ባዶውን ተሰናበተ፥ ወጣ።

**ሙልጩን (ሙልጭ)ወጣ** ዝ.ከ.

**ሞላጫ** ቅ 1. ወስላታ፥ የወጣለት ሌባ። 2. የማይያዝ፥ የማይጨበጥ።

**ሙልጭ አለ** ግ 1. ሙጥጥ አለ፥ ጥርግ አለ። *አንድም ሳይቀር ሁሉም ሙልጭ ብሎ ሄደ።* 2. ጥርት አለ፥ በደንብ ፀዳ። *እቃው ሙልጭ ብሎ ታጥቧል።*

**ሙልጭ አደረገ** ግ 1. ሟጠጠ፥ ባዶ

*አደረገ፥ ምንም ሳይተው ቀረ:: ሊቃውን ሙልጭ አድርጎ ወሰደ::* 2. በጣም ተሳደበ:: *ሌትየዋን ሙልጭ አደረጋት::*

***ሞለጨለጨ**

**ሙልጭልጭ** ቅ ዳላጣ፥ ግላጋ፤ የማይጨበጥ::

**ሙልጭልጭ አለ** ግ ተሙለጨለጨ::

**ሙልጭልጭ አደረገ** ግ አሙለጨለጨ::

**ተሙለጨለጨ** ግ 1. አልያዝ፥ አልጨበጥ አለ:: 2. ግላጋ ሆነ፥ ዳላጣ ሆነ::

**አሙለጨለጨ** ዝ.ከ.

***ሞለፈጠ**

**ሞልፋጣ** ቅ 1. ስራ ፈት፥ ዋልጌ፥ ማጋጣ:: 2. ባለጌ፥ ዘልዛላ:: 3. በአነጋገሩ፥ በአለባበሱ ወይም በሌላ ሁኔታው ደስ የማያሰኝ::

**ተሞላፈጠ** ግ 1. ስራ ፈታ፥ ዋልጌ ሆነ:: 2. ባለገ፥ ተንዘላዘለ::

**አሞላፈጠ** ግ አሞላቀቀ፥ አንዘላዘለ::

**ሞላ**[1] ግ 1. ባዶ ወይም ጎደሎ በነበረ ነገር ውስጥ ከአፍ እስከ ገደፉ ጨመረ፥ ከተተ፥ ጢም አደረገ:: 2 ቀዳ፥ ጨመረ:: *ቤንዚን ሞላ:* 3. በአነሰው ወይም በጎደለው ላይ ጨምሮ ወይም አክሎ ልክ አደረሰ፥ በቂ አደረገ:: 4. አደረገ፥ ፈፀመ፥ አሳካ:: *የልቡን ሞላ::* 5. በማዞር፥ በመጠምዘዝ ወይም በሌላ መንገድ አስፈላጊውን ሃይል ሰጠ፥ እንዲሰራ አደረገ:: *ሰዓቱን ሞላ::* 6. በተዘጋጀው የመጠይቅ ወረቀት ወይም ባዶ ቦታ ላይ አስፈላጊውን መረጃ ፃፈ:: 7. ሊይዝ የሚችለውን ያህል ያዘ፥ ሙሉ ሆነ:: *አዳራሹ ሞልቷል፥ ከዚህ በላይ ሰው አይጨምርም::* 8.ተሳካ፥ ተፈፀመ:: *ሃሳቤ ሞላ::* 9. ሆነ:: *ስድስት ሰዓት ሞላ:* 10. በዛ፥ አያሌ ሆነ:: *ቤክ ቤት በከተማው ሞላ::* 11. ያለውን ቦታ ሁሉ ያዘ:: *ሜዳውን የሞላው ቆሻሻ ነው::*

**በሞላ** ሁሉም፥ በጠቅላላ::

**ሞልቶ ቷል** ብዙ አለው:: *ገንዘብ ሞልቶታል::*

**ሞላለት** ተሳካለት::

**ከሞላ ጎደል** ሙሉ በሙሉ ሳይሆን፥ በአብዛኛው::

**መሙያ (መሙሊያ)** ስ 1. የስአት ሃይል መስጫና ማስተካከያ እጀታ:: 2. አረፍተ ነገርን ሙሉ ማድረጊያ ቃል ወይም ሃረግ (ለምሳሌ *"በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ሄደ"* በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ "ወደ ትምህርት ቤት" የሚለው ሃረግ መሙያ ነው)::

**ሙሉ** ቅ ጢም ያለ፥ ያልጎደለ፥ ያልተቀነሰለት::

**በሙሉ አይን አያየውም** ከመሳሳት ወይም ከመፍራት ወይም ከንቀት ወይም ከጥላቻ የተነሳ አትኩሮ አይመለከተውም::

**በሙሉ ልብ** 1. በእርግጠኝነት:: 2. በድፍረት::

**በሙሉ አፍ** በድፍረት::

**ሙሉ ለሙሉ** በጠቅላላ::

**ሙሉ ልብስ** ስ አንድ ላይ እንዲለበስ ሆኖ የተዘጋጀ አንድ አይነት ኮትና ሱሪ (የወንድ)::

**ሙሉ ሰው** ከወጣትነት ያለፈና በጣም ያልሸመገለ ሰው፤ ጎልማሳ::

**ሙሉ ቀን** ከጠዋት እስከ ማታ::

**ሙሉ ቁጥር** ስ ያለ ቀሪ ለሁለት መከፈል የሚችል ቁጥር (2፥4፥6፥...)::

**ሙሉ ቃል** ስ ምንም ሳይቀነስ ወይም ሳይጨመር እንዳለ የተወሰደ ንግግር::

**ሙሉ በሙሉ** በጠቅላላ::

**ሙሉ ጨረቃ** ስ ጨረቃ ሙሉ ክብ ሆና ስተወጣ የምትጠራበት ስም::

**ሙሉ ፍታት** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ለፍታት ተብሎ ከተመደበው ፀሎት ውስጥ ምንም ሳይቀነስ ለሙታን የሚደረግ ፀሎት::

**ባለሙሉ ስልጣን** ለተሾመበት ቦታ ሙሉ ስልጣን ያለው::

**ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር** ስ በተመደበበት አገር አገሩን በመወከል ማንኛውንም ጉዳይ የሚፈፅም አምባሳደር::

**ምላት (ምልአት)** ስ ሙሉነት::

**ምልአተ ጉባኤ** ስ አንድን ስብሰባ ለማካሄድ የሚያስችል ከተሰብሳቢዎች ውስጥ መገኘት ያለበትና በህገ ደንቡ ላይ የተደነገገ የአባላት ቁጥር ብዛት::

**ተሞላ** ግ 1. ተጥለቀለቀ፥ ተዋጠ:: *በደስታ ተሞላ::* 2. ተላበሰ:: *ፊቱ ፈገግታ ተሞላ:* 3. ተጠመደ፥ ተመረዘ:: *ከልጅነቱ በተንኮል ተሞላ::*

**ተሟላ** ግ 1. ተፈላጊው ነገር ተገኘ፥ ቀረበ፥ ሙሉ ሆነ:: 2. የታሰበው፥ የታለመው፥... ተሳካ፥ ተፈፀመ፥ ተደረገ::

**አሟላ** ግ የተፈለገውን ነገር አቀረበ፤ የጎደለውን አገኘ፤ ሙሉ አደረገ::

**አሟልቶ የሰጠው** እንከን የማይወጣለት፥ ምንም ያልጎደለው፥ ሁሉ ያለው::

**ማሟያ** ቅ የጎደለ ማስተካከያ::

**ሞላ**[2] ስ ጥምዝ ሆኖ የተሰራ፥ ሲገፉ የመሰብሰብና ሲጎተት ደግሞ የመለጠጥ ባህሪ ያለው፥ ተገፍቶ ወይም ተጎትቶ ሲለቀቅ ወደፊተኛው ቅርፁ ወይም ቦታው መመለስ የሚችል ብረት ወይም ሽቦ::

**ሞላጫ** "ሞለጨ" ስር ተመ.

**ሞልቃቃ** "*ሞለቀቀ" ስር ተመ.
**ሞልጋጋ** "*ሞለገገ" ስር "ሞለገግ" ን ተመ.
**ሞልፋጣ** "*ሞለፈጠ" ስር ተመ.
**ሞረሞረ**[1] ግ በረበረ፥ ሞሸለቀ፥ ውስጥ ውስጡ ተሰማ (ረሃብ)::
**ሞረሞረ**[2] ግ አሾለ፥ አሞጠሞጠ (አፍን)::
**ሙርሙርት** ቅ የሾለ፥ የሞጠሞጠ::
**ሙርሙርት አፍ** ቅ (ስድብ) ሹልአፍ፥ ሙጢ አፍ::
**ሞረሽ** ስ በጭለማ ወይም በአደጋ ጊዜ ከአካባቢው ራቅ ያለ ሰውን ለመጥራት የሚያገለግል የስም ምትክ (የሰውየው ስም የማይጠራው ሰውየውን ለአደጋ ላለማጋለጥ ሲባል ነው)::
**ሞረደ** ግ በሞረድ ፈገፈገ፥ ሳለ (ብረትን፥ ወርቅን፥ ጥፍርን፥...)::
**ሞረዳይ** ስ በሞረድነት የሚያገለግል በበረሃ ወይም በወንዝ ውስጥ የሚገኝ ሻካራ ድንጋይ::
**ሞረድ** ስ እንጨትን፥ ብረትን፥ ጥፍርን፥ ወርቅን፥... ለማለስለስ፥ ለማስላት፥ ለማሳነስ፥ ለማሳመር፥...የሚያገለግል ሻካራነት ያለው ብረት::
**ሞራ** ስ አብዛኛውን ጊዜ አንጀትና ጨጓራን ሸፍኖ፥ አንዳንዴም በጮማ ስጋ አካባቢ የሚገኝ ስብነት ያለው ነጭ የስጋ አይነት::
**ሞራ ገላጭ** ቅ ከብት ከታረደ በሂላ ወዲያውኑ ሞራውን ዘርግቶ በማየት የሚጠነቁል (ሰው)::
**ሞራል** ስ 1. የመንፈስ ብርታት፥ ጥንካሬ፥ ፅናት:: 2. ግብረገብ::
**የሞራል ካሳ** ስ በስድብ፥ በመንገላታት ወይም በሌላ ምክንያት ለደረሰ በደል ወይም የክብር መነካት ለተበደለው የሚከፈል ካሳ::
**የሞራል ድጋፍ** ስ ለማበረታታት የሚሰጥ (ገንዘብ ወይም ቁሳቁስ ያልሆነ) የሃሳብ ድጋፍ::
**ሞሸለቀ(መሸለቀ)** ግ 1. ገሸለጠ፥ ገፈፈ፥ ላጠ:: 2. ፈጀ፥ አቃጠለ፥ ላፈ:: 3. ገረፈ፥ መታ (በጅራፍ፥በአለንጋ፥...):: 4. ሰረቀ:: 5. ራበ፥ ሞረሞረ::
**ሞሽላቃ** ቅ ሌባ::
**ተሞሻለቀ** ግ አጭበረበረ::
**ሞሸሞሸ** ግ በመራስ ወይም በመበስበስ ሟሸሸ፥ ሉኩሉኩ::
**ሞሸረ** ግ 1. ሸፈነ፥ ጠቀለለ፥ ሸበለለ፥ በውስጥ አደረገ (ለምሳሌ የኮባ ተክል መሃል ለመሃል አዲስ የሚወጣውን ቅጠሉን):: 2. በአዲስ ልብስ፥ በጌጥ፥... አሳመረ፥ አስዋበ (ሙሽራን):: 3.በጫጉላ ቤት አስቀምጦ ጥሩ ጥሩ ነገር መገበ፥ ተከባከበ (ለምሳሌ ሙሽራን)::
**ሙሽራ** ስ 1. እንደ እንሰት፥ ሙዝና ዘንባባ ባሉ ተክሎች እናት ላይ አዲስ እየወጣ ያለውና የተጠቀለለው ወይም የተሸበለለው መሃከለኛው ቅጠል:: 2. የጋብቻ በአሉን (ኗን) በማክበር ላይ ያለ(ች) ወይም በቅርቡ ያገባ (ች) እና በጫጉላ ቤት የሚገኝ ወይም የምትገኝ (ሰው)::
**ሙሽሪት** ስ ሴት ሙሽራ::
**የሙሽራ ልብስ** ስ ሴት ሙሽራ የሰርጓ እለት የምትለብሰው ልብስ፤ ቬሎ::
**የሙሽራ ቤት** ስ ጫጉላ ቤት::
**ተሞሸረ** ግ 1. ሙሽራ ሆነ:: 2. አጌጠ፥ ተሸለመ (በሰርጉ እለት):: 3. ጫጉላ ቤት ገባ:: 4.ተከተተ፤ ከቤት ሳይወጣ በድሎት፥ በክብካቤ ተያዘ፥ ተቀመጠ::
**ሞሸላቃ** "ሞሸለቀ" ስር ተመ.
**ሞቀ** ግ 1. ጋለ፥ ተኮሰ፥ ሰማ:: 2. እሳት ላይ ትንሽ ቆየ፥ ለብ አለ፥ ሙቅ ሆነ:: 3. ሙቀት ወሰደ፥ አገኘ:: *እሳት ሞቀ::* 4. ወበቀ:: 5. (ዘይ.) ደመቀ፥ ደራ (ጨዋታ፥ ወሬ፥...)::
**ሞቀው** የደስታ፥ የኩራት ስሜት ተሰማው::
**የሞቀ** 1. የደመቀ፥ ከፍ ያለ፥ ትልቅ:: *የሞቀ አቀባበል::* 2. የተመቸ፥ የተደላደለ:: *የሞቀ ትዳር::*
**ሳይሞቅ ፈላ** (ስድብ) ያለእድሜው የጉርምስና ባህርይ ወይም አድራጎት የሚያሳይ::
**ሙቀት** ስ 1. ግለት፥ ትኩሳት:: 2. ወበቅ:: 3. የቅዝቃዜ ተቃራኒ::
**የሙቀት መለኪያ** ስ የትኩሳትን መጠን ለመለካት የሚያስችል መሳሪያ፤ ቴርሞ ሜትር::



የሙቀት መለኪያ

**ሙቅ** ቅ 1. የሚሞቅ፥ የሚተኩስ:: ስ 2. እንደ አጃ ወይም ስንዴ፥... ያለ የእህል ዱቄት፥ በተወሰነ መጠን ከውሃ ጋር ተበጥብጦና ተፈልቶ የሚጠጣ ፈሳሽ ምግብ፤ እንትክትክ ወይም አጥሚት:: 3. ከእህል ዱቄት በተለይም ከስንዴ የሚዘጋጅና በማጣበቂያነት የሚያገለግል ወፈር ያለ ፈሳሽ::
**ሞቃት** ቅ የሚሞቅ (ወቅት፥ ስፍራ፥ አካባቢ፥...)::
**ሞቅታ** ስ መጠነኛ ስካር::
**ሞቅ አለ** ግ 1. ከሚገባው መጠን ትንሽ

አለፍ፥ በዛ አለ:: *ወጡ ወው ሞቅ ብሎታል::*

**ሞቅ አለው** 1. በመጠኑ ሰከረ:: 2. ሞቀው::3. በአገኘው አስደሳች ሁኔታ የኩራት ስሜት ተሰማው::

**ተሟሟቀ** ግ 1. ደራ፥ ደመቀ:: 2. (ስፖ.) መጠነኛ የሰውነት እንቅስቃሴ አደረገ፥ ተፍታታ::

**አሟሟቀ** ግ 1.(ዘይ.) አዳመቀ፥ አቃለጠ፥ ሆይ ሆይ አለ:: 2. (ስፖ.) አፍታታ፥ አንቀሳቀሰ (ሰውነትን)::

**አሟሟቂ** ቅ ወሬ አዳማቂ፥ ሆይ ሆይ ባይ::

**ሞቀለለ** ግ ቀመቱ ረዘመ፥ ተንቀዋለለ::

**ሞቀለል (ሞቅላላ)** ቅ ረዥም፥ ቀውላላ::

**ሞቀሞቀ** ግ 1. በደንብ ባለመብሰል ወይም በሌላ ምክንያት የተነባ እንደሊጥ ሆነ (ዳቦ):: 2. በመቆየት፥ በመበሰበስ ወይም በሙቀት የተነሳ ሉክሉክ (ፍራፍሬ):: 3. በሰበሰ፥ ሉክሉክ (ቁስል)::

**አሞቀሞቀ** ዝ.ከ.

**ሞቃት "ሞቀ"** ስር ተመ.

**ሞቅላላ "ሞቀለለ"** ስር ተመ.

**ሞቅታ "ሞቀ"** ስር ተመ.

**ሞተ** ግ 1. ነፍሱ ከስጋው ተለየች፥ በህይወት መኖር አቆመ፥ በድን ሆነ:: 2. ተዳከመ፥ ቀነሰ:: *ገበያው ሞተ::* 3. ሃይሉ በጣም ተቀነሰ፥ አቅም አጣ:: *ባትሪው ሞተ::* 4. ከመጠን በላይ ለፋ፥ ደከመ:: *በስራ ብዛት ሞተ/ በሩጫ ሞተ::* 5. ቀነሰ፤ ጠፋ (ፍላጎት):: 6. የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም አቃተው (የወንድ አባለዘር):: 7. ሰነፈ ተስፋ ቆረጠ:: *ልቡ ሞተ::* 8. አንድን ነገር ከተገቢው መጠን በላይ አደረገ:: *በሳቅ ሞተ/ ሳልቅሶ ሞተ::*

**ሞተላት** 1. እጅግ በጣም ወደዳት፥ አፈቀራት:: 2. ህይወቱን ሰዋላት::

**የሞተ** ተልካሻ፥ የማይረባ፤ ሃሞተ ቢስ::

**የሞተ ነገር** ያለቀለት::

**ይሙት በቃ** ስ የሞት ቅጣት፥ የሞት ፍርድ::

**ሞተ ከዳ** ስ 1. የሞተ ሰው በህይወት እያለ ይለብሰው የነበረና ለሌላ ሰው የተሰጠ ወይም የተሸጠ ልብስ፤ ነፍስ ይማር 2. ባለቤት የሌለው እቃ::

**ሙት**[1] ቅ 1. የሞተ፥ በድን የሆነ:: 2.(ዘይ.) በጣም ደካማ፥ ሃሞቱ የፈሰሰ:: 3. እጅግ ከፍተኛ ፍቅር ያለው:: *ለልጁ ሙት ናት::*

**ሙት**[2] ቅ ለሁለተኛ መደብ ግለሰብ የተነገረውን ነገር እውነትነት ለማረጋገጥ የሚደረግ መሃላ (የተናገርኩት ነገር ሃሰት ከሆነ አንተን በሞት ልጣ እንደማለት ነው):: *ወንድሜ ሙት! ነገ እመጣለሁ::*

**ለ___ ሙት ነው___** በጣም ይወዳል:: *ለጓደኛ ሙት ነው/ ለገንዘብ ሙት ነው::*

**ሙት አመት** ስ የሟች አንደኛ አመት ወይም በየአመቱ ለሟች መታሰቢያ የሚደረግ ተዝካር::

**የሙት ልጅ** ስ አባቱ ወይም እናቱ ወይም ሁለቱም የሞቱበት ልጅ::

**ሙትቻ** ቅ ሰነፍ፥ ደካማ፥አቅመ ቢስ::

**ሞት** ስ የነፍስ ከስጋ መለየት፥ የህይወት ፍፃሜ፥ እልፈት::

**ሞት ይርሳኝ** እንደረሳሁህ እኔንም ሞት ይርሳኝ ለማለት ለጓደኛ፥ ለልጅ፥:..የሚነገር የቀልድ አባባል::

**በሞት ተለየ** ሞተ::

**የሞት ሞት** ትልቅ ቅሌት፥ ውርደት::

**የሞት ሞቱን** ፍርሃት ወይም ድካም በተሞላው ከፍተኛ ጥረት፥ ትግል፤ እንደምንም::

**የሞት ሽረት ትግል** ወሳኝ ፍልሚያ፥ ለመጨረሻ የሚደረግ ከፍተኛ ትግል::

**የሞት አፋፍ** አደገኛ ሁኔታ፥ ለሞት የቀረበ::

**የሞት ፍርድ** ስ የሞት ቅጣት እንዲፈፀም የሚያደርግ ፍርድ::

**ሟች** ቅ 1. የሚሞት:: *ሰው ሁሉ ሟች ነው::* ስ 2. የሞተ(ው) ሰው:: *የሟች ቤተሰብ በተገኘበት...::*

**ተሟሟተ** ግ ከፍተኛ ትግል ወይም ጥረት አደረገ፥ ተጋደለ::

**አሞተ** ግ አደከመ፥ አሰነፈ:: *ላስቀድሞ ልቡን ሰላሞተው ስራውን መስራት ላቃተው::*

**ሞተር** ስ ነዳጅ በማቃጠል፥ የኤሌክትሪክ ሃይልን በመጠቀም ወይም በሌላ ሁኔታ ሃይል ሊፈጥር የሚችል ወይም አንድን መሳሪያ ሊያንቀሳቅስ የሚችል የመሳሪያው አካል::

**ሞተር አጠፋ** የሞተሩን እንቅስቃሴ አቆመ::

**ሞተር ብስክሌት** ስ በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስ ወይም የሚሽከረከር ብስክሌት፤ ዶቅዶቀ (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)::

**የሞተር ዘይት** ስ የሞተርን መሽከርከር እንዲያቀላጥፍ ሞተር ውስጥ የሚጨመር ዘይት::

**ሞተረኛ (ሞተር ብስክሌተኛ)** ቅ ሞተር ብስክሌት በመጠቀም ስራውን የሚያከናውን::

**ሞት "ሞተ"**ስር ተመ.

***ሞነሞነ**

**ሞንሟና** ቅ ያማረ፥ የተዋበ፥ ሽሙንሙን (ብዙውን ጊዜ ለሴት)::

**ተሞናሞነ** ግ ተሽሞነሞነ፥ አማረ፥ ተዋበ::

**አሞናሞነ** ግ አሽሞነሞነ፥ አሳመረ፥ አስዋበ::

***ሞነደለ**

**ሞንዳላ** ቅ ደልደል ያለና ያማረ (ብዙውን ጊዜ ለሴት የሰውነት ቅርፅ)፡

**ተሞናደለ** ግ ደልደል ብሎ ያማረ ሆነ (የሰውነት ቅርፅ)።

**ተሞናደለች** ግ ሞንዳላ ሴት የሰው አይን በሚስብ ሁኔታ ተራመደች።

**አሞናደለ** ግ እንዲመቸው፥ እንዲያምርበት አደረገ።

**ሞነጨረ** ግ 1. በጫጨረ፥ አበላሸ (ለፅሁፈት)። 2.ቧጨረ።

**ሙንጭርጭር** ቅ የተበላሸ፥ የተበጫጨረ፥ አስቀያሚ (ለምሳሌ ፅሁፍ፥...)።

**ሞነጫጨረ** ግ 1. በጫጨረ (ለምሳሌ ሰውነትን)። 2. በጫጨረ፥ የማይነበብ አድርጎ ወይም አበላሽቶ ፃፈ። 3. በጣም ያልታሰበበትና ያልተደከመበት፥ እንደ ነገሩ የሆነ ፅሁፍ አዘጋጀ።

**ተሞነጫጨረ** ግ 1. ተበጫጨረ (ለምሳሌ ሰውነት)። 2. ተበጫጨረ፥ ተበላሸ (ለፅሁፈት)።

**ሞንሟና** "*ሞነሞነ"ስር ተመ.

**ሞንዳላ** "ሞነደለ"ስር ተመ.

**ሞኖፖል** ስ በአንድ የስራ መስክ በተለይ የተወሰነ ምርትን በማምረት፥ በመሸጥ፥... ረገድ ብቸኛ የሆነ ባለመብት ድርጅት። *ትንባሆ ሞኖፖል።*

**በሞኖፖል ይዞታል** ለብቻው ያለተቀናቃኝ ይዞታል።

***ሞኘ**

**ሞኝ** ቅ 1. ቂል፥ ጅል። 2. በቀላሉ የሚታለል፥ ተላላ። 3. የዋህ፥ ገር።

**ሞኝ አንግስ** ስ እቤት የሚዘጋጅ አረቄ፣ ካቲካላ።

**ሞኛሞኝ** ቅ ሞኝነት ያለበት፥ ሞኝ ቢጤ፣ ቂላቂል።

**ተሞኘ** ግ ተታለለ፥ ተደለለ፥ ተሸነገለ።

**አሞኘ** ግ አታለለ፥ አቄለ፥ ሸነገለ።

**ሞከረ** ግ 1. አንድን ነገር ለማድረግ፥ ለመስራት፥ ለማወቅ፥... ጣረ ወይም ታገለ። 2. የአንድን ነገር ምንነት፥ በትክክል መስራትና አለመስራት ወይም መበላሸትና አለመበላሸት፥... ለማረጋገጥ ፈተሸ፥ ፈተነ፥ መረመረ። 3. በመጠኑ ቻለ። *መኪና መንዳት ይሞክራል።* 4. ቀመሰ፥ አየ። 5. ጀመረ። *ሞክሮ ተወው።* 6. ለካ፥ አጥልቆ አየ (ልብስን፥ ጫማን፥...)።

**አይሞከርም** 1. አይቻልም፥ ከባድ ነው። 2. አይደረግም።

**ሙከራ** ስ 1. አንድን ነገር ለመስራት ወይም ለማወቅ የሚደረግ ጥረት። 2. የአንድን ነገር ምንነት፥ መስራትና አለመስራት፥ መበላሸትና አለመበላሸት ለማወቅ የሚደረግ ምርመራ ወይም ፍተሻ። 3. የመጀመሪያ ልምምድ።

**የሙከራ ጊዜ** ስ አዲስ የተቀጠረ ሰራተኛ ቋሚ ከመሆኑ በፊት የጠባዩና የአሰራሩ ሁኔታ የሚገመገምበት ወቅት።

**ተሞካከሩ** ግ ተፈታተኑ፥ ተፈታተሹ (በጉልበት፥ በአቅም፥ በችሎታ)።

**ተሞክሮ** ስ ከተግባር፥ ከልምድ የተገኘ እውቀት፣ ገጠመኝ።

***ሞከሸ**

**ተሞከሸ** ግ 1. ተቆላመጠ፥ በቁልምጫ ተጠራ። 2. ተሞገሰ።

**አሞከሸ** ግ 1. አቆላመጠ፥ በቁልምጫ ጠራ። 2- አሞገሰ።

**ሞከተ** ግ 1. ተባእት በግን ወይም ፍየልን አኮላሽቶ ወይም ቀጥቅጦ ቀለበ፥ አወፈረ፥ አደለበ፥ አሰባ። 2. ደለበ፥ ወፈረ፥ ሰባ።

**ሙክት** ስ ተኮላሽቶ ወይም ተቀጥቅጦ የተቀለበና የሰባ ወፍራም በግ ወይም ፍየል።

**ሞከከ** ግ 1.በጣም በሰለ (እንደኮሽም፥ ቀጋ፥... ያሉ ፍራፍሬ)። 2.(ዘይ.) በጣም ሰከረ።

**ሙክክ አለ** ዝ.ከ.

**ሞክሼ** ቅ 1. አንድ አይነት መጠሪያ ስም ያላቸው(ሰዎች)። *ሞክሼ ነን።* 2. ተመሳሳይ መጠሪያ ወይም ድምፅ ያላቸው (ሆሄያት ወይም ፊደላት)። *"አ"ና "ዐ" ሞክሼ ሆሄያት ናቸው።*

**ሞክድ** "ሙግድ"ን ተመ.

**ሞዘቀ** ግ በሙዚቃ መሳሪያ ተጫወተ፥ አዜመ።

**ሙዚቃ** ስ ለጆሮ ተሰሚነት ያለው፥ ስሜትን ሊቀሰቅስ የሚችል፥ በመሳሪያና በሰው ድምፅ ወይም በመሳሪያ ብቻ የተቀናበረ ጣእመ ዜማ።

**የሙዚቃ መሳሪያ** ስ ልዩ ልዩ አይነት ጣእመ ዜማዎችን ለማውጣት፥ ለመጫወት የሚያስችል እንደክራር፥ ዋሽንት፥ ጊታር፥ ፒያኖ፥... ያለ መሳሪያ(ስእሉን በሚቀጥለው ገፅ ተመ.)።

**የሙዚቃ ቤት** ስ በቴፕ ክር፥ በሸክላ፥... የተቀረፁ ልዩ ልዩ ዘፈኖችና የሙዚቃ ቅንብሮች የሚሸጡበት መደብር።


**ሙዚቀኛ** ቅ በኦርኬስትራ፥ በባንድ፥... ውስጥ ተቀጥሮ የሙዚቃ መሳሪያዎችን የሚጫወት።

**ሞዘዘ** ግ ቸከ፥ ለዛ አጣ፥ አሰለቸ።

**ሙዝኝ** ቅ ሞዛዛ።


**ሞዛዛ** ቅ ለዛ ቢስ፥ ቸካ።

## ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች




1. ክራር
2. መለከት
3. ዋሽንት
4. እምቢልታ
5. ከበሮ
6. ነጋሪት
7. አታሞ
8. ማሲንቆ
9. ፋንፋን
10. ቃጭል
11. በገና
12. ፀናፅል

## ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች




1. አኮርዲዮን
2. ክላርኔት
3. ቫዮሊን
4. ቪዮላ
5. ሃርሞኒካ
6. ትራምፔት
7. ፒያኖ
8. ጊታር
9. ሳክስፎን

**ተሟዘዘ** ግ ተመናቸከ፥ ለዛ አጣ።

**ሞዠቀ** ግ ፈገፈገ፥ ፈተገ (ብዙ ጊዜ ሻካራ በሆነ ነገር)።

**ሞያ "ሙያ"ን ተመ.**

**ሞያሌ "ሙጃሌ" ን ተመ.**

**ሞይደር** ስ ወተት መስል ፈሳሽ የሚወጣው ሃረግ የሚመስል የእፅዋት አይነት።

***ሞደሞደ**

**ሞድሟዳ** ቅ አሳባቂ፥ ወሬኛ።

**ተሞዳሞደ** ግ አሳበቀ፥ ወሬ ከወዲያ ወዲህ አመላለሰ።

**አሞዳሞደ** ዝ.ከ.

**ሞዴል**[1] ስ 1. ካሁን በፊት ላለ ወይም ወደፊት ለሚሰራ ነገር እንደምሳሌ፥ እንደማስረጃ ሆኖ የሚቀርብና የሚታይ ናሙና፥ ቅርፅ፥ምስል። 2. ለስእልና ቅርፃቅርፅ ሙያ ጥናት ሲባል በሙያተኞች ፊት በተለያየ አቋም በመሆን ልዩ ልዩ አካላዊ ቅርፆችን፥ ስሜቶችን፥... የሚያሳይ ወይም የምታሳይ (ሰው)። 3. በተለያየ ፋሽን የተሰሩ ልብሶችን፥ ጫማዎችን፥ ጌጣጌጦችን፥... በመልበስ ለንግድ የሚያስተዋውቅ፥ የሚያሳይ ጥሩ የሰውነት ቅርፅና ቁመና ያለው ሰው (ብዙ ጊዜ ሴት)።

**ሞዴል**[2] ስ 1. የተለያዩ ጉዳዮችን ለመመዝገብ የተዘጋጀ ቅፅ ወይም ሰነድ ወይም ካርኒ። 2. መስሪያ ቤቶች ለሰራተኞቻቸው በቅድሚያ የሚሰጡትና ከደመወዛቸው ላይ ተቆራጭ ሆኖ የሚከፈል የገንዘብ ብድር።

**ሞዴስ** ስ ሴቶች በወር አበባ ጊዜ ከሙታንታ ውስጥ አድርገው የሚታጠቁት ከጥጥና ከለሰለሰ ጨርቅ የሚሰራ የወር አበባ ማምጠጫ።

**ሞድ** ስ ፋሽን። *በአዲሱ ሞድ የተሰፋ ቀሚስ።*

**ሞድሟዳ "*ሞደሞደ"** ስር ተመ.

**ሞጀረ** ግ 1. ሳይመጥን፥ ሳይለካ በብዛት ጨመረ። *ከወጡ ውስጥ ጨውን ሞጀረችው*። 2- የማይገባውን ወይም የማይስማማውን ነገር ጨመረ። *አፈሩን አይኑ ውስጥ ሞጀረበት።*

**ሞጀጀ** ግ 1. ሞገገ፥ ከሳ፥ መነመነ፥ ሰለሰለ፥ ቀጠነ። 2. ረዘመ፥ ተንቀዋለለ።

**ሞጃጃ** ቅ 1. ሞጋጋ፥ ከሲታ፥ መንማና። 2. ረዥም፥ ቀውላላ።

**ሞጃ** ስ ሃብታም፥ ዲታ፥ ባለጠጋ።

***ሞገሰ**

**ሞገስ** ስ ክብር፥ ተወዳጅነት።

**ሞገስ አገኘ** ተከበረ፥ ተወደደ።

**ሙገሳ** ስ ምስጋና፥ አድናቆት፥ ውዳሴ።

**ተሞገሰ** ግ ተመሰገነ፥ ተወደሰ።

**አሞገሰ** ግ አመሰገነ፥ አወደሰ።

**ሞገተ** ግ 1. በንብረት፥ በወንጀል፥... ምክንያት ፍርድ ቤት ወይም ሸንጎ ላይ ተከራከረ። 2. ነዘነዘ፥ ጨቀጨቀ፤ ተከራከረ።

**ሙግት** ስ በፍርድ ቤት ወይም በሸንጎ ላይ ከሳሽና ተከሳሽ የሚያደርጉት ክርክር፥ የሚነጋገሩበት ጉዳይ፥ እሰጥ አገባ።

**ተሟገተ** ግ 1. አንድ አቋም ይዞ "እንዲህ ነው" ወይም "እንዲህ ይሁን" እያለ ተከራከረ። 2. ተጨቃጨቀ።

**አሟገተ** ግ 1. አከራከረ፥ አጨቃጨቀ(ጉዳዩ)። 2. በዳኝነት ተሰይሞ ከሳሽና ተከሳሽን አነጋገረ፥ አከራከረ።

**ሞገደ** ግ አወከ፥ እምቢተኛ ሆነ፥ አስቸገረ፥ አሻፈረኝ አለ።

**ሞገድ** ስ እልህ፥ ሃይል።

**ሞገደኛ** ቅ ሃይለኛ፥ እልሀኛ፥ እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ባይ።

**ሞገድ** ስ 1. በነፋስ ምክንያት የሚፈጠር የባህር መናወጥ። 2. በአየር ላይ የሚተላለፍ የድምፅ ስርጭት።

**ሞገገ** ግ በጣም ከሳ፥ አጥንቱ ገጠጠ።

**ሞጋጋ** ቅ ከሲታ፥ አጥንቱ የገጠጠ።

**ሞጌ** ዝ.ከ.

**ሞጌው ወጣ** እጅግ ከሳ፥ መነመነ፥ አጥንቱ ገጠጠ።

**ሞጋሳ**

**የሞጋሳ ልጅ (ሞጋሳ)** ስ የማደጎ ልጅ።

**ሞጋጋ "ሞገገ"** ስር ተመ.

**ሞጌ** ዝ.ከ.

**ሞግዚት** ስ 1. ልጅን የሚያሳድግ፥ የሚንከባከብ ቅጥር ሰራተኛ። 2. ልጅ ራሱን እስከሚችል ድረስ በበላይነት የሚያስተዳድር፥ የሚንከባከብና ስለሱ ሆኖ ማንኛውንም ጉዳይ የሚፈፅም ሰው።

**ሞግድ "ሙግድ"ን ተመ.**

**ሞጠለቀ** ግ ሰረቀ፥ መነተፈ፥ ሞጨለፈ።

**ሙጥልቅ** ቅ ዋና ሌባ።

**ሞጠለቅ (ሞጥላቃ)** ዝ.ከ.

**ሞጠሞጠ** ግ ሾለ።


**ሙጢ [አፍ]** ቅ ነገረኛ፥ ምላሰኛ።

**ሞጥሟጣ** ዝ.ከ.

**ተሞጣሞጠ** ግ ተሳደበ፤ ብዙ ተናገረ፥ ለፈለፈ።

**አሞጠሞጠ** ግ 1. ሾለ፥ አሞለሞለ። *ቆለሉ አሞጥሙጧል።* 2. ለመሳደብ ወይም ለመናገር ተዘጋጀ፥ አፉን አሾለ።

**ሞጣህት** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በአንገት እንዲጠለቅና በደረት በኩል ወደታች እንዲንጠለጠል ሆኖ የተሰራ፥ ቄስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲያገለግል ከሚለብሳቸው አልባሳት አንዱ።



ሞጣህት

**ሞጥሟጣ** "**ሞጠሞጠ**" ስር ተመ.

**ሞጨለሰ** "**መጨለሰ**"ን ተመ.

**ሞጨለፈ** ግ 1. ቀማ፥ ነጠቀ (በድንገት)። 2.ሰረቀ።

**ሞጨለፍ(ሞጭላፋ)** ቅ ቀማኛ፥ ነጣቂ፥ ሌባ።

**ሞጨሞጨ** ግ አይናር ያዘ፥ እንባ አቀረረ፥ ተጨናበሰ (አይን)።

**ሞጭሟጫ** ቅ አይኑ አይናር የያዘ፥ እንባ ያቀረረ፥ ጨንባሳ።

**አሞጨሞጨ** ግ ሞጨሞጨ።

**ሞጨጨ (ሟጨጨ)** ግ 1. አጣበቀ። 2. ተጣበቀ፥ ያዘ።

***ሙጭጭ አለ*** ግ 1. አልለይ፥ አልለቅ አለ፤ ተጣበቀ። *ሰውየው ልጅቷ ላይ ሙጭጭ አለ።* 2. ድርቅ፥ ሙዝዝ አለ። *በሰው እቃ ሙጭጭ አለ።*

***ሙጫ*** ስ 1. ከዛፍ የሚወጣና ፈሳሽነት ያለው መጣብቅ። 2. ከያዘ የማይለቅ።

**ሞጫጨረ** "**ሟጨረ**" ስር ተመ.

**ሞጭሟጫ** "**ሞጨሞጨ**" ስር ተመ.

**ሞፈር** ስ ወፈር ረዘም ካለ እንጨት ተጠርቦ የሚሰራና ከቀንበር ጋራ በምራን የሚያያዝ የእርሻ መሳሪያ።

**ሞፈር ሰቀል** ቅ (የን.አነ.) በቅርብ ጊዜ የእርሻ ስራውን ትቶ ከተማ የገባ ገጠሬ፥ ባላገር።

**ሞፈር ዘመት [እርሻ]** ስ ካሉበት አካባቢ ርቆ በመሄድ የሚታረስ እርሻ (አሰያየሙ ሞፈር ተሸክሞ መሄድን ያመለክታል)።

**ሞፎ** ስ 1. የጥራት ደረጃው ዝቅተኛ የሆነ ፉርኖ፥ ዳቦ። 2.(ዘይ.)በጣም ወፍራም ሆኖ አቅም የሌለው (ሰው)።

**ሚ** የ "መ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

**ሚለጠ** ግ 1. በጣም ለዘበ፡ ለሰለሰ፡ ሻካራነት የሌለውና ዳላጣ ሆነ (ለምሳሌ ያልተወቀረ የእጅ ወፍጮ)። 2. ስራ ፈት፡ ማጋጣ ሆነ።

**ሚላጣ** ቅ 1. ሻካራ ያልሆነ፡ በጣም የለዘበ፥ የለሰለሰ፡ ዳላጣ። 2. (ዘይ.) ስራ ፈት፡ ዋልጌ።

**አሚለጠ** ግ 1. አዳለጠ። 2. አማገጠ፥ ዋልጌ አደረገ።

**ሚለጨ** ግ ድጥ ሆነ፥ ዳለጠ፥ አልያዝ አልጨበጥ አለ።

***ሙልጭልጭ*** ቅ 1. ዳላጣ፥ ለመያዝ ወይም ለመጨበጥ፥ ለመርገጥ የሚያስቸግር። 2. (ዘይ.) በቃሉ የማይገኝ፥ አታላይ። 3. ሊያገኙት ሲፈልጉ የማይገኝ፥ እዚህ ነው ሲሉት ሌላ ቦታ የሚገኝ (ሰው)።

***ሙልጭልጭ አለ*** ግ 1. አልያዝ አልጨበጥ አለ፥ ማላጋ ሆነ። 2. (ዘይ.) በቃሉ የማይገኝ ሆነ፥ ዋሸ፤ በፈለጉት ቦታ ሳይገኝ ቀረ፥ አልገኝ አለ።

**ተሙለጨለጨ** ዝ.ከ.


**አሙለጨለጨ** ግ አልያዝ አልጨበጥ አለ፥ ማላጋ ወይም ዳላጣ ሆነ።

**አሚለጨ** ግ አልያዝ አልጨበጥ አሉ፥ አልረገጥ አለ፥ ማላጋ ሆነ፥ አዳለጠ።

**ሚሚ** ግ ጠጣር የነበረው ነገር ቀለጠ፥ ወደ ፈሳሽነት ተለወጠ፤ ሚሸሸ።

**ሚረ**

**አሚረ** ግ ቀለሰ።




1.ሞፈር
2.ቀንበር
3.ማነቆ
4.ምራን
5.እርፍ
6.ድግር
7.ወገል
8.ማረሻ
9.የማነቆ ጠፍር
10.የወገል ጠፍር
11.ቅትርት

***ሚረተ**

**ሚርት** ስ 1. የመጥፎ ነገር ትንቢት፥ ምልኪ (ለምሳሌ ውሻ ካነጠሰ፥ እንቅፋት ከመታ፥.... መጥፎ ነገር ሊያጋጥም ይችላል የሚል እምነት):: 2. በሌላው ላይ መጥፎ ነገር ወይም ጉዳት እንዲያደርስ ተብሎ ጉዳቱ እንዲደርስበት በተፈለገው ሰው ወይም አካል አካባቢ የሚቀበር፥ የሚቀመጥ ወይም የሚጣል፥... መተት፥ ደንቃራ::

**ሚርተኛ** ቅ 1. በሌላው ላይ ክፉ የሚተነብይ፥ የሚመኝ፤ የሚያሚርት:: 2. ሚርት ወይም ደንቃራ የሚጥል::

**አሚረተ** ግ 1. በሌላው ላይ መጥፎ፥ ክፉ ነገር ተነበየ:: 2. ደንቃራ ጣለ፥ መተት አደረገ::

**ሚሰሰ** ግ ነጨ፥ ነቀለ (ሳርን፥ እህልን፥...በእጅ)::

***ሚሸ**

**ሙሽት** ስ አዲስ በተሚሸ ምጣድ ላይ ወዲያው የሚጋገር እንደቂጣ ያለ እንጀራ::

**አሚሸ** ግ 1. እንደ ምጣድ፥ ድስት፥... ያለን አዲስ የሸክላ እቃ እንዲጠነክር፥ እንዲለዝብና ለተፈለገው አገልግሎት ብቁ ሆኖ እንዲገኝ በእሳት ለበለበ፤ እንደ ጥፍጥሬ፥ ጎመን ዘር፥... ባለ የቅባት እህል አሸ፥ ወለወለ:: 2. (ዘይ.) ለመጀመሪያ ጊዜ ሰራ፥ አከናወነ ወይም በአንድ ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቀመ::

**ሚሸሸ** ግ በመተንፈስ፥ በመክሳት፥ በመድረቅ፥... ቀድሞ ከነበረው መጠን ቀነሰ፥ ጎደለ፥ አነሰ፤ ከሰመ::

**ሚቾ** " **ሞተ**" ስር ተመ.

**ሚነነ** ግ እየቀጠነ፥ እያነሰ ሄደ (ብዙ ጊዜ ለፈትል)::

**ሞናና** (**ሙናና**) ቅ አነስ፥ ቀጠን ያለና የሚያምር::

**አሚነነ** ግ አቀጠነ፥ ቀጭን አደረገ (ፈትልን)::

**ሚዠ** (**ሚጀ**) ግ 1. ቀለም፥ ቅባት፥... ቀባ፥ ለቀለቀ:: 2. አለዘበ፥ አለሰለሰ፥ ፈገፈገ (ጅማትን፥ በትርን፥...)::

**ሚደደ** ግ 1. ከስሩ ጥርግ አድርጎ፥ ቆረጠ:: 2.(ዘይ.) ሰረቀ፥ ሞለጨ::

**ሚደድ** ቅ ጭርስ አድርጎ ጠራርጎ የሚወስድ ሌባ::

**ሚጀ** "**ሚዠ**"ን ተመ.

**ሚጠጠ** ግ 1. ምንም ሳያስቀር ጥርግ አድርጎ አነሳ፥ ወሰደ፥ ባዶ አደረገ፥ ጨረሰ (ቅቤን፥ ድልህን፥ ቡኮን፥...):: 2. ሰረቀ፥ ባዶ አስቀረ::

**ሙጣጭ** ቅ የመጨረሻ፥ ተሚጦ የቀረ፥ እላቂ::

**ሚጠጥ** [**ሌባ**] ቅ ምንም ሳያስቀር ጠርጎ የሚወስድ፥ ሞሽላቃ ሌባ፤ ሚደድ፥ ሌባ::

**ተሚጠጠ** ግ አለቀ፥ ባዶ ቀረ::

**አሚጠጠ** ግ ጨረሰ፥ ባዶ አስቀረ::

**ማሚጠጫ** ቅ የመጨረሻ:: እገሌ *ለወላጆቹ ማሚጠጫ [ልጅ] ነው*::

**ሚጨ** ግ ፋቀ፥ ጠረገ፥ ፈገፈገ፥ አፀዳ (ጥርስን)::

**መሚጫ** (**ማሚጫ**) ስ የጥርስ መፋቂያ::

**አሚጨ** ግ ሚጨ::

**ሚጨረ** ግ 1. በጥፍሩ ወይም በሹል ነገር ጫረ፥ አቆሰለ፤ ቧጨረ:: 2. ላይ ላዩን አረሰ::

**ሙጭርጭር** ቅ የተበላሸ፥ የማይነበብ (ፅሁፍ)::

**ሞጫጨረ** ግ 1. ቧጨረ፥ ሰለጠጠ፥ ሰነጣጠቀ:: 2. የተበላሸ፥ የማይነበብ ፅሁፍ ፃፈ:: 3. እንደነገሩ ፃፈ፤ በሚገባ ያልታሰበበትና ያልተለፋበት ፅሁፍ አዘጋጀ::

**ሚጨራ**[1] ስ ከጤፍ ጋር የሚበቅል ፍሬው ጤፍ የሚመስል ሳር::

**ሚጨራ**[2] (**ሚጫራ**) በእንጀራ ሰበከት ላይ የሚገኝ፥ እጅ ላይ የሚጣበቅና አራራ የሚመስል ነገር::

**ሚጨጨ** "**ሞጨጨ**" ስር ተመ.